
# ሐመር

የካቲት 1985 ቅጽ ፩ ቁጥር ፱



✣ ልሳን

✣ ጠበል

✣ ለበረከት ሁን

✣ እመ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ

✣ የታተመ ፍቅር

✣ የተወደዱ እግሮች

✣ ቅዱስ ጋብቻ

© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org



የመጽሔታችን ማኅበርተኛ መሆን ለምትፈልጉ ሁሉ።

ለከ/ሀገር የዓመቱን ብር 38.40 ለአዲስ አበባ ብር 37.80 ወይም

ለከ/ሀገር የመንፈቁን ብር 19.20 ለአዲስ አበባ ብር 18.90 በአድራሻችን በአቶ ዮሐንስ አፈወርቅ ብትልኩ ስም እያንዳንዱን እትም በአድራሻችሁ የምታገኙ መሆኑን ስንገልጽ በመንፈሳዊ አክብሮት ነው።

አቶ ዮሐንስ አፈወርቅ
ሐመር መጽሔት ዝግጅት
የመ.ሣ.ቁ. 80078
አዲስ አበባ

# ሐ መ ር

መጀመሪያ ዓመት ቁጥር 2

የካቲት 1985 ዓ.ም.


## ይዘት


1. ከአዘጋጁ .......................... 1
2. የማኅበሩ መልእክት .............. 2
3. ደብዳቤዎቻችሁ .................. 3
4. ትምህርተ ሃይማኖት
   - ❖ ሦስትነት በአንድነት.......... 5
   - ❖ ልሳን .......................... 7
   - ❖ ጠበል ........................10
   - ❖ እመ አምላክ በመ. ቅዱስ.....13
5. ኪነ ጥበብ
   - ❖ የታተመ ፍቅር.................15
   - ❖ የተወደዱ እግሮች............19
6. እናስተዋውቃችሁ
   - ❖ የቦረዳው ድንቅ ዋሻ ..........20
   - ❖ የሐመረ ብርሃን ገዳም.........25
7. ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
   - ❖ ቅዱስ ጋብቻ...................29
   - ❖ ሦስቱ አርእስተ ኃጣውዕ......33
8. በረከተ ወንጌል
   - ❖ ጸሎትህ ተሰምቶልሃል .......34
   - ❖ ለበረከትም ሁን! ..............38



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።


## ከአዘጋጁ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን። ስለማይመረመር ጸጋው ለአምላካችን ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብን እናስቀድማለን።

ነቢይነትን ከክህነት ጋር አስተባብሮ ይዞ የነበረው ሕዝቅኤል እግዚአብሔር ለልዩ ተልእኮ በፈለገው ጊዜ መጀመሪያ የተሰጠው ትእዛዝ ተነሥቶ በእግሩ እንዲቆም ነበር። እርሱም በትእዛዙ መሠረት ተነሥቶ በእግሩ ቆሟል ሕዝ.2፥1። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ጸጋ አድሮበታል። የተሰወረ ዕውቀት ተገልጾለታል፤ ወደ አሳዛኙ የእሥራኤል ወገን ተልኳል–የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያሰማ።

ይህ ነቢይ ለእሥራኤል ከተናገረው መካከል፤

«ኃጢአተኛውም ከአደረጋት ኃጢአት ሁሉ ቢመለስ ትእዛዜንም ሁሉ ቢጠብቅ ፍርድንና ቅን ነገርንም ቢያደርግ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም።» ሕዝ.18፥21።

የሚል ይገኝበታል። የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ዓለሙ ሁሉ ከበደሉ እንዲመለስና በሕይወት እንዲኖር በመሆኑ ዘወትር ሕዝቡን የሚጠራው ወደንስሐና ሕይወት ነው፤ ሞት ወደሌለበት ዘለዓለማዊ ሕይወት። ይህንን ጥሪ እንዲናገር፣ ሕዝቡንም ለንስሐ ሕይወት እንዲጠራ የተላከው ሕዝቅኤል ድምፁን ከፍ አድርጎ የንስሐ ጥሪውን በፈቃደኝነት ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ አስተጋባው። ግሩም ምርጫ፣ ግሩም ተልእኮ ነበር። እግዚአብሔር ለአገልግሎት የመረጣት፣ ወደ ሕዝቡም የላካት በፊቱም የቆመች ሕይወት የተመሰገነች ናት። የሕዝቅኤል ሕይወት ተመረጠች፤ በእግዚአብሔር ፊትም ቆመች፤ የሕይወት ጥሪን እንድታስተላልፍ ወደ ሕዝቡ ተላከች። የተወደደች ሕይወት።

ዛሬ የምንኖርባት ዓለምና በውስጧ ያሉ የሰው ልጆች ሁሉ እንደቀደሙት ሕዝበ እሥራኤል በፈጣሪአቸው ፊት በአመፅ ቆመዋልና እግዚአብሔር ወደዚህ ሕዝብ የሚሄድና የንስሐ ጥሪውን የሚያስተላልፍለት በእግዚአብሔርም ለመመረጥና በፊቱም ለመቆም የተዘጋጀ ሕይወት ይፈልጋል። ይህንን የአዋጅ ጥሪ የምትናገርለት የሕዝቅኤል ምሳሌ ቤተ ክርስቲያን ነች። በቤተ ክርስቲያን አድሮ ዛሬም እንደገና የነቢዩን የጥሪ ቃል እነሆ ወደምእመናን ያስተጋባል። ሐመር (ቤተ ክርስቲያን) ይህን ቃል ተሸክማ የእያንዳንዱን ምእመን የልቡና በር እያንኳኳች ለሕይወት ልትጠራ እነሆ ጉዞዋን ከጀመረች ውላ አደረች። ከእግዚአብሔር የተሰጣትን ተልእኮ ይዛ ወጥታ የበደለ ሁሉ ከኃጢአት ቢመለስ፣ ንስሐ ቢገባ፣ በቅንነት መንገድ ቢሄድ፣ ከጥፋት ቢርቅ፣ ልቡናውን ለእግዚአብሔር ቢያስገዛ ፈጽሞ ሞት በሌለባት ተስፋ የቅዱስ ሥጋውና የክቡር ደሙ ተቀባይ ቢሆን ለዘለዓለም በሕይወት ይኖራል ዮሐ.6፥46–59። ከቶም አይሞትም በማለት ሐመር ጥሪዋን ታቀርባለች።

በዚህ የሐመር ጥሪ ሕይወታችንን መርምረን በእግዚአብሔር ፊት በሃይማኖት ለመቆም፣ መልእክቱንም ለዓለም ልንሰብክ ለሚቀርብልን ተልእኮ እሺ! በጄ! ብለን ልንጓዝ፣ የሚነገረንንም የንስሐ ጥሪ ሰምተን ከኃጢአት ራሳችንን በመለየት ልባችንን ከክፋትና ተንኮል በማጽዳት ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙን ያለጥርጥር እየተቀበልን እውነተኞች ክርስቲያኖች ለመሆን እንድንበቃ የነቢያትና የሐዋርያት አምላካቸው በቸርነቱ ይርዳን።

ጸጋ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን።


ዋና አዘጋጅ – ብርሃኑ ጎበና ካሣ

ም/ዋና አዘጋጅ – ዲ. እሸቱ ታደሰ ወንድም አገኘሁ

✉ 80078/1283

☎ 12–34–25

አዲስ አበባ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

## የማኅበረ-ቅዱሳን ዓርማ ይዘትና ትርጉም

ማኅበሩ ማኅበረ ቅዱሳን የተባለበትን ምክንያት በመዘርዘር ባለፈው እትማችን ማቅረባችን ይታወሳል። ዛሬ ደግሞ የማኅበሩ ዓርማ በውስጡ ምን እንደያዘና የሚያስተላልፈው መልእክት ምን እንደሆነ እናቀርባለን። የማኅበሩ ዓርማ በመጽሔታችን ሽፋን በስተቀኝ የሚገኘው ነው።

ዓርማው ክብ ነው — ክብ መሆኑ የዓለምን ክብነት ያመለክታል። የማኅበሩ ዓላማ ለዓለም ሁሉ እንድትሰበክ የተሰጠችውን ሐዲስ ሕግ፣ ወንጌልን ማስተማር ነውና ለአገልግሎቱ እግዚአብሔር የፈቀደለትን ያህል የሚሰፋ እንጂ ገደብ የሌለው መሆኑን ያሳያል ማር.28፥19፤16፥15።

ርግብ — የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። ማኅበሩ መንፈሳዊ እንደመሆኑና አገልግሎቱም ከአበው አሠረ ፍኖት ፈቀቅ የማይል የመንፈስ ቅዱስ መሪነት በእጅጉ የሚያስፈልገው መሆኑን በማመን በፈለገ ዮርዳኖስ ጌታችን በተጠመቀ ጊዜ ነገረ እግዚአብሔር (ምሥጢረ ሥላሴ) ሲገለጥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መታየቱን፣ ለሐዋርያት ቋንቋ መግለጡን ለማስታወስና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በዓለሙ ሁሉ ላይ የሚሰፍንና ወሰን የሌለው መሆኑን ያመለክታል። ማቴ.3፥16። ማር.1፥10። ሉቃ.3፥22። ዮሐ.1፥32–34። የሐዋ.2፥4። ኢዩ.2፥28–32።

አርባዕቱ እንስሳ — እነዚህ የእግዚአብሔርን መንበር የሚሸከሙ መላእክት (ኪሩቤል) ናቸው። በሌላም በኩል አራቱም ወንጌላውያን በእነዚህ አርባዕቱ እንስሳ ተሰይመዋልና በዚሁ ምሳሌ ማኅበሩ የሚያበረክተው መንፈሳዊ አገልግሎት መሠረቱ ቅዱስ ወንጌልና የአበው ትምህርት መሆኑን ይገልጻል። ራእ.4፥7–9። ሕዝ.1፥10። ኢሳ.6፥2–3።

ጸናጽል — ከበሮና መቋሚያ:- አስቀድሞ ሕዝበ እሥራኤል ባሕረ ኤርትራን ተሻግረው ሲወጡ ከእነርሱም በኋላ እነቅዱስ ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት የዘመሩበት እንዲሁም ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ እግዚአብሔርን በግዕዝ፣ በእዝልና በአራራይ ዜማ ባመሰገነ ጊዜ ለስብሐተ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው የኢ.ት.ኦ.ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን አንጡራ ሀብት መሆናቸውንና የማኅበሩ ትምህርትም ሆነ ዝማሬው ከቅዱስ ያሬድ የዜማ ሕግ ከቤተክርስቲያንም ሥርዓተ መዝሙር የማይወጣ መሆኑን ያሳያል።

ከዚሁ ጋር ምሥጢሩ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጅ እግሩን በብረት መቸንከሩን ራሱን በበትር መመታቱን፣ በቀኝና በግራ ፊቱን መፀፋቱንና ከግራ ወደቀኝ ከቀኝ ወደግራ፣ ከኋላ ወደፊት ከፊት ወደኋላ እያዳፉ ያንገላቱት መሆኑን የምናስታውስባቸውና የምንገለገልባቸው መሆኑን በጠሊቅ ያስተምራል። 2ሳሙ.6፥5። ዘዳግ.15፥20። መዝ.150፥3–5። ማቴ.26፥57–68፤27፥15–50። ማር.15፥1። ሉቃ.22፥23–71፤23፥1–49።

መስቀል — በክቡ ውስጥ ከላይ እስከታች ድረስ የቆመ መስቀል አለ። የመጾር መስቀል ነው። ዲያቆናት በቅዳሴ ጊዜ የሚይዙት። በመስቀሉም ላይ የተጠመጠመ መሰላል የሚመስል ጨርቅ አለ፤ ሰበን ይባላል። መስቀሉ በክቡ መካከል መተከሉ ጌታችን በማዕከለ ምድር (ቀራንዮ) ለዓለም ሁሉ ቤዛ ሆኖ መሰቀሉን የሚያጠይቅ (የሚያስረዳ) ሆኖ በመሰላል መልክ በመስቀሉ ላይ የተጠመጠመው ጨርቅ እመቤታችን በቶማስ አማካኝነት ለሐዋርያት የሰጠቻቸው የመግነዟ መታሰቢያ ነው። እንዲሁም በመሰላል መልክ መሠራቱ እመቤታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሉዛ ባያት ከምድር እስከሰማይ በደረሰችው መሰላል ስለምትመሰል፤ በእርሷም መሰላልነት በመስቀሉ ዙሪያ መጓዝና መንግሥተ ሰማይን ገንዘብ ማድረግ እንደሚገባ ለማሳወቅ ነው። ማቴ.27፥32–35። ማቴ.27፥59። ዘፍጥ.28፥10–17። ዮሐ.19፥27። ማቴ.16፥24። ሉቃ.9፥23።

መላእክት — በመስቀሉ ግራና ቀኝ ሁለት ክንፋቸው የተጋጠመ መላእክት አሉ። እነዚህም ዘወትር በመስቀሉ ዙሪያ የሚጓዙትንና መስቀሉን ተመርኩዘው፣ ወላዲተ አምላክን ወገን አድርገው በአማላጅነቷ በመታመን የሚኖሩትን ምእመናንና ቤተክርስቲያንን በአማላጅነታቸውና በክንፈ ረድኤታቸው የሚጠብቋት መሆኑን ለማመልከት ነው። መዝ.90፥11–12። መዝ.33፥7። ዳን.3፥19–29። የሐዋ.12፥11። ማቴ.18፥10። ቅዳሴ እግዚእ።

በመላእክት አክናፍ መካከል ያለች ሰዎችም በውስጧ ያሉባት መርከብ:- መርከቢቱ የቀደመችውን የኖህ መርከብ ታስታውሰናለች። በእግዚአብሔር የታመኑ ኖህና ቤተሰቦቹ ከጥፋት ውኃ የዳኑባት ናትና። በዚሁ አንፃር ወላዲተ አምላክን እንድናስብ ታስገድደናለች። የጥፋት ውኃ ምሳሌ በነበረ ምልዓተ ኃጢአት በዓለም ባሕር ጠልቆ ለዲያብሎስ ባርያ የሆነ የሰው ዘር ሁሉ የዳነበት፣ የዓለም ቤዛ መድኃኒታችን የተገኘባትና የተዋሐዳት እርሷ አማናዊቱ መርከብ ናትና። በሦስተኛ ደረጃ ግን የቤተ ክርስቲያንን ነገር ታሳስበናለች። ዛሬ በዓለም ባሕር ላይ የኃጢአት ማዕበል የሚያናውጠው የሰው ልጅ በኖህ መርከብ በተመሰለችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተገኝቶ እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ በሃይማኖትና በምግባር በትሩፋትም በመጽናት ለሰላማዊው ዘለዓለማዊ መንግሥት መብቃት የሚያስፈልገው መሆኑን ለማስገንዘብ፤ ይህም የሕይወት ጉዞ ዘወትር በመላእክት ጥበቃና ቡራኬ ጭምር የሚቃና መሆኑን ለማሳየት ነው። ዘፍ.7፥1–24። ሮሜ.5፥12–21። ኢሳ.53፥10–11። ማቴ.8፥23። ያዕ.2፥14–26። ራእ.2፥1። ራእ.3፥1።

በክበቡ ውስጥ ያሉት ቅዱሳት መጻሕፍት:- ለቤተክርስቲያን ትምህርት መሠረቷ ቅዱሳት መጻሕፍት በመሆናቸው ቃላቸውን የጠበቁ ምእመናን ከጥፋት እንደሚድኑ ሁሉ መሠረታችንን ቃለ እግዚአ ብሔር አድርገን በሕጉና በትእዛዙ ብንኖር በምድር በቤተ ክርስቲያን ከዓለምና ከኃጢአት፣ በሰማይ በመንግሥተ ሰማይ ከገሐነም እሳት እንድናለን ለማለት ነው። ኢያ.1፥5–9። ማቴ.24፥35። ያዕ.1፥22–25።

ቀስተ ደመና — ቀስተ ደመናው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለ የምሕረት ኪዳን ምልክትና የረድኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። ከምን ተነስቶ ከየት ላይ እንደሚያበቃ አለመወሰኑ የእግዚአብሔር ረድኤቱና ጥበቃው ወሰን የሌለው ኪዳኑም የማይለወጥ ዘለዓለማዊ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው። ዘፍ.9፥8–17። መዝ.138፥6–12። ሰቆ.ኤር.3፥22።

ቀለማት — ነጭ፣ የቅዱሳን ልባቸው፣ መንገዳቸው፣ ሕይወታቸው ንጹሕ መሆኑን። አረንጓዴ፣ ልምላሜ ጽድቅን። ብጫ፣ ፍቅር መንፈሳዊትን (በክርስቶስ ያለችውን)፤ ተስፋ መንግሥተ ሰማያትን። ቀይ፣ የክርስቶስን መስዋእትነት፤ የቅዱሳን ሰማዕታትን ጽናትና ተጋድሎን የሚያመለክት ነው። አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ፣ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ነው። ማኅበሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እንደሆነ ለመግለጽ ነው።

ወለእግዚአብሔር ስብሐት

© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም.

# ደብዳቤዎች

በዚህ ዓምድ ከአንባብያን የተላኩ ገንቢ አስተያየቶችን፥ መንፈሳዊ ምክሮችንና የተለያዩ ጥያቄዎችን ከነመልሳቸው እናቀርባለን።

## የጥያቄዎቻችን መልሶች

ሀ. ለሰም

ታመው የነበሩ ሁሉ ባለፈው ሳምንት ዓርብ ከታረደው በግ ሥጋና ደም ተመግበው ከበሽታቸው ዳኑ።

ለወርቅ

በኃጢአት በሽታ ታመው የነበሩ የአዳም ልጆች ሁሉ በዕለተ ዓርብ በቀራንዮ በተሰዋው አማናዊ በግ – ኢየሱስ ክርስቶስ – ሥጋና ደም (በቅዱስ ቁርባን) ነጹ፥ ዳኑ።

ለ. ለሰም

እባክሽን በእኔ ሞት በቅርብ ወደሚገኘው የእኔ ቤት ልጅሽን ይዘሽ በማለዳ ነይ።

ለወርቅ

ወላዲተ አምላክ ሆይ ከዚህች ዓለም በሞት በተለየሁ ጊዜ ከፍርድ እድን ዘንድ ወደ ምድረ ግብፅ ይዘሽው የተሰደድሽውን የልጅሽን ቸርነት አማልደሽ ወደ እኔ አምጪልኝ።

ሐ. አቤልና ቃየል እናትና አባታቸው ተፈጠሩ እንጂ አልተወለዱም፤ ጡትም አልጠቡም። እነርሱ ግን ለመጀመሪያ ጡት ጠቡ። ለመጀመሪያ ጊዜም ተወለዱ።

✣

## ከአንባብያን

በስመ አብ ወወልድ ወመንደስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ለማ/ቅ መጽሔት ዝግጅት ክፍል ለዚህ የተቀደሰ ተግባር ያዘጋጃችሁ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን። በዚህ አሁን ባለንበት ወቅት የእናንተ ዓይነቱን መንፈሳዊ ምግብ የሚመግቡ መጽሔቶችን ማግኘት ታላቅ እድል ነው። ይህ ትውልድ የኢ.ት.ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ሃይማኖትና ማንነት አውቆ ከሰይጣናዊ ተግባራት ተወግዶ እውነተኛውን የእግዚአብሔር መንገድ እንዲከተል የምታስተምር በመሆኗ ለዚህ ተግባሯ መሳካት የኃያሉ የእግዚአብሔር ዕርዳታና ጥበቃ አይለያት።

ወንድማገኝ ሀይሉ

አሜን።

✣

ባለችኝ ቁንፅል አስተሳሰብ ማስገንዘብ የምፈልገው የጀመራችሁት ሥራ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነው። ነገር ግን ሥጋ ለባሽ እንደመሆናችሁ እንዳትሳሳቱ እግዚአብሔርንም የሚያስቆጣ ነገር እንዳትሠሩና እንዳትርቁ በንጽሕት ድንግል ማርያም ስም እለምናችኋለሁ።

1. ማንኛውንም እምነትና የእምነት ተከታዮች እንዳትሳደቡ

2. ዝግጅታችሁ አጠቃላይ ከፖለቲካ ውጭ እንዲሆን

ስመክርስትና ማህደረ–ማርያም (ገነት)

● እኛም ዓላማችን ይህ አይደለም።

✣

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

በልዑል እግዚአብሔር ወንድም የሆናችሁ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች እንደምን ሰንብታችኋል?

በመጀመሪያ እትማችሁ ያወጣችኋቸውን መንፈሳዊ ጽሑፎች አንብቤ በጣም ረክቼባችኋለሁ። የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ ይባል የለ (በልማድ)። እናም እኔም እስቲ ከእኛ በፊት የነበሩ አባቶችና ነገሥታት ስለ ሃይማኖት የነበራቸውን ክብርና የሚያደርጉት ክርክር ለእኛ የሚያስተምረን ይሆናል በሚል «ከግራኝ አህመድ ወረራ» በተክለጻድቅ መኩሪያ ከተጻፈው የሃይማኖት ክርክር በአጭሩ ልኬላችኋለሁ።

እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን

ምናሴ ሠይፉ

ከአዋሳ ደብረምሕረት ቅ.ገብርኤል ቤ/ክ

● ለአስተያየትዎና ለላኩልን መልእክት ምስጋናችንን እያቀረብን ወደፊትም የተለመደ ትብብርዎ አይለየን።

✣

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

እንደምን ከርማችኋል የሐመር መጽሔት አዘጋጆች? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሆን ዘንድ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ስም እናንተን ወጣት መምህራን ብርታቱን ትጋቱን በረከቱን ይስጣችሁ እላለሁ። የጀመራችሁት ሥራ ሁሉ በጣም የሚያረካ ነው አስደስቶኛል። በርቱ። የቤ/ክርስቲያን ፎቶዎች ስላሉኝ ልሰጣችሁ ፈቃደኛ ነኝ። ግን ያስፈልጋችሁ ይሆን?

የእናንተው ባህሬ አለማየሁ

ከአዲስ አበባ

● በጣም ያስፈልገናል፤ አስተዋይነት ምን እናደንቃለን።

✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ውድ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች

እንኳን ለመለከት መጽሔታችን እህት ለሆነችው ሐመር መጽሔት ልደት አደረሳችሁ። ተጠምተን የነበረውን የቤተክርስቲያን ታሪክና የወንጌል ቃል ልታረካን ወደእኛ በመምጣቷ ደስታችን ወሰን የለውም። በመጨረሻም እግዚአብሔር አምላካችን ጀማሪ ሳትሆኑ ፈጻሚ ያደርጋችሁ ዘንድ የዘወትር ጸሎቴ ነው።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

የአብ ጸጋ የወልድ ቸርነት የመንፈስ ቅዱስ ሕብረት ከእናንተ ጋር ይሁን አሜን

ተሾመ ግርማ

ከጂማ

● ዘወትር በጸሎትዎ አይርሱን

✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

እናንተ ሐመሮች የልባችንን ማን ነገራችሁ? ወይስ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ልጆች በመሆናችን እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነን ነው? ብቻ በአጭር ቃል በጣም ተደስቻለሁ። ልክ የሐመ ርን ትርጓሜ እንደተረዳሁ የኖህ ዘመን ትዝ አለኝ። ሐመር ማለት መርከብ አይደለም? እንግዲህ ወደ መርከቢቱ መግባት ነዋ! ጅምራችሁ ዕፁብ ድንቅ ነው። በሚገባን ቋንቋ ተከሽኖ ስለቀረበ ማንም ያለአስተርጓሚ መረዳት ይችላል። በርቱ የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለያችሁ አሜን።

ገነት ፍቃዱ

ከጊንጪ ሚካኤል

● አስተያየቱንና ምክሩን በአኰቴት ተቀብለናል። ጸሎትዎ አይለየን።

✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ለመጽሔቱ አዘጋጆች በሙሉ ሰላምና ጤናን እየተመኘሁላችሁ ይህችን «ሐመር» የተሰኘች መጽሔት ገና ከሽፋኗ ሳያት እንዴት መሰላችሁ ደስ ያለችኝ? ውስጧማ አይነሣ ከድንቅም ድንቅ የምትባል የተዋጣላት ናት። ገና ከጅምሩማ ይህንን ከመሰለች ለወደፊቱ እንጃ! በዚሁ ግፉበት! መጨረሻውን ያሳምርላችሁ።

እግዚአብሔር አምላክ ከእናንተ ጋር ይሁን

መቅደስ ደርብ

● ጀምረናል እንጂ ስላልፈጸምን እንዳሉት ፍጻሜውን ያሳምርልን ዘንድ በእጅዎ በመጻፍና ዘወትር በመጸለይ አብረውን ይሁኑ። ስለአስተያየቱ እግዚአብሔር ይስጥልን።

✣

ውድ የሐመር መጽሔት አዘጋጆች እግዚአብሔር አምላክ እንኳን ለዚህ አበቃን እያልኩ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንደምን ሰነበታችሁ እላለሁ። በማስከተልም ስለ ሐመር መጽሔት ያለችኝን አስተያየት እንድገልጽ በትህትና እጠይቃለሁ። መጽሔቷ እያዝናናች የእግዚአብሔርን ተአምር የምታስረዳ በመሆኗ እጅግ በጣም ወድጃታለሁ። ለወደፊቱም ያሰባችሁትን ሁሉ እግዚአብሔር ይፈጽምላችሁ። እኔም በበኩሌ ያለኝን መጠነኛ ዕውቀት ለወገኖቼ ለማካፈል ዝግጁ ነኝ።

እግዚአብሔር የዓለምን ሕዝብ ሁሉ ይባርክ አሜን

መምህር ተክለ ሃይማኖት አንተነህ

ከወረዳ 18 ቀበሌ 06 አ.አ

● መምህር እግዚአብሔር የቃልዎ ፈጻሚ እንዲያደርግዎ እኛም እንጸልያለን።

✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

ከሁሉ አስቀድሜ እኔ የምላችሁ ሠላም ጤና ይስጥልኝ እንደምን አላችሁ? ለሐመር መጽሔት እንኳን አበቃችሁ እያልኩኝ በዚሁ ለመቀጠል በርቱ፥ ጠንክሩ፥ ግፉበት እላለሁ። እኔም ባለሁበት ይጠቅማል የምለውን በመላክ ለመሳተፍ ዝግጁ ነኝ።

ወጣት ንግስት ውሃቤ

ጐጃም ደ/ማ

ጽርሐ ጽዮን አብማ ማርያም ሰ/ት ቤት አባል

● በቃልሽ መሠረት ለመጽሔታችን ይጠቅማል የምትይውን ከመላክ ወደ ኋላ እንዳትይ እግዚአብሔር ያበረታሽ ዘንድ ጸሎታችን ነው።

✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት በጻድቃን በሰማዕታት ተራዳኢነት እያመንኩና እየተማፀንኩ ይህቺን መልእክት ለሐመር መጽሔት አዘጋጆች ስልክ በጣም ተደስቻለሁ። በርቱ! እግዚአብሔር ይርዳችሁ! የአምላክ እናት ትምራችሁ! መላእክት ከክፉ ነገር ይጠብቋችሁ።

በፍቃድህ

ከጅማ ቶጪ ቅ/ኪ/ም ሰ/ት/ቤት

● አሜን። በፍቃድህ! እግዚአብሔር ብርታቱን ሰጥቶን ብዙ እንድንሠራ ጸሎትህ አይለየን።

✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የማኅበረ ቅዱሳን የሥነ ጽሑፍና መዝሙር ዝግጅት ክፍል እንደምን አላችሁ? ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣችው ሐመር መጽሔትን ለክርስቲያን አንባብያን በግሩም አቀራረብ ስላቀረባችሁ ተደስቻለሁ። ለወደፊትም እግዚአብሔር ይርዳችሁ እያልኩ የሥራችሁን ዋጋ ኃያሉ፥ ገናናው፥ ዘለዓለማዊው እግዚአብሔር ይክፈላችሁ እላለሁ።

መዘምር እንዳለ ይታፈሩ

ናዝሬት

● አሜን። እኛም ለአስተያየትዎ እግዚአብሔር ይስጥልን እንላለን።

✣

ከፍ ብሎ ከቀረቡት ሌላ!

ጥላሁን ለገሠ፥ ተክለኢየሱስ ወ/አምላክ፥ ዲ.ዘመንፈስ ክብረድንግልና ወ/ሮ ሃይማኖት ገድሌ ከአሰላ! ጥላዬ ሽታሁን፥ ሕይወት አንተነህና ከንፈ—ሩፋኤል ቸርነት ከአዲስ አበባ የላካችሁልን አስተያየትና ጥያቄዎች ደርሰውናል። ለአስተያየታችሁና ለመንፈሳዊ ምክራችሁ እግዚአብሔር ውለታውን ይክፈላችሁ ስንል ለወደፊትም በዚሁ እንደምትቀጥሉ እምነታችን ጽኑዕ ነው። ለጥያቄዎቻችሁ ግን በሚቀጥለው እትማችን በቂ መልስ ለመስጠት የምንሞክር መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን። ✣



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# ትምህርተ– ሃይማኖት

በብርሃኑ ጎበና

ይህ ዓምድ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማና ቀኖና) የምንማርበት ይሆናል።

በዚህ ዓምድ ሥር ባለፈው እትማችን ስለ እግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት መጻፍ መጀመራችን ይታወሳል። ዛሬም ካለፈው የቀጠለውን ትምህርተ ሃይማኖት እንደሚከተለው አቅርበናል።

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት የተገለጸ ቢሆንም እንደ ሐዲስ ኪዳን በግልጽ አልተረዳም ነበር። እግዚአብሔር ሦስትነቱን በብሉይ ኪዳን ግልጽ ያላደረገበትን ምክንያት አበው ሊቃውንት ሲተነትኑ እሥራኤላውያን ብዙ ጊዜ የአሕዛብን አማልክት (ጣዖታት) በማምለክ እግዚአብሔርን ያስቀኑት ነበር። እነርሱም እንደ አሕዛብ ብዙ አማልክት እንዲኖሩአቸው ፍላጎት ስለነበራቸው «በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ» እንዲሉ በዚህ ዓይነት መወላወል ላይ ላሉት እሥራኤላውያን ሦስትነቱን ቢገልጽላቸው ኖሮ እነርሱም እንደ አሕዛብ ብዙ አማልክት አሉን ብለው በመለኮት በባህርይ አንድ የሆነውን አምላክ ሦስት አድርገው እኔ የአብ ነኝ፥ እኔ የወልድ ነኝ፥ እኔ ደግሞ የማምነው በመንፈስ ቅዱስ ነው ወደሚል ከንቱ አምልኮ እንዳይገቡ ጊዜው እስኪደርስ ማለትም ባለቤቱ ራሱ በሥጋ ተገልጦ ሦስትነቱን በተረዳና ጉልህ በሆነ ሁኔታ እስኪገልጸው ድረስ ተሰውሮ ነበር።

ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ንጽሕት ቅድስት ከምትሆን ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ተወልዶ ልዩ ሦስትነቱን ገሐድ አደረገው። ስለዚህ ነገር የመጽሐፍ ቅዱስን ምስክርነት ወደ መመርመር እንግባ።

ማቴ.3፥16–17፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕረ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ ከወጣ በኋላ እነሆ ሰማያት ተከፈቱ ይላል። እዚህ ላይ ለሰማይ መስኮት ኖሮት የሚከፈት የሚዘጋ ሆኖ አይደለም። ነገር ግን ደጅ በተከፈተ ጊዜ በቤት ውስጥ ያለው ሁሉ እንደሚታይ እንዲሁም እስከዛሬ ገሐድ ያልነበረው የእግዚአብሔር ልዩ ሦስትነት ታወቀ፤ ተረዳ ማለት ሲሆን እንዲሁም የአምላኩን ገጽታ አጥቶ ጣዖትን ያመልክ የነበረው የሰው ልጅ የአምላኩን ፊት አየ፤ አምላኩን ዐወቀ፤ በአንድነትና በሦስትነት የሚሰለስ የሚቀደስ መሆኑን ተገነዘበ ማለት ነው። ከዚህ ላይ አንዱ አካል አብ በደመና ሆኖ የምወደው የምወልደው ልጄ ይህ ነው እርሱ የሚላችሁን ስሙት በማለት አባት መሆኑን በተለየ አካሉ «አብ» እንደሚባል ገለጸልን። መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል የጌታችንን ራስ ቆንጠጥ አድርጎ (በራሱ ላይ በማረፉ) በተለየ አካሉ ታይቷል። ሦስተኛው አካል አካላዊ ቃልም ሥጋን ተዋሕዶ በዮርዳኖስ ባሕር ተጠምቋል።

## ሦስትነት በአንድነት

እንግዲህ ሰባልዮሳውያን እንደሚሉት እግዚአብሔር አንድ ገጽ ነው በተለያዩ ዘመናት ራሱን በተለያየ መልክ ለውጦ መጣ ማለት የሐሰት ትምህርት መሆኑንና እግዚአብሔር በአካል፥ በግብር፥ በስም ሦስት መሆኑን ያስረዳበት ትምህርተ ሥላሴ የተገለጠበት የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ከፍ ብለን ያየነው መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

ማቴ. 22፥44፤ «...ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።» በዚህ ጥቅስ ላይ ሁለት ጌታ ተጠቅሷል። ዳዊት አስቀድሞ የእግዚአብሔር ሦስትነት ወይም ሥላሴ የተገለጸለት ስለነበር ጌታዬ አብ ጌታዬ ወልድን በቀኜ ማለት (በዕሪናዬ) ኑር አለው እንደምን አለ? ብሎ አብ የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ያለው፤ ወልድም የራሱ የሆነ ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ያለው መሆኑን አስረድቷል። መንፈስ ቅዱስም ሕልው ሆኖ መኖሩ የታወቀ ነው።

ማቴ.28፥19፤ «...በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ» ማለቱ እግዚአብሔር በስም ሦስት መሆኑን ሲገልጽ ነው። አብ ሲል ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ያለውን የወልድ አባት ማለቱ ነው። ወልድ ሲልም ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ያለውን ከአብ አካል ዘእምአካል ባህርይ ዘእምባህርይ የተወለደውን ወልድ ማለቱ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሲል ፍጹም ገጽ ፍጹም መልክዕ ያለውን አብን አህሎ አብን መስሎ ከአብ የወጣውን መንፈስ ቅዱስን መጥራቱ ነው።

ሉቃ.1፥35፤ «መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል የልዑል ኃይልም



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ነው።» እንዳለው ሥላሴ በእመቤታችን ተገልጸዋል። አብ ለማጽናት፥ መንፈስ ቅዱስ ለማንጻት ወልድ በተለየ አካሉ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ለመዋሐድ ለመወለድ።

<u>ዮሐ.14፥15–17</u>፤ «ከወደዳችሁኝስ ትእዛዜን ጠብቁ ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር የሚኖር ጰራቅሊጦስን አብ ይልክላችኋል።» እንግዲህ አንድ ገጽ ባዮች ይህን በምን ሊያስተባብሉት ይችሉ ይሆን? አንዱ ገጽ እንዴት ብሎ እንዲህ ዓይነቱን የሦስት አካላት ግብርና ኩነት (አኳኋን) ሊናገር ይችላል?

<u>ዮሐ.15፥26</u>፤ «ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል።» እኔ በማለቱ የራሱን በአካል ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ መለየት ሲናገር ከአብ በማለቱ የአብን በአካል ልዩ መሆን ገልጾአል፤ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስም አካል የሌለው ዝርው ኃይል (IMPERSONAL POWER) አለመሆኑንና አካል ያለው (PERSONAL) መሆኑን ሲገልጽ እርሱም ብሎታል። እርሱም የሚባለው ሕይወት ያለው እኔ ባይ አካል እንጂ ዝርው ኃይል አይደለም። እውነተኛ የባህርይ አምላክነቱንም ሲገልጽ የእውነት መንፈስ አለው። በተጨማሪም አካላዊ መሆኑን ሲያረጋግጥ «እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» በማለት ፍጹም ገጽ፥ ፍጹም መልክዕ ያለው አካላዊ መንፈስ መሆኑን በግልጽ አስረድቶናል።

<u>ዮሐ.1፥1–2</u>፤ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ» ብሎ አካላዊ ቃልን፤ «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» ብሎ ያ ቃል በእግዚአብሔር አብ ህልው መሆኑን ገልጦ አብን በተለየ አካሉ ጠርቶታል፤ «ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር» ብሎ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ያነሣል።

<u>ዮሐ.7፥55</u>፤ ቅዱስ እስጢፋኖስ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ቆሞ እንዳየው ተናግሯል። እንግዲህ ከቅዱስ እስጢፋኖስ አነጋገር የተረዳነው አብና ወልድ በአካል ልዩ መሆናቸውን ሲሆን መንፈስ ቅዱስም በእርሱ አድሮ ምስጢርን በመግለጡ ታውቋል።

<u>2ቆሮ.13፥14</u>፤ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የእግዚአብሔርም ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስም አንድነት ከሁላችን ጋር ይኹን።» በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የሥላሴን ነገር በመግለጥ አስተምሯል።

<u>ራእ.14፥1–2</u>፤ «አየሁም እነሆም በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር፥ ከእርሱም ጋር ስሙና የአባቱ ስም የመንፈስ ቅዱስም ስም በግምባራቸው የተጻፈባቸው...» በጉ ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፥ የአባቱ ስም ብሎ አብን፥ የመንፈስ ቅዱስም ስም ብሎ መንፈስ ቅዱስን መጥራቱ የሥላሴ (የሦስትነት) ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በሐዲስ ኪዳን በግልጽ መጻፉንና መነገሩን የሚያስገነዝብ በመሆኑ እንዲሁ በደረቁ በጥራዝ ነጠቅ ጥቅሶችን ይዞ የእግዚአብሔርን ሦስትነት ከመጻረር መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄና በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት መመርመር ያስፈልጋል።

## የእግዚአብሔር ሦስትነት እንዴት ነው?

እግዚአብሔር በስም፥ በአካል፥ በግብር፥ በኩነት ሦስት ነው።

<u>የስም ሦስትነት</u>፤ ሥላሴ በስም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። አብ ማለት አባት ማለት ሲሆን የማን አባት ቢባል የወልድ፤ ወልድ ማለትም ልጅ ማለት ሲሆን ልጅነቱም የአብ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ማለት ሠራፂ (የወጣ) ማለት ሲሆን ከማን የወጣ ቢባል ከአብ ነው። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የአካላት ስም መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

<u>የአካላት ሦስትነት</u>፤ መጠቅለልና መቀላቀል ሳይኖርባቸው በተከፍሎ በተፈልጦ በፍጹም ገጽ በፍጹም መልክዕ በየራሳቸው ህልው የሆኑ ሲሆኑ፤ ኩነታት ተከፍሎ ተፈልጦ ሳይኖርባቸው በተዋሕዶ፥ በተጋብኦ በአንድነት አካላትን በህልውና እያገናዘቡ በአንድ መለኮት የነበሩ፥ ያሉ፥ የሚኖሩ ናቸው። እነዚህም ከዊነ ልብ፥ ከዊነ ቃል፥ ከዊነ ሕይወት (እስትንፋስ) ናቸው። ከዊነ ልብ በአብ መሰረትነት ለራሱ ለባዊ ሆኖ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ዕውቀት መሆን ነው። ከዊነ ቃል በአብ መሠረትነት ለራሱ ነባቢ (ተናጋሪ) ሆኖ ለአብ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ንባብ መሆን ነው። ከዊነ እስትንፋስ ለራሱ ሕያው ሆኖ ለአብ ለወልድ ሕይወት መሆን ነው። (ከዊን ማለትም ሁኔታ ማለት ነው።)

<u>የእግዚአብሔር አንድነት</u>፤ እግዚአብሔር በባህርይ በህልውና በመለኮት አንድ ነው። ለዚህም፥ «እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ» ዘፍ.1፥1፤ «እሥራኤል ሆይ ስማ እግዚአብሔር አምላክህ አንድ ነው» ዘዳግ.6፥4፤ «የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች በእግዚአብሔርም ቃል ሰማያት ጸኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ።» መዝ.32፥6፤ «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ...ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር» ዮሐ.1፥1–2፤ «እኔና አብ አንድ ነን» ዮሐ.10፥30፤ «እኔን ያየ አብን አየ...እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ» ዮሐ.14፥8–11።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# ልሳን

ከአባ ወ/ትንሣኤ አያልነህ

በዚህ ጽሑፍ መሠረት ልሳን ማለት ቋንቋ ማለት ነው የሐዋ.2፥4። በልሳን መናገር ማለት የሰው ልጆች በሚሰሙትና በሚናገሩት ቋንቋ መናገር ማለት ነው። እንዲሁም በአዲስ ልሳን መናገር ማለት በአዲስ ቋንቋ መናገር ማለት ነው። ማር.16፥17። በአዲስ ቋንቋ መናገር ማለትም ተወልደው ባላደጉበት፥ ወጥተው ወርደው ባልተማሩት ቋንቋ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት መናገር ማለት ነው።

ልሳን ቁጥር ስፍር ከሌላቸው መንፈስ ቅዱስ ከፍሎ ለክርስቲያኖች ከሚሰጣቸው ስጦታዎች አንዱ ነው። 1ቆሮ.12፥10።

የልሳን ጸጋ በሐዲስ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠው ለሐዋርያት ነው። ዕለቱም መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት በወረደበት በጰንጠቆስጤ (በሃምሳኛው) ቀን (በበዓለ ኀምሳ) ነው። የሐዋ.2፥1።

ከፍ ብሎ የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች በአንክሮ መመልከት የእግዚአብሔርን የባህርይ አንድነት ያረጋግጥልናል።

ከላይ እንደተገለጸው የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት በኀላ በተረዳ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ መሆኑን አስረድተናል። በተጨማሪ ዮሐንስ ሐዋርያው በመጀመሪያ መልእክቱ ላይ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት ግልጽ በሆነና በማያከራክር ሁኔታ የገለጸው ስለሆነ ይኼን አማናዊ ማስረጃ በተለያየ ቋንቋ ከተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍት እናቀርባለን።

## በጽርዕ (በግሪክ) ቋንቋ የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ

" Οτι τρεις εισιν οι μαρτυρουντες εν τω ουρανω, ο Πατηρ, ο Λογος και το Αγιον Πνευμα, και ουτοι οι εν εισι."

ΙΩΑΝΝΟΥ Α' κεφ. 5 : 7

## በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈው የኪንግ ጀምስ ቨርሽን (King James Version)

"For there are three that bear record in heaven; The Father, The Word, and The Holy Ghost, and these three are one"

I John chap. 5 No. 7

## በ1886 ዓ.ም. የታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ።

«በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስት ናቸው። እነርሱም አብ፥ ልጅም መንፈስ ቅዱስም ናቸው። እነዚህ ሦስቱም አንድ ናቸው» 1ዮሐ.5፥7።

እነዚህ ማስረጃዎች የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚያስረዱን ሲሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከሚታተሙት «አዲስ ትርጉም» የተሰኙ ቅዱሳት መጻሕፍት ለምን ተቀንሰው እንደቀሩ ስናስተውል በእጅጉ አስደንቆናል። የእግዚአብ ሔርን አንድነትና ሦስትነት ትምህርት ከምእመናን ለመሰወር ይሆን? እግዚአብሔር ይወቀው!

### ማጠቃለያ

አንባብያን ሆይ አምላካችን እግዚአብሔር የአንድነትና የሦስትነት ባለቤት ስለሆነ እኛም ዛሬ በኋለኞቹ ዘመናት የሐሰት ትምህርት የሚያስተምሩ ይመጣሉ ተብሎ በወንጌል ስለተነገረን የእግዚአብሔርን ሦስትነት እነርሱ ክደው እኛንም ለማስካድ ከሚሯሯጡና ይህ ምሥጢር ካልገባቸው ሰዎችና የሐሰት መምህራን ራሳችንን ጠብቀን በሃይማኖታችን ልንጸና ይገባናል። እንዲህም በማለት፤ «በስመ እግዚአብሔር ዋሕድ በመለኮት፤ በስም፥ በአካላት፥ በግብርና በኩነታት ሦስት በሚሆን በእግዚአብሔር እናምናለን።» አሜን። ✥

በዋናስ አሳታሚ ድርጅት «መለከት» በሚል ስያሜ በየወሩ እየታተመች የምትወጣውን ኦርቶዶክሳዊት መጽሔት ገዝተው አንብበዋል?

እንዲያነቡ እንመክርዎ! መለከት በውስጧ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ብዛት፥ አማላጅነት በአጸደ ሥጋና በአጸደ ነፍስ፥ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር፥ እንዲሁም ሌሎች መልእክቶችን አካታ ይዛለች።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

የመጀመሪያውንና እውነተኛውን ልሳን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:-

«በሁሉም (በሐዋርያት) መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስ ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።

ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር፤ ይህም ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ፥ እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር የሚሉትን አጡ። ተገርመውም ተደንቀውም እንዲህ አሉ:- እነሆ እነዚህ ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን?

የጳርቴና የሜድ፥ የኢላሜጤም ሰዎች፥ በሁለት ወንዝም መካከል በይሁዳም በቀጰዶቅያም በጳንጦስም በእስያም፥ በፍርግያም በጵንፍልያም በግብፅም በቀሬናም በኩል ባሉት በሊቢያ ወረዳዎች የምንኖር፥ በሮሜም የምንቀመጥ፥ አይሁድም ወደ ይሁዲነትም የገባን የቀርጤስና የዓረብ ሰዎች፥ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን። ሁሉም ተገረሙና አመንትተው እርስ በእርሳቸው እንጃ ይህ ምን ይሆን? አሉ። ሌሎች ግን እያፌዙባቸው ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አሉ።

ነገር ግን ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመ፥ ድምፁንም ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥ እናንተ የይሁዳ ሰዎች በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፥ ቃሌንም አድምጡ። ለእናንተ እንደመሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም፥ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዮኤል የተባለው ነው።

«እግዚአብሔር ይላል፥ በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፥ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ...የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል።» ዮሐ.2፥1–21።

እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ ተምልቶ በሌላ ልሳን መናገር ማለት በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት የሰው ልጆች በሚሰሙትና በሚናገሩበት ልዩ ልዩ ቋንቋ መናገር ማለት እንደሆነ በዚሁ ምዕራፍ በግልጥ ተረድተናል።

በመንፈስ ቅዱስ ተምልቶ ልዩ ልዩ ቋንቋ መናገር የዕብራይስጥ ቋንቋ ብቻ ለሚያውቁ፥ ለአይሁድ ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሰክሮ እንደመለፍለፍ ነበር። መንፈስ ቅዱስ የማያውቁትን ቋንቋ እንደሐዋርያት አልገለጠላቸውምና።

በበዓለ ኀምሳ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ (ስጦታ) ሐዋርያት በልዩ ልዩ ልሳን (ቋንቋ) ወንጌልን በሰበኩ ጊዜ ግን አድማጮች ከዕብራይስጥ በቀር ሌላ ቋንቋ አይችሉም። ሆኖም ሐዋርያት በእያንዳንዳችን ቋንቋ ወንጌልን እንዴት ሊሰብኩ ቻሉ? በማለት ከመገረማቸውም በላይ ይህን ተአምር በማየት በአንድ ቀን 3000 (ሦስት ሺህ) ሰዎች ተጠምቀዋል። የሐዋ.2፥41። በመንፈስ ቅዱስ ተምልቶ በልሳን (የሰው ልጆች በሚሰሙት ቋንቋ) መናገር ለማያምኑት ይጠቅማል፥ ካመኑት ይልቅ ለማያምኑት እንደምልክት ሆኖ እንዲያምኑ ያደርጋልና 1ቆሮ.14፥22።

በልሳን (በአዲስ ቋንቋ) መናገር በሐዋርያት ብቻ የተወሰነ አልነበረም። በማርቆስ ወንጌል 16፥17 እንደምንረዳው ላመኑትና ለተጠመቁት ከሚሰጧቸው ጸጋዎች አንዱ በአዲስ ቋንቋ መናገር እንደመሆኑ መጠን አምነው ከሚጠመቁት ምእመናን ለአንዳንዶቹ ይሰጣቸው ነበር። ለዚህም የሚከተለውን እንመልከት።

«ይህንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ፥ ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ። ሰዎ ቹም ሁሉ አሥራ ሁለት ያህሉ ነበር» ይላል። የሐዋ.19፥5–7።

ቅዱስ ጳውሎስም፥ «በልሳኖች ከመናገር አትከልክሉ» ይላል። 1ቆሮ.14፥39። የልሳን ጸጋ ተሰጠኝ ተብሎ በጉባኤ መካከል ቁጥር ሥፍር በሌለው ቋንቋ መናገር እግዚአብሔር የማያውቀው ቋንቋ ስለሌለ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ሙሉ ግንኙነት ይኖረዋል እንጂ ለጉባዔው ሙሉ በሙሉ እንደማይጠቅም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል:-

«በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም የሚያስተውለው የለምና» 1ቆሮ 14፥2።

በልሳን (በልዩ ልዩ ቋንቋ) የመናገር ጸጋ የተሰጠው ሰው በጉባኤ መካከል በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገር ከሆነ በጉባዔው የተሰበሰቡት ሰዎች



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

በሚሰሙበት የወል ቋንቋ መተርጐም እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ያዛል። እንዲህ ሲል:-

«ስለዚህ በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ» 1ቆሮ 14፥13። በልሳን (በተለያዩ ቋንቋዎች) የመናገር ጸጋ ተሰጥቶት በጉባዔ የተሰበሰቡት ምእመናን ሁሉም እንዲሰሙ የጋራቸው ወደሆነው ቋንቋቸው የመተርጐም ጸጋ ካልተሰጠው ደግሞ በ1ቆሮ12፥10 ላይ እንደተገለጠው የመተርጐም ጸጋ የተሰጠው ሌላው ብዙኃኑ ወደሚሰሙት የወል ቋንቋ እንዲተረጉምለት መደረግ አለበት።

ይህም የግእዝን ቋንቋ እያወቅንና ግእዙን እያነበብን ቅኔ ባለማወቃችን ወይም የግእዝን ትርጉም ባለመረዳታችን ምክንያት ግእዙን ወደ አማርኛ የሚተረጉም ሌላ ትርጓሚ እንደሚያስፈልገን እንደ አንዳንድ ሰዎች ማለት ነው ግእዝን የምናነብ ሰዎች ሁላችንም በትክክል የመተርጐም ዕውቀት የለንምና።

በልሳን ወይም በልዩ ልዩ ቋንቋ መናገር በጉባኤ ከተሰበሰቡት ለብዙዎች ቢገለጥላቸው መናገር የሚገባቸው ግን ተራቸውን ጠብቀው ሁለት ቢበዛ ሦስት ሰዎች ብቻ መናገር እንደሚገባቸውና የመተርጐም ጸጋ የተሰጠውም እነርሱ የሚናገሩትን ልዩ ልዩ ቋንቋ ብዙኃኑ ወደሚሰሙበት የጋራ (የወል) ቋንቋ እንዲተረጉምላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ተነግሯል። 1ቆሮ.14፥27።

ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ ስለልሳን ብዙ ከተናገረ በኋላ በእውነት ላመኑ ክርስቲያኖች የልሳን ወይም የቋንቋ ጋጋታ ምንም እንደማይጠቅም እንዲህ ሲል ተናገረ:-

«እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም። ትንቢት (ማስተማር) ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም። እንግዲህ ማኅበር ሁሉ አብረው ቢሰበሰቡ ሁሉም በልሳኖች ቢናገሩና ያልተማሩ ወይም የማያምኑ ሰዎች ቢገቡ አብደዋል አይሉምን?

ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን የማያምን ወይም ያልተማረ ሰው ቢገባ በሁሉ ይወቀሳል፥ በሁሉም ይመረመራል፥ በልቡም የተሰወረ ይገለጣል፥ እንዲሁም እግዚአብሔር በእውነት በመካከላቸው ነው ብሎ እየተናገረ በፊቱ ወድቆ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል።» 1ቆሮ 14፥22-25።

በዚህ ምንባብ ውስጥ (ቁጥር 24) «ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን» የሚለው ሁሉም ወይም በጉባኤው የተገኙት ሰዎች በሙሉ በሚሰሙበት በጋራ ቋንቋቸው ወንጌል ቢያስተምሩ ማለት እንደሆነ መዘንጋት የለብንም። የወንጌሉ ትምህርት «ትንቢት» መባሉም ላላመኑት ብታምኑና ብትጠመቁ ትድናላችሁ፥ ላመኑት ደግሞ መድኀን ክርስቶስ ዳግም ይመጣል፥ የዘለዓለም ሕይወት መንግሥተ ሰማያትን እንወርሳለን። ስለዚህ ሁልጊዜ ዝግጁ ሆነን እንጠብቅ ተብሎ በትንቢት (በይሆናል) መልክ የሚሰበክ ስለሆነ ነው።

ስለ ልሳን የቅዱስ ጳውሎስን ምክር እንመልከት:-

«ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች (በቋንቋዎች) እናገራለሁና እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፥ ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ።» 1ቆሮ.14፥18-19።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እልፍ ቃላት በልሳን ከምናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ መናገርን እወዳለሁ ሲል ገና ጸጋው ተሰጠኝ ብዬ በጉባኤ የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉም በማይሰሙት በልዩ ልዩ ቋንቋ እየተናገርሁ ጊዜየን ከማባክን በአእምሮዬ (እኔ በማውቀውና ሌሎችም በሚያውቁት) በአንድ ቋንቋ አምስት ቃላት ብናገር በጉባኤ የተሰበሰቡት ይጠቀማሉ ማለት ነው። «በአእምሮዬ» ሲል በማውቀው፥ በዕውቀቴ፥ በሚያውቁት በዕውቀታቸው ለማለት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃው እንዲህ ይላል።

«ወንድሞች ሆይ በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ ለክፋት ነገር ሕፃናት ሁኑ እንጂ። በአእምሮ የበሰላችሁ ሁኑ» 1ቆሮ.14፥20።

በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ ሲል በዕውቀት እንደሕፃናት አትሁኑ ለማለት እንደሆነ ግልጥ ነው። ምክንያቱም ሕፃናት ምንም የሚያውቁት ነገር የለምና።

«በአእምሮ የበሰላችሁ ሁኑ» ሲልም በዕውቀት የበሰላችሁ ሁኑ ማለት ነው።

በሌላ በኩል አእምሮ ማለት ማስተዋል ይሆናል። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ እልፍ ቃላት ሰው በማያስተውለው (በማያውቀው) ቋንቋ ከምናገር ሰው በሚያስተውለው (በሚያውቀው) ቋንቋ አምስት ቃላት መናገር ይጠቅማል ሲል፥ በልሳን ከመናገር በአእምሮ መናገር ይጠቅማል ካለው ጋር አንድ ነው።

አንባብያን ሆይ! ስለልሳን በመጠኑም ቢሆን ተመልክተናል። ልሳን ማለት ቋንቋ ማለት እንደሆነና በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በሌላ ልሳን (በአዲስ ቋንቋ) መናገር ማለት ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት ተወልደው ባላደጉበት ተምረው ባላወቁት የሰው ልጆች የሚናገሩትን ቋንቋ ሁሉ ማወቅና መናገር ማለት እንደሆነ በሐዋ.2፥1-17 ተረድተናል። ነገር



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ግን ይህን የመሰለው እውነተኛውና መጽሐፍ ቅዱሳዊው የልሳን ጸጋ በዘመናችን አለ ለማለት የሚቻል ቢሆንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተጽፎ የምናገኘውን ይህንን ጸጋ ለመቀበል የተዘጋጀ ሕይወት ያለው ሰው እምብዛም ነው። ይህ ለምን ሆነ እንል ይሆናል። ለዚህ መልስ የተለያዩ ክፍሎች የየራሳቸውን አስተያየት ይሰጣሉ። ከእነዚህ መካከል ሁለቱን ግምቶች እንደሚከተለው አቅርበናል።

1.ሀ. «በዓለም ምናልባት ቁጥር የሌለው የቋንቋ ዓይነት ይኖራል። ቋንቋ የሌለው ሕዝብ የለም፤ እንግዲህ የቋንቋውን ፍች ባላውቅ ለሚናገረው እንግዳ እሆናለሁ፥ የሚናገረውም ለእኔ እንግዳ ይሆናል። 1ቆሮ.14፥10–11።

ለ. «እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም» ይላል። 1ቆሮ.14፥22። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት በጉባዔ ቆሞ በዓለም ያሉ ሕዝብ ሁሉ በሚናገሩባቸው ቁጥር ሥፍር በሌላቸው ቋንቋዎች መናገር ጊዜን ማባከን እንጂ ማኅበሩን አያንጽም። ምክንያቱም ማኅበሩ የሚታነጸው በጉባኤ የተሰበሰቡት ሁሉም በሚሰሙት በወልቋንቋቸው ወንጌል ቢሰበክ ነውና። ደግሞም ቅዱስ ጳውሎስ የልሳን (የቋንቋ) ብዛት ለማያምኑ ምልክት እንጂ ለሚያምኑ አያስፈልግም ስላለ በዚህ ምክንያት ይሆናል የሚል መልስ አለ።

2. መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ የልሳን ጸጋውን ያፈሰሰው አንድ ልብ በሆነች መለያየት በሌለባት ቤተክርስቲያን ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃውም እንዲህ ይላል። «በዓለ ሃምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሞላው። እየተጎረደ እንደሚሄድ እሳት የተከፋፈሉ የእሳት ላንቃዎች ታዩአቸው፥ በእያንዳንዳቸውም ላይ አደረባቸው። ሁሉም ኃይል የሚሆናቸውን መንፈስ ተሞሉ፤ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች (ቋንቋዎች) ይናገሩ ጀመር። ...እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር የሚሉትን አጡ፥ ተገርመውም ተደንቀውም እንዲህ አሉ፥

እነሆ እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን?» ይላል የሐዋ.2፥1–9።

መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው። ጸጋው (ስጦታው) ግን ብዙ ነው። 1ቆሮ 12፥4። መንፈስ ቅዱስ ብዙ ከሆነው ጸጋው (ስጦታው) ውስጥ አንዱ የልሳን ጸጋ ነው። ነገር ግን ይህን የልሳን ጸጋ ለመስጠት አንድ ልብ የሆኑ መለያየት፥ መነቃቀፍ፥ ክርክር በመካከላቸው የሌለ ክርስቲያኖችን ይፈልጋል። ሆኖም ግን መለያየት፥ መነቃቀፍ፥ ክርክር በዚህ ዘመን ጐልቶ ይታያል። በመለያየት መካከል ደግሞ የመንፈስ ጸጋ የለም።

ስለዚህ በዚህ ዘመን ምናልባት የልሳን ጸጋ የተቋረጠው በክርስቲያኖች አንድ ልብ አለመሆንና መለያየት ምክንያት ነው የሚል መልስ አለ።

በተረፈ ግን ልሳን በዚህ ዘመን የተቋረጠበትን ምክንያት የልሳን (ቋንቋ) ወይም የጸጋ ሁሉ ባለቤት ለሆነ ለልዑል እግዚአብሔር እንተዋለን። የእርሱን ምሥጢር ማንም አያውቅምና። 1ቆሮ.2፥11። በዘመናችንም በልሳን እንናገራለን የሚሉ አሉ። ለመሆኑ ይኸ አባባላቸው እውነት ይሆን? ✣

ይቀጥላል።

# ጠበል

በአባ ወልደትንሣኤ አያልነህ

ጸበል ማለት ቃሉ የግእዝ ሲሆን ፍቹም አፈር (አቧራ) ማለት ነው። ነገር ግን ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ጠበል ብለን የምንጠራው በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ሕሙማን የሚፈወሱበት ተአምራት የሚደረግበት ቅዱስ ውኃ ማለት ነው።

ጸበል ማለት በግእዙ አፈር (አብዋራ) ማለት ከሆነ ሕሙማን የሚፈወሱበት ተአምራት የሚደረግበት ቅዱስ ውኃ ለምን ጠበል ተባለ? የሚል ጠያቂ ቢኖር መልሱ በዮሐንስ ወንጌል 9፥6–8 የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉም እንዲህ ይላል፥ «በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ። ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ፤ በምራቁም ጭቃ አድርጐ በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀባና ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው። ስለዚህ ሄዶ ታጠበ፥ እያየም መጣ» ይላል። በዚህ ምንባብ ውስጥ እንደምንመለከተው አንድ ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ እውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ብርሃነ ዕውራን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን የተዋሐደ አምላክ ነውና አፈሩን በምራቁ ለውሶ የዕውሩን ዓይኖች ከቀባ በኋላ ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ ዓይንህ ይበራል ስላለው የተባለውን ፈጽሞ ዓይኑ በርቶለታል። ይህ ተአምር የተደረገው ሥጋን የተዋሐደ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምራቁ ለውሶ ጭቃ ባደረገው መሬትና በሰሊሆም መጠመቂያ ከሚገኘው ቅዱስ ውኃ ድብልቅ በመሆኑ ሕሙማን የሚፈወሱበት ቅዱስ ውኃ ጠበል ተብሎ ተጠርቷል።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

## ስለጠበል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች

1ኛ. ንእማን የተባለ ከፍተኛ የሶርያ ባለሥልጣን ነበር። ይህም ሰው ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ እንደበረዶ ነጭ በሆነ ለምፅ የነደደ ነበረ። ከሀገሯ ከእሥራኤል ወደ ሶርያ ተማርካ የሄደችና በዚህ በለምጽ በሽታ በተያዘው ባለሥልጣን ቤት የነበረች አንዷት እሥራኤላዊት ብላቴና በአገሬ በእሥራኤል ምድር ለምፅን የሚፈውሱ ነቢያት አሉ። ንእማን ቢሄድ ይድናል ብላ በተናገረችው መሠረት ለምጻሙ ንእማን ሠራዊት አስከትሎ ወደ እሥራኤል በመሄድ ከነቢዩ ከኤልሳዕ ጋር ተገናኝቶ ስለበሽታው ሲወያዩ ነቢዩ ኤልሳዕ ለንእማን ከለምፅህ የምትነጻው በዮርዳኖስ ውኃ 7(ሰባት) ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብለህ ታጥበህ ስትወጣ ነው አለው። ንእማንም ሰው በውኃ ከበሽታ እንዴት ይድናል? ብሎ በአሁኑ ዘመን እንደሚጠራጠሩት እንደ አንዳንድ ሰዎች የውኃ ውኃማ በአገሬ በደማስቆ የሚገኙት ወንዞች አባናና ፋርፋ ከእሥራኤል ወንዞች አይሻሉምን? በማለት በከፍተኛ ብስጭት ወደ አገሩ ሲመለስ የራሱ ተከታዮች የከበደ ነገር አልጠየቀህም አምነህ በውኃ ታጠብ ነው ያለህ ለምን አትታጠብም አሉት። የተከታዮችንም ቃል በመስማት ተመልሶ በእምነት በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብሎ ሲወጣ ከለምፁ ተፈውሷል። 2ነገሥ.5፥1–15። በተለይም ቁጥር አሥራ አራትን ይመልከቱ።

2ኛ. በኢየሩሳሌም ውስጥ ቤተ ሰይዳ የምትባል አንዷት መጠመቂያ እንደነበረችና በእርሷም ውስጥ ያለውን ውኃ የእግዚአብሔር መልአክ እየባረከው በዚህ ቅዱስ ውኃ በሽተኞች፥ እውሮች፥ አንካሶችም ሰውነታቸውም የሰለለ ሁሉ ይድኑ እንደነበረ እንረዳለን። ዮሐ.5፥2–5። በዚህ በተጠቀሰው ምዕራፍና ቁጥር ውስጥ 38 ዓመት ሙሉ በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ ተይዞ የኖረ አንድ በሽተኛ ሰው እንደነበረና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን ሰው በዚያው ቦታ አግኝቶት ልትድን ትወዳለህን? ብሎ በጠየቀው ጊዜ መልአኩ ውኃውን ሲባርከው ውኃ ውም ሲንቀሳቀስ ወደ ውኃው የሚያስገባኝ ዘመድ በማጣቴ እንጂ እኔማ እድን ዘንድ እወድ ነበር ብሎ ስለመለሰለት እንደ ኤልሳዕ በውኃ ታጠብ ሳይል በቃሉ ብቻ ተነሣ አልጋህንም ተሸከመህ ሂድ በማለት ፈውሶታል።

ይህንን መንሥኤ በማድረግ በሐዲስ ኪዳን በቃሉ ብቻ እንጂ ጠበል የተባለ ውኃ አያስፈልግም የሚሉ አሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ጠበሉ የሚያስገባው ዘመድ ያጣውን ይህን ሰው ወደ ውኃው በማስገባትና በውኃው በመፈወስ ፈንታ በቃሉ ብቻ የፈወሰው በሐዲስ ኪዳን ጠበል የተባለ ቅዱስ ውኃ አያስፈልግም ለማለት አይደለም። እኛ የሰው ልጆች በምንታመምበት ጊዜ ወደ ጠበል የሚወስደን ዘመድ ብናጣ ባለንበት አልጋ ላይ ሆነን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ማረን ብለን ብንጸልይ ምልዓተ መለኮቱ በሁሉም ቦታ የሚገኝ አምላክ በቃሉ ብቻ የሚፈውሰን መሆኑን ሊያረጋግጥልን ስለ ፈለገ ብቻ ነው። ይልቁንም የጠበሉ ባለቤት አምላካችን ራሱ በዚያ በመገኘቱና ለዚህ ሰው ወደጠበሉ መሄድ ስላላስፈለገው ነው።

3ኛ. በሐዲስ ኪዳን ጠበልን ባርኮ እንደሰጠን ተጨማሪ መረጃ «ሲያልፍም (አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ) ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው አየ። ደቀ መዛሙርቱም መምህር ሆይ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ? ብለው ጠየቁት። ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ። የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሰሩም። ብርሃን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል ማንም ሊሰራ የማይችልበት ሌሊት ትመጣለች። በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ፥ በምራቁም ጭቃ አድርጐ በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀባና ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው፤ ስለዚህ ሄዶ ታጠበ እያየም መጣ» ይላል ዮሐ.9፥1–8። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሁሉን ቻይ አምላክ መድኀኒ ዓለም ክርስቶስ ይህን ዓይን የሌለውን ሰው በሰሊሆም መጠመቂያ ታጥበህ ውጣ ዓይንህ ይበራል ብሎትና ሰውየውም እንደታዘዘው ተጠምቆ ዓይኑ የበራለት በቃሉ ብቻ ዓይኑን ማብራት አቅቶት ሳይሆን በብሉይ ኪዳን ሕሙማን ይፈወሱበት ተአምራት ይደረግበት የነበረው ቅዱስ ውኃ (ጠበል) በሐዲስ ኪዳንም የተባረከና ፈቅዶ የሰጠን ፀጋ መሆኑን ለማስረዳት ነው።

ይህ መረጃ በሚቀርብበት ጊዜ መልካም መቀበሉንስ እንቀበለው ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ.14፥14 ሁሉን ነገር በስሜ ለምኑ ይልና በተጨማሪም በሐዋ.4፥12 ላይ «ከሰማይ በታች ከምድር በላይ መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ሌላ የለም» ይላል። ስለዚህ ጠበሎች ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠራት ሲኖርባቸውና አዳኙም እርሱ ብቻ መሆን ሲገባው ለምን የድንግል ማርያም ጠበል፥ የሚካኤል፥ የገብር ኤል፥ የጊዮርጊስ፥ የገብረ መንፈስ ቅዱስ ወዘተ...ጠበል ተባለ? የሚሉ አሉ።

መልሱ አጭር ነው። ይኸውም በጠበሉ ቅዱሳኑ እንዲታሰቡለት



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ነው። በኢሳይያስ 56፥4–6። ባለው ምንባብ ውስጥ፥ «ደስ የሚያሰኘኝን ነገር ለመረጡ ቃል ኪዳኔንም ለጠበቁ ጃንደረቦች ከሴቶች ልጆችና ከወንዶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ በቤቴና በቅጥሬ መታሰቢያቸውን አደርጋለሁ። የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ» ባለው ቃል መሠረት ነው። እዚህ ላይ ጃንደረባ የሚለው ቃል በማቴዎስ 19፥12። ስለ መንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን ጃንደረቦች ያደረጉ አሉ። በማለት የዚህን ዓለም ፍትወቱን፥ ፍቅሩን ሁሉ ትተው መስቀሉን ተሸክመው በብቸኝነት ራሳቸውን ያሳለፉትን ቅዱሳኑን መሆኑን ያረጋግጣል። በተጨማሪም «የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ነው» ይላል መዝ.፥111፥7። መታሰቢያቸውም ለበረከት እንደሆነ ለማረጋገጥ «የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው» ይላል ምሳ.10፥7። በዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ መሠረት በጠበሉ ቅዱሳኑ መጠራታቸው መታሰቢያቸው እንዲሆን ነው። መታሰቢያነት ብቻም ሳይሆን በረከትነትም አለው ብለን እናምናለን እንጂ ጠበሉን የፈጠረው መድኀኒ ዓለም አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑና በጠበሉም አድሮ ሕሙማንን የሚፈውሰውና ተአምራትንም የሚያደርገው ሁሉን ቻይ የሆነው የአምላካችን የእግዚአብሔር ኃይል መሆኑ ጠፍቶን አይደለም። በጠበል ታጥበን እንድንፈወስ የሆነው በሚታዩ በሚጨበጡ ቅዱሳት ምልክቶች የማይታየውን የማይጨበጠውን አጋንንትን በማባረር፥ ሕሙማንን የመፈወስ ተአምራትን የማድረግ ረቂቅ ኃይሉን እንዲያስተላልፍባቸው ስለፈቀደ ነው። ለምሳሌ ያህል:-

1. የኤርትራ ባህር የመክፈል ኃይሉን በሙሴ በትር ዘጸ.14፥15–17።

2. ሙት የማስነሳት ኃይሉን በዐፅመ ኤልሳዕ.2ነገ.13፥20።

3. ደዌያትን የመፈወስ ኃይሉን በቅዱስ ዘይት ማር.6፥14፤ ያዕ.5፥14።

4. አጋንንትን የማባረር ኃይሉን ቅዱስ ጳውሎስ ለብሶት በነበረው ልብስ የሐዋ.19፥11።

እንዳስተላለፈ ሁሉ በዚህ ጠበል ተብሎ በተጠራው በቅዱሱ ውኃም እስከአሁን ድረስ ወደፊትም ሕሙማንን የመፈወስ ታአምራትን የማድረግ ረቂቅ ኃይሉን እያስተላለፈልን እየተፈወስን እንገኛለን።ወደፊትም እንፈወስበታለን። ለዚህ ምሳሌ የአዲስ አበባ ኪዳነ ምሕረትን፥ ተ/ሃይማኖትን፥ ገ/መንፈስ ቅዱስን፥ ዑራኤልን፥ የሚጣቅ አማኑኤልን፥ የለብታ ኢየሱስን ጠበል መጥቀስ በቂ ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው እግዚአብሔር ኃይሉን በገለጠባቸው ማደሪያዎቹ ባደረጋቸው የጠበል ቦታዎች ሰዎች ከደዌ ሥጋ ተፈውሰው ከሥቃይ አምልጠው በሰው ፊት እንደሰው ለመኖር በቅተዋል። ንዕማን የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ኤልሳዕ የነገረውን ሰምቶ በሃይማኖት ወደ ዮርዳኖስ ወረደ፤ ተጠመቀም፤ በሰዎች ፊት ያሳፍረው ከነበረው ሰዎች ከሚያዩት ለምጽ ነፃ ተፈወሰ፤ ቡራቡሬ የነበረው ሰውነቱ እንደሕፃን ልጅ ገላ ታደሰ፤ አዲስ ሰው ሆነ።

እንዲሁም ዛሬም የቤተክርስቲያንን አባቶችና አባታዊ ምክራቸውን፥ ትምህርታቸውን ሰምቶ እግዚአብሔር በሚያደርገው ድንቅ ተአምር ሳያንጐራጕሩ ማመን፥ ሳይጠራጠሩም እግዚአብሔር የኃይሉ መግለጫ ባደረገው ቅዱስ ጠበል በመጠመቅ አፍአዊ ከሆነ በሽታ መፈወስ ብቻ ሳይሆን መምህራን የሚነግሩንን አማናዊ ቃለ ሕይወት ሰምቶ ውሳጣዊ ከሆነና እግዚአብሔር ብቻ ከሚያየው የኃጢአት ለምጽና በሽታ መዳን ያስፈልጋል። ትውልዱ የእግዚአብሔርን ሥራ ማመን ሲቸግረውና፥ ለእግዚአብሔር የሚሆን ልቡና፥ እግዚአብሔርም ሥራውን የሚሰራበት የተቀደሰ ሕይወት ሲያጣ እግዚአብሔር ኃይል የሚያደርግባቸውን የድኅነት ምክንያቶች ሁሉ እየካደ ባለበት ዘመን የምንገኝና ክርስቲያኖችነን የምንል የዘመኑ ሰዎችም ከዚህ ርቀን ይልቁንም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፥ ማደሪያዎቹ መሆናችንን አምነን እግዚአብሔር በሕይወታችን፥ በንግግራችን እንዲያድር የኃጢአት ለምጽ፥ የቂምና የበቀል ለምጽ፥ የቅናትና የክፋት ለምጽ የሚያሰቃያቸውን ወገኖች ለማዳን ምክንያት ለመሆን እንዘጋጅ።

ይህ ብቻ አይደለም እንግዲህ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነ የእኛስ ሰውነት የቱን ያህል ተለውጦ ለሰዎች ሕይወት መዳን አብነት ሆኖ ይሆን? የንዕማንን በመሰለ አፍአዊ ለምጽ፥ የመጻጉዕን በመሰለ ሽባነት በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ዘጠኝ እንደተጠቀሰው ባለ የዓይን ዕውርነት ሳይሆን ውሳጣዊ ለምጽ የያዛቸውንና ሕይወታቸው ቡራቡሬ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም የሚያሳፍራቸውን፥ በኃጢአት በሽታ ሽባ ሆነው ወደ መዳኛይቱ አማናዊት ቤተሳይዳ (ቤተክርስቲያን) የሚወስዳቸው አጥተው ለዘመናት በዚህ ደዌ ኃጢአት የሚሰቃዩትን፥ በሥጋቸው የሚያዩ እየመሰላቸው በአእምሮአቸው የታወሩትን፥ በነፍሳቸው በጨለማ ሕይወት የሚመላለሱትን ዕውራን ልቡና በእግዚአብሔር ቃል የሚያንፃ፥ የሚፈውስና የሚያበራ ሕይወት ያለው ክርስቲያን ነው፥ በእርግጥ የእግዚአብሔር ሰው፥ እውነተኛ ክርስቲያን ሊባል የሚችለው።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

የብዙዎቻችን ሕይወት (ኑሮ)፥ ሥራችንና ንግግራችን ሰዎችን የኃጢአት ለምጽ የሚያስይዝ፥ ጤነኛውን በሽተኛ የሚያደርግ፥ ደዌ ነፍስ የሚያስይዝ፥ ልቡናው ብሩህ የሆነውን የሚያሳውርና ወደ ቤተክርስቲያን ከሚመልስ፥ ለሕይወት ከሚጠራ ይልቅ ከቤተክርስቲያን የሚያርቅ፥ ከሕይወት የሚያሸሽ በሆነና በመመሳለስ ብቻ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከዮርዳኖሱ ውኃ ከቤተሳይዳውና ከሰሊሆሙ መጠመቂያ እጅግ አንሰን እንታያለን።

እግዚአብሔር አክብሮ ማደሪያዎቹ አድርጐናልና ማንነታችንን ረስተን የእኛ በምንለው የአላዋቂዎች ጥበብ ከእግዚአብሔር የማዳን ኃይል እንዳንርቅ ከቸርነቱም እንዳንወጣ በሥራው ላይ ከማመጽ ይልቅ በንስሐ ራሳችንን ብናርም፥ ሕይወታችንን ብንለውጥ፥ ልቡናችንን ብናድስ መልካም መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል። ሮሜ.12፥2። ስለዚህ ካስነወረን የኃጢአት ለምጽ፥ ሽባ ካደረገን ከኃጢአት ደዌ፥ ምሥጢርን ሰውሮ ማስተዋልን አጥፍቶብን በልቡናችን ዕውር ካደረገን የትዕቢት በሽታ የሚያነጻውን የንስሐ ሕይወት ገንዘብ አድርገን በማየገቦው ታጥበን በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ ታትመን ዘላቂ ለሆነ ሕይወት መንግስተ ሰማያት እንድንበቃ እግዚአብሔር በቸርነቱ ወላዲተ አምላክ በረድኤቷ መላእክት በጥበቃ ቅዱሳን በአማላጅነታቸው ከሁላችን ጋር ይሁኑ። ✣

ወይትባረክ እግዚአብሔር

# እመ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ

አሪት ዘፍጥረት 4፥2–8።

ከዲ. ተክለጻድቅ

አምላካችን እግዚአብሔር በባህርዩ ንጹሕ በመሆኑ ንጹሕ የሆነ ነገር እንዲቀርብለት ፈቃዱ ነው። በንጽሕና በሚቀርብለት ነገር ሁሉ ይደሰታል። ስለዚህም ነው ዘወትር «ንጹሕ ልብን ፍጠርልን» በማለት ወደ እርሱ ልመና የሚቀርበው። ስለዚህ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው መሥዋዕት ንጹሕ ሊሆን ይገባል። ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የምናነበው ቃልም የሚያስተምረን ይህንኑ ነው። ታሪኩ በሁለት ወንድማማቾች በአቤልና በቃየል ሕይወት ላይ የተመሠረተ ነው።

ቃየል የአቤል ታላቅ ወንድም እንደ መሆኑ በአስተሳሰብና በአመለካከት ከታናሽ ወንድሙ ከአቤል ይልቅ መሻል ይገባው እንደነበር ለራሱ መልካምና የበለጠውን ነገር ለማድረግ እንደሚወድ መገመት አይቸግረንም። በዚያ የሕገ ልቡና ዘመን ገና መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ማቅረብ ሳይለመድ እነዚህ ወንድማማች ወጣቶች ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንደአቀረቡ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። በዚሁ መሠረትም ቃየል ገበሬ እንደመሆኑ ከአመረተው እህል ግርዱን፤ ለራሱ እንኳን የማይጠቀምበትን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ። የልብን ሀሳብ መርምሮ የሚያውቀው እግዚ አብሔር አምላክ ማእምረኩሉ ነውና የልቡን ክፋት ተመልክቶ ቃየልን መሥዋዕቱንም ናቀ፤ አልተቀበለውም።

አቤል ግን የበጎች እረኛ እንደ መሆኑ ከሚጠብቃቸው በጎች መካከል ፀጉሩ ያላረረውን ቀንዱ ያልከረከረውን የሰባውን ጠቦት ከበኩራቱ መካከል መርጦ በፍፁም የዋህነት ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ። የዋህነቱን የተመለከተው እግዚአብሔር ወደ አቤልና ወደ መስዋዕቱ ተመለከተ፤ ተቀበለውም። እንዲሁ ሁሉ ምንጊዜም ቢሆን አምላካችን በየዋህነት የሚያቀርቡለትን ማንኛውንም ተገቢ መስዋዕት የሚቀበል መሆኑ የታመነ ነው። አቤል እንዲመረጥ፥ እግዚአብሔርም እንዲመለከተው መሥዋዕቱንም እንዲቀበልለት ምክንያት የሆነው «እግዚአብሔርን የማስደስተው ይህን የመሰለ መስዋዕት ባቀርብ ነው» ብሎ ያሰበበት ቅንነቱ፥ የዋህነቱና የልቡ ንጽሕና ነው። ፈጣሪያችንም የተመለከተው የአቤልን ንጽሕና ነው። ንጹሐንን መመልከት የአምላካችን ባህርዩ ነውና።

አባቶቻችን ወላዲተ አምላክን ቅድስት ድንግል ማርያምን በዚህ የአቤል የዋህነት ወይም ደግነት በንጽህናው ይመስሏታል (የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ተመልከት።) «እርሷ እመቤታችን በንጽሕናዋ ከንጹሐን ሁሉ የምትበልጥ በመሆንዋ እግዚአብሔር ወደ እርሷ ተመለከተ፥ መረጣትም። የአቤል መመረጥም እግዚአብሔር ባየው ንጽሕናውና ደግነቱ ነውና በዚህ አቤልን ትመስለዋለች» ይላሉ። አባቶቻችን በሐተታቸው አቤል ከየዋህነቱና ከልቡ ንጽህና የተነሳ የበደልና የኃጢያት ሃሳብ ከቶውኑ በእርሱ ዘንድ ባለመኖሩ እግዚአብሔር እንደወደደው ከቃየል ይልቅም እንደመረጠው እመቤታችንም ፍጹም በሆነ ንጽሕናዋና ቅድስናዋ ከፍጥረት ሁሉ የበለጠች በመሆኗ ለሥላሴ ማደሪያነት፤ ለእመ አምላክነት ተመርጣለች። የአቤል ንጽሕና ከእመቤታችን ንጽሕና ጋራ ይወዳደራል ብለው ሳይሆን ዓለም ሁሉ የሚድንበትን የዓለም መድኃኒት ጌታችንን ለወለደች ለእመቤታችን ንጽሕና ምሳሌ በመሆኑ እግዚአብሔርም አስቀድሞ በምሳሌ የገለጣት መሆኑን ለማስረዳት ነው። እርሷም ንጽሕተ ንጹሐን ቅድስተ ቅዱሳን መሆኗ የታወቀ ነው።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

አቤል የዋህነቱ በዘመን መጨረሻ የሚገኘውን ክብር አገኛለሁ ብሎ ነውና በአመፀኛው ወንድሙ በቃየል ቢገደልም በሥጋ ከመሞቱ በስተቀር በእግዚአብሔር ዘንድ በነፍሱ ሕያው መሆኑ የታወቀ ነው። ንጽሕት ከሆነች ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተነሳ በሆነው የመዳን ምሥጢር የእግዚአብሔርን ሰው መሆን አምኖ ዓለሙ ሁሉ ሕያው እንዲሆን ለሕይወት ተጠርቷል።

ሰው በእግዚአብሔር ፊት የሚመላለስ መሆኑን እያሰበ ንጹሐ ባህርይ የሆነ አምላኩን በሚገባው መንገድ መቅረብ ይገባዋል። እግዚአብሔር አይዘበትበትም፤ እርሱ አይታለልም። እግዚአብሔርን ለመደለል የሚሞክሩና የሚያስቡ ሁሉ ራሳቸውን በማታለልና በገዛ ራሳቸው ፈቃድ በመጓዛቸውም ያለ ዋጋ ይቀራሉ፤ የእግዚአብሔርም ዓይኖች ከእነርሱ ይመለሳሉ፤ አይመለከቷቸውም። ቀደም ብሎ የተመለከትነው የቃየል ሕይወት የዚህ ዕድል ፈንታ ተቋዳሽ ነው። ለፈጣሪው የማይገባ ስጦታን በማቅረቡ እግዚአብሔር ወደ እርሱ ወደ መሥዋዕቱም አልተመለከተም።

ስጦታን ሁሉ ይዞ ወደ እግዚአብሔር ከመቅረብ አስቀድሞ ወደ እርሱ ፊት ሊቀርቡ በሚገባቸውና ሊቀርቡ በማይገባቸው ስጦታዎች መካከል ምርጫ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህንን በሕገ ልቡና ጠንቅቆ በመረዳት ንጹሕ ልቡናን፥ ፍጹም የዋህነቱን ከተመረጠው ንጹሕ መስዋዕት ጋር ለእግዚአብሔር ያቀረበውና ፈጣሪውን ያስደሰተው የአቤል ሕይወት የሚያስተምረን ይህን ነው።

እኛም እያንዳንዳችን ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ቤት (ቤተክርስቲያን) እንሄዳለን። ነገር ግን ለእግዚአብሔር ስለምናቀርበው ስጦታ አስበን እናውቅ ይሆን? አስበን ከሆነ ደግሞ ምን ልንሰጠው አቅደናል? እስከ ዛሬ ባለው ሕይወታችንስ ምንድነው ለእግዚአብሔር የሰጠነው ስጦታ? በእርግጥ እኛ ኢትዮጵያውያን ወደ ቤተ ክርስቲያን መባዕ ይዞ መሄድ እንግዳችን አይደለም። ችግሩ የምናደርገው ነገር ምን ያህል በሕይወታችን ውስጥ ትርጉም ተሰጥቶታል የሚለው ጥያቄ ሲነሳ በምንሰጠው መልስ ይታወቃል። በእጃችን የያዝነውን ከቤተ ክርስቲያን ወስደን አስቀምጠን መምጣቱ አይደለም እግዚአብሔር እንዲመለከተን የሰጠነውንም እንዲቀበል የሚያደርገው። በልቡናችን ውስጥ ያለው ለውጥና በተለይም በእግዚአብሔር ፊት በፍጹም የዋህነትና በንጹህ ሕሊና መቅረባችን ነው እንጂ። ከዚህ አንፃር እንግዲህ የየራሳችንን ሕይወት ልንመረምር ያስፈልጋል። የድንግል ማርያምን ንጽሕና የመረጠ የእኛንም የልቡና ንጽሕና ተመልክቶ ለቃሉ ማደሪያ እንዲያደርገን ማንነታችንን ማደስና ለሕይወት መቅረብ ይኖርብናል።

ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ ለእግዚአብሔር ዓይኖች ሊታይ በሚችል እንደ አቤል ባለ ንጽሕና ሊሆን ይገባል። እንዲሁ ሁሉ በፊቱ የምናቀርበውም መስዋዕት ከሁሉ የሚበልጠው ንጹሕ ልቡናችን እንዲሆን ያስፈልጋል። ያን ጊዜ እግዚአብሔር አስቀድሞ አቤልንና መስዋዕቱን እንደ ተመለከተና እንደ መረጠ በኋላም የወላዲተ አምላክን ንጽሕናና ቅድስና አይቶ ማደሪያው ትሆን ዘንድ እንደወደደ የእኛንም መስዋዕት በፊቱም መቆማችንን እንዲወድና እንዲቀበለው ፈቃዱ ይሆናል።

ይሁን እንጂ ዓለም ዛሬ ለእግዚአብሔር የምታቀርበው ንጹሕ የሆነ ስጦታን አይደለም። አምልኮቷ የተበረዘ፥ ሃሳቧ የተጣመመ፥ መንገዱ የተሳሳተና በቅንነት ላይ ሳይሆን በሥጋ ጥበብ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ እግዚአብሔርን አያስደስተውም። ዓለማውያንም እንዲሁ ለእግዚአብሔር በማይመች ሕይወት የሚመላለሱ ስለሆነ ዓይኖቹ አይመለከቷቸውም።

ስለዚህ የእግዚአብሔር የሆንነውና የእግዚአብሔር ነን የምንል ሁሉ ንጹሐን ልንሆን በንጽሕናም ወደ እግዚአብሔር ልንቀርብ ይገባል። በመሆኑም ሁላችን የምናቀርብለትን ስጦታ የሚቀበለው ከኃጢአት የተለየ፥ ክፋት የሌለበት እንደሆነ ዐውቀንና ሰውነታችንን አንጽተን፤ በንስሐ ውኃ ታጥበን፥ በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ ታትመን መገኘት ይኖርብናል። ለዚህ በረከትና ደጋ እንዲያበቃን የእግዚአብሔር ቸርነቱ፥ የወላዲተ አምላክ አማላጅነቷ፥ የቅዱሳን ጸሎታቸውና በረከታቸው፥ የመላእክት ጥበቃ ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን። ✣

ወይትባረክ እግዚአብሔር

## ግቡ ከሐመሯ

የጥንቱ እንዳይጠፋ እኛም እንዳንወድቅ፥
ማስተዋል እንዲህ ነው የልቡናን ማወቅ፥
ኀሊናን መማረክ በአምላክ ቃል መድመቅ።
በመጽሐፍ ያለውን ሁሉንም ጠንቅቃ፥
ረጋ ባለ መንፈስ ከምሥጢሩ ጠልቃ፥
ቅረቡ አለችን ሐመር የእኛ አለቃ።
ዱብ ዕዳ ሆኖብኝ የዓለም ክህደቱ፥
ሳስብ ስጠራጠር ስጨነቅ በከንቱ፥
ንዑ ኀቤየ ቡሩካኑ አለች ሐመራቱ።
ሐመር ቤተክርስቲያን ሐመር እመቤቴ፥
መጥቻለሁ እነሆ ቁሚልኝ ለሕይወቴ፥
ርኅርኅት ነሽና ቅድስቲቱ እናቴ።
ዘምራለሁ እንግዲህ ያሬዳዊ ዜማ፥
ተወልደዋልና ልጆች ለእኛ እማማ።
ዋፈጠን በሉ ግቡ ከሐመሯ፥
ሕይወትን ለማትረፍ ሳይዘጋ በሯ፥
ዶግማዋ የታመነ ሰማይ ነው አገሯ።

ዲያቆን ደጀኔ ሽፈራው
ዘአማኑኤል ካቴድራል



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# ኪነ ጥበብ

## የታተመ ፍቅር

ከዳንኤል ክብረት

«የመግደሎን አገር ሰው ነኝ። ብዙ ኃጢአት የሚያሠሩኝ ሰባት አጋንንት በላዬ ሰፍረው ያሰቃዩኝ ነበር። ከሰው በታች ሆኜ እንደ ዕብድ ተቆጥሬ እኖር ነበር። በሩቁ የሚሸሸኝ እንጂ ቀርቦ የማያነጋግረኝ፥ አብሮኝ የሚበላ ወግ አጥባቂው የሀገሬ ሰው አልነበረም። ቤተዘመዶቼ ሰልችቻቸው ትተውኛል። የትም ውየ ሳድር «ልማዷ ነው» እያሉ መፈለጋቸውን እርግፍ አድርገው ትተውታል። የመገደሎን ነዋሪዎች ገና በሩቅ ሲያዩኝ «ያች ጋኔላም መጣች» እያሉ ከኔ እየሸሹ ይጠቃቀሱብኛል።

አንድ ቀን ነው መንገድ ለመንገድ እየተቅበዘበዝኩ ስጓዝ፥ እንደ ቁራ ስጮህ እፊት ለፊቴ ብዙ ሰዎች የሚከተሉት አንድ ሰው ወደ እኔ ሲመጣ ተመለከትኩት። ቆም አልኩና አስተዋልኩት። ፈገግ ብሎ ወደ እኔ ያመራል። ወደ እኔ በፈገግታና ሳይከፋ፥ ሳይፈራኝ፥ ሳይጠቃቀስብኝና ሳይጠየፈኝ የመጣ የመጀመሪያው ሰው እሱ ብቻ ነው። ገርሞኝ ደንቆኝ ከቆም ኩበት አልተንቀሳቀስኩም።

«እናንተ አጋንንት እላችኋለሁ ውጡ» አለ ያ ሰው በሚያስገመግም ድምፁ። ቃላት አይደለም የተናገረው። አንድ የሆነ ኃይል ነው፤ መንፈስ። ኃይሉ ውስጤን ዘልቆ ገብቶ ሲበረብረው ሲፈትሸው ይታወቀኛል። ከራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ አናውጾኛል። አንድ የሆነ ነገር ከላየ ግፍፍ ብሎ ሲነሣና አእምሮየ ልክ የተፋቀ ሲመስለኝ ይታወቀኛል። ያለወትሮየ ፈገግ አልኩ። እንዲያው ሰው የመሆን ስሜት ተሰማኝ። ቀና ስል ያ ቅድም ወደ እኔ ሲመጣ የነበረው እነዚያን መድኃኒት የሆኑ ቃላት የተናገረው ሰው ፈገግታው እንዳበራ እጁን ወደ እኔ ዘርግቶ ቆሞአል። እዚያ አካባቢ የነበረው ሕዝብ ሁሉ ዓይኑ እኔ ላይ ተተክሎአል። ምናልባት ገርሞአቸው ይሆናል። ያ ሰው ከእኔ ጋር በመነጋገሩ፥ ወደ እኔ በመምጣቱ እንባ እንባ አለኝ። ፈገግታው ተራ አይደለም፤ የሳቅ ሳይሆን የፍቅር፥ የደግነት፥ የአባትነት፥ ወደ እርሱ የሚስብ፥ የሚጠራ የሚጋብዝ እንጂ።

ምን እንደጐተተኝ ሳላውቅ ተንደርድሬ ሄጄ እግሩ ሥር ተደፋሁ። እግሮቹን ሳምኩ። እንባዬ እየወረደ እግሩ ላይ ተደፋሁ።

«ማርያም ተነሺ ኃጢአትሽ ተሠርዮልሻል» አለኝ። እናም በቀኝ እጁ ቀና አደረገኝ። ከኋላው እጅግ ብዙ የሚሆኑ ወንዶች ከእነርሱ በኋላም በጣም ብዙ ሴቶች ቆመው ይመለከቱኛል። እኔም ተቀላቀልኩ። ከዚያ በኋላ ከእሱ አልተለየሁም።

ይኸን ታሪክ ሁሉም ያውቀዋል። የማይረዱልኝ ግን አንድ ታሪክ አለኝ። አንድ ልባዊ ታሪክ። ለጌታዬ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለኝ ፍቅር። ከዚያ መዓት፥ ከዚያ ውርደት፥ ከበታችነት፥ ከአጋንንት መጫወቻነት ላወጣኝ ክርስቶስ ያለኝ ልባዊ ፍቅር። አገር ይሸሸኝና ይንቀኝ ብሎም ይጠላኝ የነበርኩ ሰው ከጌታዬ ጋር ከዋለበት ውየ ካደረበት ለማደርና ቃሉን እንደ እህል ውኃ ለመመገብ፥ ሰው ተብየ ለመቆጠር ያበቃኝ እርሱ ነውና እስከሞት ድረስ በነፍሴ ፍቅሩ ተቀርጾባታል።

ታዲያ ያች የጭንቅ ቀን መጣች።

...ይኸን ስትለኝ አንገቷን ደፋ አድርጋ የዕንባ ዘለላዎች በጉንጮቿ የክረምት ጐርፍ መውረጃ የመሰለ መሥመር ሠርተው ነው። ከዚያም ደፋ አለችና ጉልበቷ ላይ ተንሰቅስቃ አለቀሰች። እውነትም ለእርሱ ልዩ ፍቅር አላት። ምን ታድርግ? የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያውቀው የቀመሰው ነው። የመድኃኒትን ጥቅም የሚያውቀው ታሞ የዳነበት አይደል? ብዕሬን ከብራናየ አገናኝቼ ቀና ብላ የኔን ልቦና የሚመስጥ ታሪኳን እንድታወጋኝ ጠበቅኋት። ፀጥ ርጭ ብሏል። በማርቆስ እናት ቤት ውስጥ ጸሎት እየተደረገ ስለሆነ ግቢው ኰሽ የሚል ድምፅ እንኳን የለውም። ሩፊኖስ የተባልኩት ታሪክ ጸሐፊና መግደላዊት ማርያም ከቤቱ በስተቀኝ ነው የተቀመጥነው።

ቀና አለች። ፊቷ ከብዷል። የዕንባ መሥመሮቹ አሁንም አልጠፉም። ዓይኗ ቀልቷል። በዚያች ቀን እርሱን ሲይዙት እነማርታ ቤት ነበርኩ። ሐዋርያትን ወደ አልዓዛር ቤት ለፋሲካ ወስዷቸው ስለነበር እኛ ሴቶቹ በማርታ ቤት ምግብ ለጉባኤው እያበሰልን ነበር። ጠዋት ታዲያ ኢየሩሳሌም ትታመሳለች። ስንወጣ በአካባቢው ሰው የለም። ወደመሐል ከተማ የሚያወጣውን መንገድ ይዤ ብቅ አልኩ። ሰው መታጠቂያውን ሳይቀር እየጣለ ወደ መሐል ከተማ ይንጉዳል። ይጋፋል፥ ይሮጣል፥ ይወድቃል፥ ይነሣል፥ ይንሾካሾካል። ምን ልበል? ልቤ በጣም ፈራ። ቶሎ ብሎ ሃሳቤ ወደ ጌታዬ ሄደ። ከጥቂት




© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ቀናት በፊት እንደሚይዙት፥ እንደሚ ሰቀል ነግሮን ነበር። ያን ሳስበው ሁል ጊዜ ልቤ እንዳለቀሰ ነበር።

አንድ አዛውንት በከዘራ እየተ መረኮዙ ጉንበስ ቀና እያሉ ሲሮጡ አየሁና፥

«ምንድን ተፈጠረ አባቴ?» አልኳቸው።



አይ! ጨካኙ የሰው ልጅ...! አይ ውለታ ቢሱ የሰው ልጅ..

«አልሰማሽም?» አሉኝ።

«ምኑን?»

«ያ ወንበዴ እኮ ተያዘ»

«የቱ?» አልኩ ልቤ እስኪፈርስ ደንግጬ።

«ያ ኢየሱስ የሚሉት»

ብቻ...ብቻ...ብቻ...ነፍሴን አላውቀውም። መጐናፀፊያዬም የት እንደ ወደቀ አላሰታውሰውም። እግሬ ምን እንደሚረግጥ ትዝ አይለኝም። ያኔ ያየኝ የኢየሩሳሌም ነዋሪ፥ «አገረሸባት» ሳይለኝ አለቀረም።

ሮጥኩ ወደ አልዓዛር ቤት። አገር ይታሻል፤ ይታመሳል። የሚሉት አይሰማኝም ብቻ ሩጫ ብቻ።

አልዓዛር ቤት ግን አልነበረም።

ቆም አልኩ። እጆቼ ይንቀጠ ቀጣሉ፤ እግሮቼ ብርክ ይዟቸዋል። ዕንባዩ ገደቡ ተለቋል። «ጌታዬን! ጌታዬን!» እላለሁ ደጋግሜ።

«የታባቱ ዋጋውን ሰጡት» የሚል ንግግር ሰምቼ ወደቀኜ ዞር ስል አንድ ፈሪሳዊ ኑሮአል።

«የት ወሰዱት?» አለው አጠገቡ የነበረ ጓደኛው መሰለኝ።

«እቀያፋ ግቢ ነው አሉ።»

ከዚያ በኋላ የተናገሩትን አልሰ ማሁም ወደቀያፋ ግቢ። መሬት ቁና ሆናለች፤ ሕዝብ እንደ ተልባ ይታመሳል፤ እንደ አይጥ ይተረማ መሳል ግቢውን ከቦ።

«በለው በለው ደህና አርገህ»

«ጅራፉን አጥፈህ በለው»

«ስቀለው አንጠልጥለው»

አንዱ የሚደነፋውን ሌላው አይሰማውም። ብቻ ትርምስ ብቻ።

ነፍሴ እስኪጠፉ፥ ልቤ ልትፈነዳ እስከምትደርስ እየሮጥኩ ትርምሱን ሰንጥቄ ገባሁ። ዱላው፥ ግፊያው፥ ጥፊው፥ አወላልቆኝ አጥሩ ሥር ተጠጋሁ።


ያ የዕንባ ጐርፍ ተከፈተ። ተንከ ባለልኩ፤ ተፈጠፈጥኩ። እኒያ ወጠ ምሻ የሮማ ገራፊዎች፥ እኒያ ግንድ የሚያካክሉ የቀያፋ ዘቦች እየተፈ ራረቁ ይወርዱበታል። ጅራፍ ሲያልቅ ጅራፍ እየተኩ፥ ጉልበት ሲደክም ጉልበት እየጨመሩ መከራ ውን ያሳዩታል። ወዙ ከግንባሩ ወርዶ ፊቱን አጥለቅልቆታል። ከዚያም የተቸፈቸፈው ፊቱ ያመነጨው ደም ከወዙ ጋር ተቀላቅሎ የግንቦትን ጀንበር አስመስሎታል። ደክሞአል። ሌሊቱን ሙሉ ያለዕረፍት ሲቀጠቀጥ እንዳደረ እርግጠኛ ነበርኩ። አይ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ጨካኝ የሰው ልጅ፥ አይ ውለታ ቢሱ የሰው ልጅ.። አየ! አላዋቂው የሰው ልጅ…

በለቅሶ ባሕር ተዋጠች። እያለ ቀስኩ አብሬያት እጽፋለሁ። እያስ ነባችኝ ብዕሬም ታነባለች። ቀለም ሳይሆን ሕይወት፥ የፍቅር ሕይወት። ምነው እኔም ለጌታዬ ለሞተልኝ አምላክ፥ ደሙን ላፈሰሰልኝ ሥጋውን



እንዲያ መከራ ሲያበዙበት ከዋሉ በኋላ፥ እያዳፉ ወስደው፥ እየደበደቡ እንደወንጀለኛ ቀራንዮ ላይ…

ለቆረሰው ጌታ የእሷን ግማሽ ፍቅር ቢኖረኝ? የሰው ልጅኮ ለጌታው ይኸን ያህል ፍቅር ቢኖረው ኃጢአት ባልሠራ ነበር አልኩኝ በልቤ ሩፋኖስ። ከዚያ በኋላ አለችና ጀመረች እንደገና።

ከዚያች ቦታ መነቃነቅ አልቻልኩም። ግማሹ ይሰድበኛል፤ ሌላው በጥፊ ያልሰኛል። የቀረው «አንችንም አብሮ መጨመር ነበር» እያለ ይዝትብኛል። አንዳንዱ ደግሞ ውሻ! ጥፊ ከዚህ ብሎ ያባርረኛል። ግን ግን ወንድሜ ሩፋኖስ! ፍቅር ሁሉን ያስችልሃል፤ ሁሉን ያስታግሥሃል፥ መከራን የማጣፈጫው ጨው ለአም ላክህ ያለህ ፍቅር ነው።

እያዳፉ ወደ ጲላጦስ ግቢ ይዘውት ተጓዙ። አየ የዚያን ጊዜ ያየው አሣር፥ የተቀበለው መከራ፥ የተከመረበት ሕማም! ከዚያ በፊት ከዚያም በኋላ ማንም አጋጥሞታል ብዬ አልጠረጥርም። ወገቡ በገመድ ታሥሮ እፊት ያለ ሲጐትተው ከኋላ ያለ ሲለቀው ባፍጢሙ ሲደፋ፥ እዚያው ላይ በእግራቸው ሲረግጡት፥ ተነስ ብለው ሲደበድቡት፥ በል ሲላቸው ደግሞ መሬት ለመሬት እየሳቡ ሲወስዱት፥ በባልጩት ድንጋይ ፊቱን ሲጠፈጥፉት፤ የቻለ በዱላ ያልቻለ በጥፊ የራቀው በድንጋይ፥ የደከመው በስድብ ከበው አሰቃዩት። ለኛ ሲል ጌታችን ተሰቃየ።

እከተለው ነበር በሩቁ እየገፈተሩኝ። ከልቤ ነበርና አልጠፋም ነበርና የሠራልኝ ሥራ፥ የዋለልኝ ውለታ፥ ያ ፍቅሩ፥ እኔን የተጠለሁትን፥ የተናቅሁትን ያነሣበት፥ ያዳነበት ርኅራኄው በልቤ ታትሞ ነበርና ልርቀው አልቻልኩም። መንገድ ላይ ሌሎች እህቶችን አገኘኋቸውና አብረን እያለቀስን ወደ ጲላጦስ ግቢ ተከተልነው።

እዚያም ሩፋኖስ የዱላው አበዛዝ፥ የጅራፉ ጩኸት፥ የገራፊው ብርታት ዕንባን አስጨርሶ ደምን ያስለቅሳል። መላ ሰውነትን ያንዘፈዝፋል። ህሊናህን ስተህ ጥፋ ጥፋ ይላል። ትዕግሥቱን፥ ደግነቱን ስታይ ልቦና አይተርፍህም። እንዲያ ሲያሰቃዩት ከዋሉ በኋላ እያዳፉ ወስደው፥ እንደወንጀለኛ ቀራንዮ ላይ፤ ወይኔ ጌታዬ፥ ጌታዬ ለእኔ ብለህ…

የዕንባ ብርድ ልብስ አለበሳት።

ይገርማል ዕንባዬ አላቋርጥ አለ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን ገና ነው በልቤ የተቀረፀው። የክርስቶስን ፍቅር የቀመሰ ያውቃል።

አልቅሳ ቀና ብላ እንዲህ ቀጠለችልኝ።

በብዕሬና በልቤ ተከተልኳት፥ ሌላ ጉድ መጣ!

ጨረቃ ደም መስላ ፀሐይዋ ጨለመች፤ ከዋክብት ረግፈው መሬት ተናወጠች፤ ጌታዬ ተፈጸመ ብሎ ነፍሱን ሰጠ። ዮሴፍ የተባለ የአርማትያ ሰው በአዲስ በፍታገንዞ በአዲስ መቃብር በዚያው በጐልጐታ ቀበረው።

ማደር አይበለው አዳሬ፤ ሁላችንም በሦስተኛው ቀን እነሳለሁ ብሎ ስለነበር የጌታን ትንሣኤ ሳናይ እህል ላንቀምስ ተነጋግረናል። ቅዳሜ ጠዋት ብቅ ብዬ በሩቁ ያችን



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ጐልጐታ አየሁዋት። የሮማ ወታደሮች በተጠንቀቅ መቃብሩን ይጠብቁታል። አልቻልኩም ወንድሜ ሩፋኖስ ያች የትንሣኤ ሌሊት እስከምትደርስ መቆየት። ስቃዩ፥ መከራው፥ ላቡ ትዝ እያለኝ ጐትቶ ቀራንዮ ይወስደኛል። ፍቅሩን ሳስታውሰው ጌታዬ ጥሪው ትዝ ሲለኝ ከኃጢአት ባርነት፥ ከዲያብሎስ ቁራኛነት የጠራሁበት ቀኑ ትዝ ሲለኝ ሳላስበው ጐልጐታ እገኛለሁ።

እንደምንም መቼም ቅዳሜ መሸልኝ። አብረውኝ የነበሩ እህቶቼ፥ «ምናለ ትንሽ ብትተኚ» ብለው ተቆጡኝ። ጋደም አልኩ። ግን አልተኛሁም። ዓይኔን ጨፈንኩ። ግን አላንቀላፋሁም። ሃሳቤ የነበረው ጐልጐታ ነው። አሁንም አሁንም ከቀያፋ ግቢ እስከ ጐልጐታ ያደረገው ጉዞ በሃሳቤ ይጠነጠንብኛል እየደጋገመ። ተነሳሁ። አልቻልኩም። ወደበሩ ተጠጋሁ፤ በቀዳዳ አጮለቅኩ፤ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ነው። ሂጂ ብረሪ ብረሪ ወደ ጐልጐታ የሚል ሃሳብ መጣብኝ። ቀስ ብየ የበሩን መሸጐሪያ ከፈትኩ። የውሾች ጩኸት ባሻገር ይሰማል። ከዚያ ውጭ ሌላ ነገር የለም። ብቻ ለሌሊት የምሥራቅ መንገደኞች ተብሎ የሚበራው የመንገድ ላይ መብራት ብልጭ ድርግም ይላል።

በሩን መለስ አደረግኹኝና ዘወር ዘወር ብዬ አይቼ የቀራንዮን አቅጣጫ ይዤ ሮጥኩ አላስችለኝ ብሏል ተነሥቼ እስካየው። የነበረኝ ተስፋ መቃብሩን ማየት ነው። እናም የሌሊት ዘበኞች ትዝ አላሉኝም፤ የሌሊት አራዊት በልቤ አልታሰቡም። ብቻ ሌሊትም እንደቀን ሩጫ። ወደ ቀራንዮ በሩቁ ብልጭ ድርግም የምትል የመብራት ብርሃን ትታየኛለች። የሮማ ወታደሮች በጥበቃ ላይ ስላሉ የእነርሱ መሰለችኝ።

ይገርምሃል ወንድሜ ሩፋኖስ። የጠባቂ መኖር አለመኖር በዚያ ሰዓት ጉዳዬ አልነበረም። እንደምታውቀው የጐልጐታ መንገድ ደግሞ የዋዛ አይምሰልህ። ያባበጠ አለት፥ የሾለ ባልጩት የሚጨመድድ እሾህ የሚበዛበት ቦታ ነው። ልብሴን ሲቧጥጠው እግሬን ሲቆራርጠው፥ ጥፍሬን ሲያወላልቀው እኔ መች ተበገርኩ።

የሮማ ወታደሮች ተኝተዋል። እሳቱ ይነዳል። ሌሊቱም እያለቀ ነው ሰማዩ «አመድ የአህያ ሆድ» መስሏል። ቀስ ብዬ ወደ መቃብሩ ልጠጋ ስል የእግሬን ኮሽታ ሰምተው ወታደሮቹ ነቁና ወደ መቃብሩ ተመልክተው ባንድ ጊዜ ወደ እኔ ዞር አሉ። ከዚያም ተጠቃቀሱና ቁልቁል በፍጥነት እየተንደረደሩ ወረዱ። ደንግጬ ቆሜ ሳስተውላቸው ከቆየሁ በኋላ እኔም ተጠጋሁ። ድንጋዩ ተንከባሏል፤ መቃብሩ ተከፍቷል። እየተንቀጠቀጥኩ ወደ ውስጥ ስመለከት ባዶ ነው። የከፈን ጨርቅ ግን በውስጡ ነበረ።

ጌታዬን አጣሁት።

ተመልሼ ወደ ኢየሩሳሌም በድንገት መሮጥ ጀመርኩ። ሄጄም ለሐዋርያት ነገርኳቸው። ጴጥሮስና ዮሐንስ እየሮጡ መጡ። ያው ባዶ መቃብር ብቻ ነው። ወዲያው ተመልሰው ሄዱ። እኔ ግን እያለቀስኩ በዚያ ነበርኩ። ጌታዬን ሳላገኝ እርሱን ሳላይ አልሄድም ብዬ ጸናሁ የእግዚአብሔርን ጸጋ የምታገኝበት መንገድ ትዕግሥት ነው።

በዚያ የመቃብር ቦታ በዚያች ሰዓት ያለኔ ማንም አልነበረም። ወዲያው ተመልሼ ዝቅ ብዬ ወደመቃብሩ ስመለከት ሁለት ነጫጭ የለበሱ መላእክት በመቃብሩ ራስጌና ግርጌ ቆመው አየሁ። አንዱም ቀረብ ብሎ «ስለምን ታለቅሻለሽ» አለኝ። ንግግሬ በለቅሶየ እየተቆራረጠ፥ «ጌ.ታ.ዬ.ን ወ.ስ.ደ.ው.ታ.ል» አልኩት። ይኼን ተነጋገርንና ከመቃብሩ በር ዘወር ስል አንድ ሰው ቆሞ አየሁ። የዚያ አካባቢ ጠባቂ መስሎኝ ተጠጋሁት። እርሱም፥ «አንቺ ሴት ስለምን ታለቅሻለሽ? ማንንስ ትፈልጊያለሽ?» አለኝ። እኔም፥ «ጌታ ሆይ፥ አንተ ወስደኸው እንደሆንህ ንገረኝ ወዴትም እንዳደረስከው አሳየኝ ሽቱ እቀባው ዘንድ አልኩት።

እርሱም፥ «ማርያም» አለና በማውቀው ድምፅ ስሜን ጠራኝ። ፊቴ ፈካ

«ረቡኒ» አልኩት። ጌታዬ ኖሮ አል። በደስታ ተጥለቀለቅኹ፥ «ወደ ወንድሞች ሄደሽ ወደ አባቴ አርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው» አለኝ።

እንደተመኘሁት የጌታዬን ትንሣኤ አይቼ ድምፁን ደግሞ ሰምቼ ፊቴ በደስታ በራች። ወደ ኢየሩሳሌም ወደ ወንድሞቼና ወደ እህቶቼ አመራሁ፤ ሮጥኩ። ቅድም የሐዘን አሁን የደስታ።

«ጌታዬን አየሁት» አልኳቸው። ሁሉም ደነገጡ የነገረኝንም ሁሉ ነገርኳቸው። እየዞርኩም ዜናውን ነዛሁት የትንሣኤውን። እናም ይኼውልህ ያልረሳኝ ጌታዬ የትንሣኤውን ብርሃን ከሰው ዘር መርጦ መጀመሪያ ለኔ አሳየኝ። በልቤ ውስጥ የታተመው ፍቅሩ የትንሣኤን ብርሃን ለማየት አበቃኝ።

ተሰናብቻት ስወጣ አንድ ነገር በልቤ ተቀርጾ ነበር። «ፍቅርና እምነት እስከ ላይ ያደርሳል» ያለችው ምንኛ ግሩም ፍቅር ነው? በዚህ ዘመን ይህንን የመሰለ አማናዊ ፍቅር የትም የለ። ከዚያ ከመጀመሪያው የመዳን ቀን እስከ ቀራንዮ፥ እስከ መቃብሩ ሥፍራ፥ እስከ ጎልጎታ ድረስ ያውም በእንባ የራስ፥ በትዝታ ባሕር የሚያስዋኝ ድንቅ ፍቅር።

ለመሆኑ እኔስ ለክርስቶስ ያለኝ ፍቅር ምን ያህል ይሆን? ብዬ የራሴን ሕይወት በዚህች በማርያም አንፃር መረመርኩት ለካ ባዶ ነኝ። ገና አላመንኩም አልኩ። የእርሷ እውነተኛ ፍቅር እኔንም በእውነት ክርስቶስን እንዳፈቅር አድርጎኛል። እንዲያው ለወደፊቱ ዘመናት ሲለወጡ፥ ጊዜ ሲቀየር፥ ዓመታት አልፈው ዓመታት ሲተኩ የሚወለደው ትውልድ ከዚህች ሴት ሕይወት ምን ይማር ይሆን? መንፈሳዊ ፍቅርን ከእርሷ፥ ጽናትንና ትዕግሥትን ከሕይወቷ ማን ይማር ይሆን? መንፈሳዊ ፍቅርን ከእርሷ፥ ጽናትንና ትዕግሥትን ከሕይወቷ መማርና ለክርስቶስ ያለውን እውነተኛ ፍቅር በእንባ መግለጥ ታላቅ መታደል ነው።

«ፍቅርና እምነት ዘለዓለማዊው ተስፋም እስከ ላይ ያደርሳል» አለችኝ የማይረሳ የፍቅር ማኅተም በልቤ ውስጥ ቀርፃ። ✣

ሩፋኖስ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# የተወደዱ እግሮች

ከመምህር ዐወቀ ተሰማ

ወንጌል በዓለም ላይ ተስፋፍቶ ለሰው ልጆች የድኅነት መሠረት እንዲጣል በማድረግ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዙት ሐዋርያት ናቸው። ሐዋርያ ማለት «የተላከ፥ መልእክተኛ» ማለት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሥራ ከመጀመሩ አስቀድሞ ቃሉን ለዓለም የሚያዳርሱ ሰዎችን መምረጥ ጀመረ። በቅደም ተከተልም 12 ሰዎችን (ሐዋርያትን) መረጠ። በመጀመሪያ የተመረጡት ስምዖንና (ጴጥሮስ) ወንድሙ እንድርያስ ናቸው። ዮሐ.1፥14–44። ቀጥሎም ፊልጶስንና ናትናኤልን መረጠ። ሌሎችንም እንዲሁ ከተለያየ ቦታ መርጧል። ማቴ.4፥21። ም.9፥9። ሁሉም የተመረጡት ለአንድ ዓይነት ዓላማና አገልግሎት ሲሆን ይኸውም ወደ ተለያየ ቦታ ፈጥነው በመሄድ የሕይወት ምስትና የሆነውን የጌታን ቃል (ወንጌልን) ለዓለም ሁሉ እንዲያስተምሩና መላው ዓለም እንዲድን ነው። ሲልካቸውም «ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲፈጽሙ አድርጓቸው እነሆ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ብሏቸው ነበርና። ማቴ.28፥20። እነሱም ይህን የአምላክ ቃል ተቀብለው መከራ መስቀሉን ተሸክመው ሳያቅማሙና ሳያንገራግሩ በደስታ ወደ ዓለም ተጓዙ። ሥራቸውን ሲጀምሩም እግዚአብሔር በገባላቸው ቃል መሠረት አብሯቸው ይሠራ ነበር፤ ተአምራትንም የማድረግ ሥልጣን በመስጠት የትምህርታቸውን እውነተኛነት ያጸና ነበር። ማር.16፥20። የብዙዎቹም ሐዋርያት ሥራቸው ዓሣ ማጥመድ ነበር። ማር.1፥16–20። ስለዚህ እግሮቻቸው ከሚቀዘቅዘው ባሕር ውስጥ ነበር የሚውሉት ማለት ነው። እግዚአብሔር ግን ከዚህ የኃጢአት ምሳሌ ከሆነው ባሕረ ዓለም (የዓለም ባሕር) እግሮቻቸውን አወጣላቸው። ወደመልካም ቦታ ሄደው የምሥራችን እንዲናገሩ ፈቀደላቸው። ልዩ ምርጫ ነው።

እንግዲህ የሐዋርያትን ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንብበን ስናስተውለው መንፈሳዊ ቅንዓትን ያሳድራል። ምነው እኔም እንደ አንዱ ሐዋርያ በሆንኩ ያሰኛል «እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ እንግዲያስ ምን እናገኝ ይሆን?» የሚል ጥያቄ ባቀረቡ ጊዜ «የሰው ልጅ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ለፍርድ በክብሩ ዙፋን ሲቀመጥ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ልትፈርዱ በአሥራ ሁለቱ ዙፋን ትቀመጣላችሁ» ማቴ.19፥27–29። የሚለውን ተመልክተን እግዚአብሔር የገባላቸውን ቃል ስንረዳ ደግሞ አሁኑኑ ተነሥታችሁ ሂዱ!! ሂዱ! ያሰኛል። የሐዋርያት ቅዱስ ተግባራቸው ያለችግር በሄዱበት በደረሱበት ድውይ በሽተኛ) መፈወስ፥ ኀባጣ ማቅናት፥ ቃለ ወንጌልን ለሁሉ ማዳረስ ነበር። የሐዋ.3፥1፤5፥42። ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ስጦታ ደስ ስለሚያሰኛቸው ለዚህ ቅን አገልግሎት መሄድ አይታክታቸውም ነበር። የተወደዱ እግሮች የተመረጡ የተቀደሱ እግሮች ያሏችኋል እኒህ ናቸው።

ሐዋርያት እግዚአብሔርን በማወቃቸው እግሮቻቸውን ወደ መልካም ቦታ ሲያቀኑ እግዚአብሔርን ያላወቁት ደግሞ እግራቸው ደምን ለማፍሰስ ይጣደፍ ነበር። ይህንንም ቅ/ዳዊት፥ «ደምን ለማፍሰስ እግራቸው ፈጣን ነው ጥፋትና ጉስቊልና በመንገዳቸው አለ የሰላምን መንገድ አላወቋትምና» በማለት ለጥፋት የተዘጋጁትን እግሮች ሁኔታ ያስረዳል። መዝ.13:14፥16።

እነዚህን ካመዛዘንን በኋላ ነው እንግዲህ የኛ እግሮች የትኛውን ሥፍራ ይዘዋል ብለን ራሳችንን ወደ መጠየቅ የምንመለሰው። ከመልካሞቹ ነዋ! የሚለው መልስ የጥቂቶቹ ሰዎች መልስ ነው። አንዳንድም ቢሆኑ እግራቸውን የገቱ አይታጡምና። የብዙዎቻችን እግሮች ግን የሚመደቡት ከደም አፍሳሾቹ እግሮች ጋር ነው። ዛሬ በርካታው የዓለም ሕዝብ የወንድሙን ደም ለማፍሰስ አምርሮ ሲገሠግሥ ይታያል። ማጥፋት እንጂ ማልማት፤ መግደል እንጂ ማዳን አይታየውም። ዓይኑ ልቡናው በክህደት ታውሯልና መርገጥን እንጂ ማንሳትን አያውቅም። እግረ ልቡናው ደንድኗልና በእርግጥ ከዚህ ዓለም ጨርሶ ደም አፍሳሽ ይጠፋል ተብሎ አይገመትም። ሁላችንም ግን ተባባሪ መሆን የለብንም፤ የሆንም ካለን ከዚህ ዓይነት አድራጎታችን ተመልሰን ፈጣሪያችንን ይቅርታ መጠየቅ አለብን «ለጽድቅ የማይበር እግር ይሰበር» እንዲሉ። የአንዱ እግር ደም ለማፍሰስ ሲጣደፍ የእግዚአብሔር ሰዎች ደግሞ ደም ለማፈስ መሄድ አለባቸው፤ ከወንጌል የተማርነው ይህን ነውና አንዱ እግረኛ አልፎት የሄደውን ቁስለኛ ሌላ እግረኛ ግን ከነደሙ አፍሶ ወደ ቤቱ ወሰደው መልካም እግር። ሉቃ.10፥29–37። እንግዲህ ዛሬ ዓለም በጥቅሉ ስትታይ ደም አፍሳሾች በዝተውባታል ለማለት ይቻላል። በመሆኑም የብዙዎቻችን እግሮች ወደ ጥፋት ተሰማርተዋል። የማይገባ ቦታ ረግጠዋል፤ እየረገጡም ናቸው። ሰውን ያህል ክቡር ፍጥረት እንደስልቻ (አቁማዳ) አልፍተዋል፤ እንመልሳቸው፤ ያለፈው ይብቃቸው፤ እግር እኮ ሌሎቹን ህዋሳት ሁሉ የሚመራ ከሁሉም የሚቀድም ነው። በመሆኑም መላውን አካላችንን ተሸክሞ በመዞር ወደ አጉል ቦታ በመውሰድ ኃጢአት እያሠራው ጣዖት እያስመለከው ነውና ከእንዲህ ያለው መጥፎ ቦታ ተመልሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲያመራ በአእምሮአችን መሪነት እናስገድደው።

ጉዞአችን ሁሉ ከዚህ ዓለም የተለየ ሊሆን ይገባል። ይህን ዓለም ተከትለን የምንጓዝ ከሆነ መጨረሻችን ውድቀት የሞት ሞት (በኃጢአት የሚመጣ ቅጣት) ይሆናል። ይህን ዓለም ተከትለው የሚጓዙ ሁሉ አወዳደቃቸው የከፋ ነው። ኢሳ.37፥36–38።

ሐዋርያት የታደሉ ናቸው። በእግራቸው ገሥግሠው በእጃቸው ዳሰው፤ በቃላቸው አስተምረው መላውን ዓለም ከሞት አተረፉ። የረገጡት መሬት ሁሉ የተቀደሰ ነበር። ይህን ለአጥፊነት የሚጋብዝ ዓለም ተዉት፤ ይህን የሚንቅ ዓለም ናቁት፤ የሞተ ዓለም ብለው ሰደቡት፤ በእውነት ደስ የሚያሰኝ ነው። እኛም ይህን እንምረጥ። እንደ ሐዋርያት አድርገን እንበል ያጠፋነው የበደልነውም ካለ ንስሐ እንግባና ፈጣሪያችንን ይቅርታ እንጠይቀው። ለሐዋርያነት ይመር ጠን ይሆናል ለእሱ የሚሳነው ነገር የለም። ማን ያውቃል? ያም ባይ ሆን ከሐዋርያት በረከት ያሳትፈናል። እግዚአብሔር እግሮቻችንን ወደ መ ልካም ቦታ ያቅናልን። የሐዋርያት እግሮች በጌታችን ቅዱሳት እጆች የታጠቡ ናቸው። የእኛም እግሮች ከኃጢአት የታጠቡ ንጹሐን እንዲሆኑ እግዚአብሔር በሐዋርያት አማላጅነት ይጠብቀን። አሜን።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# እናስተዋውቃችሁ

*በዚህ ዓምድ ገዳማትን፣ አድባራትን፣ ታሪካዊና ተአምራዊ ቦታዎችን፣ የቤተ ክርስቲያን አባቶችንና ሌሎችንም እናስተዋውቃለን።*

በሰሜን ኦሞ ሀገረ ስብከት በሳቱሳ አውራጃ በቦረዳ ወረዳ በሚገኘው ዋሻ ውስጥ አሉ ስለተባሉት ጽላት በቁጥር 1 መጽሔታችን ከአቶ ወ/ገብርኤልና ከአቶ ሐታ ጭላሎ ጋር ያደረግነውን ቃለ መጠይቅ አቅርበን ለዛሬ የሀ/ስብከቱን ሊቀጳጳስና ሌሎች ሰዎችን አነጋግረን እንደምናስነብባችሁ ቀጠሮ ይዘን ነበረ። በቀጠሮው መሠረት ለዛሬ ያዘጋጀነውን እነሆ!!

ስለ ቦረዳው ዋሻ በሰማን ጊዜ ስለሁኔታው እንዲያስረዱን የመረጥ ነው የሀ/ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዘዛርያስን ነበረ። በዚያ አጋጣሚ ብፁዕነታቸው ለቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ስለነበር እርሳቸውን ለማግኘት ርቆ መሔድ አላስፈለገኝም ነበርና በመንበረ ፓትርያርክ ወደሚገኘው የማረፊያ ቤታቸው ማስታወሻዬን በመያዝ ሔድኩ። የመጣሁበትን ጉዳይ ስነግራቸው ከሥራ ብዛት የተነሣ ለጊዜው ሊያነጋግሩኝ እንደማይችሉ ነገሩኝ። ነገር ግን በቦረዳ ሆኗል የሚባለውን ነገር ለማረጋገጥ መፈለጌን በመግለጽ ስለአስጨነቅኋቸው በቁማቸው የተወሰኑ ጥያቄዎቼን መልሰውልኛል።

ሐመር – ብፁዕ አባታችን በቅርቡ በእርስዎ ሀገረ ስብከት በቦረዳ ወረዳ ለአንድ ገበሬ ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል በዋሻ ውስጥ ጽላት መኖራቸውን እንደነገሩትና እርሱም ወደዋሻው በመግባት የጽላቱን መኖር እንደአረጋገጠ፣ ለእርስዎም ነገሩን በማስታወቅ ወደዋሻው ገብተው የጽላቱን መኖር ለአካባቢው ሕዝብ እንደአስታወቁ ይነገራል። ይህ ምን ያህል እውነት ነው?

ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ – እርግጥ ነው። እንዲያውም በሥፍራው ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ ኮሚቴ አቋቁሜ ሥራው እየተካሔደ አይደለም እንዴ!

ሐመር – ነገሩ እርግጠኛ ነው ማለት ነው?

ብፁዕ አባታችን – ስለዚህ ጉዳይ ግን ዳግመኛ ወደሥፍራው ሔጄ በጾምና በጸሎት እስከማረጋገጥ ድረስ ጊዜ ያስፈልገኛል።

## የቦረዳው ድንቅ ዋሻ

ካለፈው የቀጠለ

ሐመር – ብፁዕ አባታችን እርስዎ በዋሻው ውስጥ ጽላት መኖሩን ምን ያህል ያውቃሉ? ይህንን ነው ለማወቅ የፈለግነው።

ብፁዕ አባታችን – ፅላት ለመኖሩማ አለ። በዓይኔ አይቻለሁ በእጄም አንሥቼ አረጋግጫለሁ።

ሐመር – ምን ያህል ጽላት ናቸው በዋሻው ውስጥ ያሉት?

ብፁዕ አባታችን – ለጊዜው ያየሁት አንድ ጽላት ነው። ነገር ግን ወደውስጥ ዘልቄ በደንብ አልተመለከትኩም። ወዲያው ነው የወጣሁት። ምናልባት ሌላም ሊኖር ይችላል። ለዚህም ነው እንደገና ወደ ሥፍራው መመለስና ማረጋገጥ አለብኝ ያልኩት።

ሐመር – ያዩት ጽላት የማን መታሰቢያ ነው?

ብፁዕ አባታችን – ያየሁት ጽላት ረዘም ያለ ዕድሜ የቆየ ስለሆነ በላዩ ላይ ያለው ጽሑፍ እንደመፍዘዝ ብሏል ለረጅም ዘመን ከመቆየቱ የተነሳ ሳይሆን አይቀርም። በእኔ ግምት በግራኝ አሕመድ ወረራ ጊዜ ካህናት ወደዚህ ሥፍራ ያመጡት ጽላት ይመስለኛል። በዋሻው ውስጥ የሰው አፅም መኖሩንም ተመልክቻለሁ እንዲሁም የእጅ መስቀልና ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት አሉ።

ሐመር – የተመለከቱት ጽላት ታድያ የማን ይመስልዎታል?

ብፁዕ አባታችን – በላዩ ላይ የተጻፈው ጽሑፍ ቢደበዝዝም የቅዱስ ሚካኤል መሆኑን ለማረጋገጥ ችያለሁ።

ሐመር – ሌሎች ጽላት አሉ እየተባለ የሚነገረውስ ምን ያህል እውነት ነው?

ብፁዕ አባታችን – መቼም አላረጋገጥኩም። ለወደፊት ከማረጋገጥ በቀር ምናልባት እንደተባለው ብዙ ጽላት ሊኖሩ ይችላሉ። እኔ ግን የሔድኩት በችኮላ ስለነበር እስከ ዋሻው መጨረሻ ገብቼ አላየሁም!




© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ስለዚህም ዳግመኛ ከማረጋገጤ በፊት እርግጠኛ ሆኜ የምናገረው ነገር የለኝም። ሁኔታውን በጥሞና ተመልከተን ከተረጋገጠ በኋላ በዜና ማሰራጫም እናስነግራለን።

ሐመር — እግዚአብሔር ይስጥልን ብፁዕ አባታችን።

የተሠራውን ይህን ልዩ የተፈጥሮ ትንግርት እያስተዋልን ጽላቱ አለበት ወደ ተባለው አምባ ደረስን። የጽላቱ መገኛ ነው የተባለው ዋሻ ከሩቅ ሲያዩት በልዩ ኅብረ ቀለማት ባጌጡ ምእመናን ደምቋል። እንኳን ሰው የወፍ ድምፅ አይሰማበትም ተብሎ የሚገመተው ያ አካባቢ በሰዎች ተጨናንቋል። ሰው ጨረቃ መስሏል። ከአርባ ምንጭ፥ ከወላይታ ሶዶ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ቁጥሩ እጅግ ብዙ የሆነ ሕዝብ የቅዱስ ሚካኤልን በዓለ ንግሥ ሊያከብር ወደዚሁ ሥፍራ መጥቷል ቀኑ የኅዳር ሚካኤል ዋዜማ በመሆኑ።



የዋሻው መግቢያ በር በመጋረጃ ተጋርዷል፥ ምእመናንም በዝማሬ እግዚአብሔርን በማመስገን ላይ እንዳሉ

ከብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ይህን ቃል መጠይቅ ከወሰድን በኋላ ዘጋቢያችንን ወደ ቦረዳ የላክነው ኅዳር 10 ቀን 1985 ዓ.ም. ነበር። ጉዞውንም እንደሚከተለው ዘግቦታል።

ኅዳር አሥር ቀን ሶዶ አድሬ በማግስቱ ወደ ቦረዳ አብረውኝ ለክብረ በዓል ወደሥፍራው ከሄዱት ሰዎች (ምእመናን) ጋር መኪና በመኮናተር ወደ አርባ ምንጭ በሚወስደው ዋና መንገድ በስተግራ ለመኪና ፈታኝ የሆነውን የቦረዳን ዳገታማ መንገድ ተያያዝነው። ከመንገዱ በሚቦነው አቧራ ተሸፍነን ከበታች የተንጣለለውንና ልዩ ግርማ ያለውን የአባያ ሐይቅ ጥርት ካለው ሰማይ ጋር የተገናኘ በሚመስለው አቀማመጡ እየተደነቅንበት መንገዳችንን ቀጠልን። የአካባቢው መልክዓ ምድርና ዙሪያ ገባው የተለየ መስህብ አለው። ድንቅ በሆነ አምላካዊ ጥበብ

ይህን ያህል ብዛት ያለው ሕዝብ በዚህ የሀገር መጨረሻ መስሎ በሚታይ ሥፍራ በማየቴ ተገረምኩ፤ የምእመናኑንም የሃይማኖት ጽናት አደነቅሁ። በቦታው ከደረስኩ በኋላ መቅርፀ ድምፄን፥ የፎቶ ማንሻ ካሜራዬን አዘጋጅቼ ወደ ታሪከኛው ዋሻ ስቀርብ አንድ ጎልማሳ፥ «ከአዲስ አበባ ነው የመጣኸው? ስለዚህ ቦታ ተአምረኛነት ከመጀመሪያው አንስቶ እከታተል ስለነበር አንዳንድ ነገር ልነግርህ እችላለሁ» አለኝ።

የአርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ መሐንዲስ መሆኑንም ገለጠልኝ። አቶ ግርማ ሠይፉ ይባላል። ከፍ ብሎ ከብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የተነገረውና በሥፍራው የተቋቋመው ኮሚቴ ሊቀመንበር ነው። የዋሻውን ዙሪያ ገባ አዘዋውሮ አስጎበኘኝ ማብራሪያም ጭምር እየሰጠ። የጠበል ቦታዎቹንም ሁሉ አሳየኝ። ላናግራቸው የፈለግሁትን ሰዎች ሁሉ በማስጠራት በመቅርፀ ድምፄ እንድቀርፃቸው በእጅጉ ተባበረኝ።

በዚሁ መሠረት የሦስት ልጆች አባት የሆኑትና በሥፍራው ያዩትን ይናገሩ ዘንድ ታዝዘው ትእዛዘ እግዚአብሔርን ባለማክበራቸው እንደበታቸው የተዘጋውን አቶ ቲና ያሞኤ የተባሉትን ገበሬ አስጠርቼ ላነጋግራቸው ብሞክርም እርሳቸው መናገር እንደማይችሉ በመኮላተፍና በምልክት ነገሩኝ። ይህን ያህል መኮላተፍ የጀመሩትም እኔ እዚያ ከመድረሴ ጥቂት ደቂቃ ቀደም ብሎ ከሕዝቡ መካከል ሆነው ሕዝቡ «እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ» ሲል እርሳቸውም ሳያስቡት በድንገት ከሕዝቡ ጋር «እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ» እንዳሉና ከዚያ በኋላም አንደበታቸው ረትቶ ሊናገሩ እንደቻሉና ከቀድሞው ይልቅ ግን ትንሽ ስለለቀቃቸው መሆኑን ልገነዘብ ችያለሁ። (የአቶ ቲና ያሞኤ ፎቶ ግራፍ ባለፈው እትማችን ላይ የወጣ ስለሆነ ከዚያ መመልከት ይቻላል።)

በጊዜው የሀ/ስብከቱ ሊቀጳጳስ በድጋሚ ወደ ሥፍራው መጥተው በነበረው የጊዜ እጥረት ሳላነጋግራቸው ቢመለሱም ታቦቱ የማይወጣ መሆኑ በመገለጡ እኔም ታቦቱ ሲከብር ለማየት አልቻልኩም። ቢሆንም ቅሉ አንዳንድ የአካባቢው ሰዎችና በዋሻው አካባቢ ባለፉት ጊዜያት የተደረጉትን ተአምራት በመጠየቅ ዘገባዬን ማጠናቀር ጀመርኩ።

በመጀመሪያ ያነጋገርኳቸው የክልሉ ነዋሪ ሲሆኑ በዕድሜም ጠና ያሉ አባት ናቸው። የሚናገሩት



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

በአማርኛ ቋንቋ ሳይሆን በጋሙኛ በመሆኑ በአስተርጓሚ ነው ቃለ መጠይቁን ያካሄድነው። አቶ ዳና ወርቁ ይባላሉ።

ሐመር — አቶ ዳና ወርቁ በዚህ አካባቢ ያዩት ነገር ምንድነው?

አቶ ዳና ወርቁ — እኔ መጀመሪያ ያየሁት ምንድነው ብትል በጣም የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ የሚያስገርም ነገር ነው። ከዚህ በፊት የዚህ ዓይነት ነገር አይቼ አላውቅም። እኔ በሶደን ሥራ የተሰማራሁ አዳኝ ነበርኩ። ታዲያ ካለሁበት ሥፍራ ወደዚህ አካባቢ ከአጋሮቼ ጋር ሆኜ ነበር፤ ስናድን አንድ ነብር አይተን ልንገድለው ብንሯሯጥ ሊሆንልን አልቻለም። እንዲያውም ከዓይናችን ተሰውሮ ወደዋሻው ገባ። እኛ ግን ወደዚህ ዋሻ ውስጥም ልንገባ አልቻልንም። የሆነ ነገር እንዳንገባ አግዶን ነበር። ከዚያ ቀን ጀምሮ ዋሻው ልዩ ክብር ያለው መሆኑን ልናውቅ ቻልን።

ሐመር — እርስዎ በዚህ አካባቢ ያዩት ለየት ያለ ነገር አለ?

አቶ ዳና — በዋሻው ውስጥ ከበሮ ይመታል። ይህን እኔ ብቻ ሳልሆን የአካባቢው ሰው ሁሉ የሚመሰክረው ነው። የጸናጽል ሻሻታ፥ የዕጣን ሽታ የመሳሰለው በማንኛውም ሰው ዘንድ የታወቀ ነው። ምንድነው ጉዱ? እያልን ራሳችንን እንጠይቅ ነበር። በክልላችን ያሉ አንዳንድ ማርያምን የማይወዱ የእምነት ክፍሎች እዚህ ዋሻ ውስጥ ያለው ሰይጣን ነው እያ ሉም ይሰብኩን ነበር። ነገር ግን እኛ እንዳየነውና ኋላም እንደተረዳነው በዚህ ዋሻ ውስጥ ያለው እነርሱ እንዳሉት ሰይጣን ሳይሆን የእግዚ አብሔር ታቦት መሆኑን ልናረጋግጥ ችለናል።

ሐመር — ሌላስ ያዩት ነገር የለም?


አቶ ዳና — የእሳት ችቦ የያዙ እንዲሁም በእጁ ሰይፍ ይዞ የሚዞር አይቻለሁ። ይኸ ምንድን ነው? ብዬ ስጠይቅ ሚካኤልና ገብርኤል ናቸው አሉኝ። እኛ አሁን በዚህ ክልል ያለነው ሰዎች በእምነት ነው ያለነው። አሁን እኛ የአምላካችን የእግዚአ ብሔር መመስገኛ ታቦት ከዚህ ዋሻ እንዲወጣ በጣም ጓጉተናል። ይህን ቤት የሠራነው ሌት ተቀን ተረባርበን ነው። ስለዚህ ታቦቱ ከዋሻው ውስጥ የሚወጣበትን ቀን በጣም ነው የምንናፍቀው።

ከአቶ ዳና ወርቁ ቀጥሎ ቃለመ ጠይቅ የሰጡኝ አቶ ደምሴ ቱሉ ናቸው።

ሩን ነገሩን። ኋላም አባታችን መጥ ተው አይተው አረጋገጡልን።

ሐመር — እርስዎ በዚህ ዋሻ አካባቢ ያዩት ለየት ያለ ተአምር አለ?

አቶ ደምሴ — በዚያ አካባቢ (ቦታውን በጣታቸው አሻግረው እያሳዩኝ) ነጭ ልብስ የለበሰ ሰው የመሰለ ቆሞ አይቼ ይህንን ዕፁብ ድንቅ ተአምር በማየቴ እግዚአብሔ ርን አመሰገንኩ። ወደ መሬትም ተደፍቼ ሰገድኩ። ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ደግሞ ወደ ዋሻው ውስጥ የብርሃን መብራት ይዞ ገባ። ከዋሻው ውስጥም ልዩ መዓዛ ያለው የዕጣን ሽታ ይሸታል።



ኅዳር 11 ቀን 1985 ዓ.ም. ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ በቦረዳ ተገኝተው ከተሰበሰበው ሕዝብ ጋር ስለጽላቱ አወጣጥ በተወያዩበት ጊዜ

ሐመር — አቶ ደምሴ መኖሪያዎ የት ነው?

አቶ ደምሴ — የእዚህ ሀገር ነዋሪ ነኝ። እንዲያውም የቦረዳ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ ጉባኤ ምክትል ሊቀመንበር ነኝ። ይህ ሁኔታ ገና ሲጀመር ጀምሮ እከታተል ነበር። መጀመሪያ ሁኔታውን ለብፁዕ አባታችን አሳውቀን ነበር። አባታችን ግን ለስብሰባ ወደ አዲስ አበባ ሄደው ስለነበር ሁለት መነኮሳትና የአውራ ጃው ሊቀ ካህናት ሆነው በመምጣት ወደዋሻውም በመግባት ታቦት መኖ

ከአቶ ደምሴ በመቀጠል ያነጋገ ርኩት ወጣት ዘሪሁን መኩሪያን ነው።

ሐመር — ወጣት ዘሪሁን ነዋሪነ ትህ የት ነው?

ወጣት ዘሪሁን መኩሪያ — አርባ ምንጭ ነው።

ሐመር — ወደዚህ አካባቢ እንዴት ልትመጣ ቻልክ?

ዘሪሁን — ሳቁሳ አውራጃ ምዕራብ አባያ ስሠራ ሳለ ይህን ታሪክ ሰምቼ ነገሩን ለማረጋገጥ ወደ ብፁዕ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

አባታችን በመሔድ ጠየቅኋቸው። እርሳቸውም እኔ እንኳን አሁን ወደ አዲስ አበባ ለስብሰባ ልሄድ ነው። ከአውራጃው ሊቀ ካህናት ጋር ተነጋገሩበት ስለአሉኝ ወደአውራጃው ሊቀ ካህናት ሄጄ ሳናግራቸው የማውቀው ነገር የለም አሉኝ። እኔም በሥራ ምክንያት ወደ ዋጅፎ ስመጣ በዚያው ወደዚህ ደረስኩ።



ከዋሻው አጠገብ የፈለቀው ጠበል

ሐመር — ወደዚህ ስትመጣ ያየኸው አስገራሚ ነገር ነበር?

ዘሪሁን — ይገርምሃል እዚህ ሥፍራ ለመድረስ የአንድ ሰዓት መንገድ ሲቀረኝ ነበር አንድ ዓይነት ልዩ ስሜት የተሰማኝ። በዚህም የቦታውን ቅድስና ልረዳ ችያለሁ። ደግሞ ሌላው የገረመኝና የደነቀኝ ነገር መላእክቱ ታይተውት ወደ ዋሻው ውስጥ ገብቶ የታቦታቱን መኖር የተናገረው ሰው፤ ወልደ ገብርኤል ማለቴ ነው፤ ቀድሞ ከጋሙኛ በስተቀር አማርኛ መናገርም ሆነ ማንበብ የማይችል ሆኖ ሳለ ዋሻው ውስጥ ገብቶ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ ግን አማርኛ መናገር መቻሉ፥ አማርኛም ሆነ ግእዝ ማንበብ መቻሉ፥ በጣም ያስገረመኝ ነገር ነው። ጆሮውን ቢቆርጡት አማርኛ የማይሰማ ሰው እንደነበረ ድፍን የአካባቢው ነዋሪ የሚመሰክረው ሐቅ ነው።

ሌላው በራሴ የገጠመኝ አስገራሚ ነገር ደግሞ ምን መሰለህ እኔም ሆንኩ ሌሎች ወንድሞቼ ሱባዔ ይዘን ነበር እዚሁ። ታዲያ ምን ሆነ መሰለህ በሱባኤው (በጾምና ጸሎት) ላይ እያለን የሆነ ድምፅ በጆሮዬ በኩል መጥቶ ፥ «ለምንድነው ዝም ብላችሁ የምትቀመጡት? ያለዕረፍት አቡነ ዘበሰማያት ድገሙ፤ እግዚአ መሐረን ክርስቶስ በሉ» አለኝ። ይህን ድምፅ ከሰማሁ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ወልደ ገብርኤል ወደ እኔ ዘንድ መጥቶ፥ «አሁን የተነገረህ ነገር ምንድር ነው?» ብሎ ሲጠይቀኝ የባሰ ገረመኝ። የተነገረኝን ነገርኩት። ወዲያውም ጸሎት ያዝን።

ሌላው አስገራሚ ነገር መምሬ ወርቁ የተባሉት ካህን የነገሩን ነው። የመጡት ከመኑካ ነው። ይገርምሃል ቅዱስ ገብርኤል በራእይ ታይቷቸው ከዚህ ቦታ ተነሥተህ እኔ ወደምመራህ ቦታ ልብሰ ተክህኖ (ካባ) ልበስና ፍም አፍመህ (የዕጣን ማጠኛ) ሂድ ብሏቸው የሦስት ሰዓት ጉዞ የሆነውን መንገድ ተጉዘው እዚህ እስኪደርሱ ድረስ አንድ ጊዜ ያፋሙት ፍም ሳይጠፋ ደርሰው በዋሻው ውስጥ አጥነዋል። ኪዳን እንዲያደርሱም ተነግሯቸው ስለነበር አብረን ኪዳን አድርሰናል።

ዳሩ ግን ይኸን ሁሉ ባይም ጥርጥር ግን በልቡናዬ ነበረ። ጥርጣሬዬን ሊያስወግድልኝ ነው መሰለኝ እኔና መምሬ ወርቁ አንድ ዓይነት ራእይ በአንድ ጊዜ አየን። ራእዩ ምን መሰለህ መጀመሪያ ቄሱን የሆነ ሰው ይቀሰቅሳቸውና «እምሥራቀ ፀሐይ» የሚለውን ምስባክ በሉ ይላቸዋል። እኔን ደግሞ ይቀሰቅሰኝና «እግዚአብሔርሰ ገሐደ ይመጽእ» የሚለውን ስበክ ይለኛል። ሁለታችንም ያየነውን ተነሥተን ተነጋገርን፤ ተገርመንም እንደተኛን ሸለብ እንደ አደረገን ሚካኤልና ገብርኤል የዕብነ በረድ ጽላት ሲያሳዩን አየን። ወዲያው ደግሞ አቶ ወልደ ገብርኤል መጥቶ ያየነውን ሲጠይቀን ነገርነው።

ሐመር — ከዚህ ሌላ በገሐድ ያየኸው ነገር አለ?

ዘሪሁን — በዋሻው አካባቢ ልዩ የሆነ መዓዛ ያለው የዕጣን ሽታ ያውዳል። ጥር 10 ቀን 1984 ዓ.ም. ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ እዚያ ዳስ ከተጣለበት (በእጁ እየጠቆመኝ) የዋሻው መግቢያ ላይ ትናንሽ የብርሃን መስቀሎች ወርደው መታየታቸውን ብዙ ሰዎች ነገሩን። ነገር ግን እኔና አንድ መስፍን መርጊያ የተባለ ልጅ ስላላየን በጣም አዝነን ለአቶ ወልደ ገብርኤል ነገርነው። እርሱም ኑ እንጸልይ ብሎን ስንጸልይ በዚያኑ ቀን በዋሻው ትክክል የብርሃን መስቀል አየን። እንዲሁም የቀለጠ ማኅሌት በዋሻው ውስጥ ሰምቻለሁ።

ሐመር — ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ወደዋሻው ውስጥ ገብተው ከወጡ በኋላ የተናገሩት ምን ነበር?

ዘሪሁን — መጀመሪያ ጥር 15 ቀን 1984 ዓ.ም. ለጥር 16 አጥቢያ አባ ኀሩይና አባ ምሥጢሩ የተባሉት ሁለት መነኮሳት መጥተው ወደ ዋሻው ገብተው ለማየት ሲሞክሩ ከዋሻው ውስጥ የሚወጣው የእሳት ወላፈን



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

አላስገባ ሲላቸው እኛ አሁን ምግብ በልተናልና መግባት አይቻለንም፤ ነገ በጠዋት መጥተን እንገባለን ብለው ሄዱ። በማግሥቱ ጠዋት መጥተው ወደዋሻው በመግባት በዋሻው ውስጥ ታቦት መኖሩን አረጋግጠዋል። ለብፁዕነታቸውም ሄደው ተናግ ረዋል። ብፁዕ አባታችንም የካቲት 5 ቀን 1984 ዓ.ም. ራሳቸው መጥተው በዋሻው ውስጥ ታቦት መኖሩን አይተው ይህንኑ ለአካባቢው ሕዝብ አረጋግጠው የቦታውንም ታላቅነት አብሥረው ከዐቢይ ጾም በኋላ እራሳ ቸው መጥተው ታቦታቱን እንደሚ ያወጡ ተናግረው ነበር።

ከወረዳው ጸሐፊ ከአቶ መስፍን ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ

ሐመር :- አቶ መስፍን ነዋሪነትዎ በየት ነው?

አቶ መስፍን:- በዚህ ክልል ነው።

ሐመር — ሠራተኛ ነዎት?

አቶ መስፍን — የወረዳው ጸሐፊ ነኝ።

ሐመር — በቦረዳ ስላለው ዋሻና በውስጡ አሉ ስለሚባሉት ጽላት ምን ያህል ክትትል አድርገዋል?

አቶ መስፍን — በመጀመሪያ ወሬውን በሰማሁ ጊዜ በጣም ከመደነቁ የተነሣ ለማመንም አስቸግሮኝ ነበር። የነገሩን እውነታነት ለማረጋገጥ ወደዚህ ቦታ መጣሁ። በእርግጥም የሚያስደንቅ ቦታ ሆኖ አገኘሁት።

ሐመር — በቦታው ያዩት አስደናቂ ነገር ምን ነበር?

አቶ መስፍን — በዚህ ዋሻ አካባቢ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳለበት ልረዳ ችያለሁ። እንደዚሁም በዋሻው ውስጥ የቅዳሴ፥ የከበሮ ድምፅ ይሰማል። ልዩ የሆነ የዕጣን መዓዛ ከዋሻው ዙሪያ በመውጣት አካባቢ ውን ያውዳል። በዋሻው ዙሪያ አስደናቂ ብርሃን አይቻለሁ።

እንዲሁም ደግሞ የሥላሴ ጽላት አለበት በተባለበት ዋሻ ውስጥ የሰው እጅ ገብቶ ሊጽፍ በማይችልበት ቦታ ሰው ሆን ብሎ ጽፎት ነው ሊባል በማይችልበት ሁኔታ «ኢየሱስ ጌታ ነው» የሚል ጽሑፍ አንብቤያለሁ።

ሐመር — አቶ ወ/ገብርኤልን ያውቁአቸዋል?

አቶ መስፍን — አዎን አውቃ ቸዋለሁ።



የቅዱስ ሚካኤል ጠበል



አቶ መስፍን

ሐመር — ከበፊቱ ምን ያህል ተለውጠውበዎታል?

አቶ መስፍን — ከፍተኛ ለውጥ አይቼባቸዋለሁ፤ በፊት ሳውቃቸው ከጋሙኛ በስተቀር አማርኛም ሆነ ግዕዝ መናገር አይችሉም ነበር። ያልተማሩ ማይም ነበሩ። ዳሩ ግን ዋሻው ውስጥ ገብተው ከወጡ በኋላ በዋሻው ውስጥ ያሉ ቅዱሳን አስተማሩኝ ብለው አማርኛ ማንበብም ሆነ መናገር ግእዝ ማንበብ ሲጀምሩ በጣም ነው የደነቀኝ፤ እንቆቅልሽም ነው የሆነብኝ። በፊት የማውቃቸው ሰው አልመስልህ አሉኝ። እኔ በፊት ይኼን ያህል ነበርኩ (ለሃይማኖት) ይህን ሁሉ አስገራሚ ነገር ካየሁ በኋላ ግን ከዚያ ከዋሻው የማልለይ ሆንኩ፤ አዲስ አበባ ድረስ አብሬያቸው ሔጂያለሁ። ከዋሻው ውስጥ ያሉት ጽላት እንዲወጡ ለቤ/ክህነት ለማሳወቅ።

ሐመር — አቶ መስፍን በአንባ ቢያን ስም ሳናመሰግንዎት አናልፍም።

ከአዘጋጁ — የተከበራችሁ አንባ ቢያን የቦረዳው ተአምራት በዚህ የሚያበቃ አይደለምና በሚቀጥለው ታሪክ ለመገናኘት እግዚአብሔር ያብቃን። ✣



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# የሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም

ከአለፈው የቀጠለ

የዛሬው የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የካህናት ማሠልጠኛ የሚገኝበት ሥፍራ ቀደም ሲል በደን የተሸፈነ እንደነበረ ይነገርለታል። እስከ 1958 ዓ.ም. ድረስም የመንግሥት ንብረት ሆኖ የቆየ ሲሆን ከዚህ በኋላ ግን በቤተ ክርስቲያኒቱ ጥያቄ ለቤተክርስቲያን ተሰጠ። በአካባቢውም ከጥቂት የክርስትና እምነት ተከታዮች በቀር ብዙ ክርስቲያኖች የሌሉበት እንደ ነበረ ይነገራል። ቦታውን ቤተክርስቲያን ከተረከበችው በኋላ ሁለተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የካህናት ማሠልጠኛ እንዲቋቋምበት ወስነው ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ጋር በመመካከርና ድጋፍም በማግኘታቸው በ1959 ዓ.ም. በቅዱስነታቸው መልካም ፈቃድ የትምህርት ቤቱና የተማሪዎቹ የመኖሪያ ሕንፃ ሥራ እንዲጀመር ሆነ። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማለትም በ1960 ዓ.ም. ሥራው ተጠናቆ ወዲያው ለአራት ዓመታት በዲፕሎማ የሚያስመርቀው የዝዋይ የካህናት ማሰልጠኛ «የዝዋይ የካህናት ማሠልጠኛ» በሚል ስያሜ ተግባሩን ማከናወን ጀመረ። በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የማሠልጠኛው ተማሪዎች በአብዛኛው ከሰሜን ኢትዮጵያ የመጡ ካህናት እንደነበሩና መምህራኑ ደግሞ ከቀድሞው የግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ከአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በቲዎሎጂ የተመረቁ እንደነበሩ ታሪክ ያስረዳል። በዚያን ጊዜ በማሠልጠኛው ውስጥ ከሚሰጡት ትምህርቶች መካከል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ የቤተክርስቲያን ታሪክ፥ ነገረ ሃይማኖት፥ ሳይንስ፥ ጂኦግራፊ ይገኙባቸዋል። በዚህ መልኩ ማሠልጠን የጀመረው ማሠልጠኛ በ1966 ዓ.ም. ችግር እስከገጠመው ድረስ ብዙ ምሩቃንን አውጥቶ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት አብቅቷል።


የገዳሙ ተማሪዎችና አበው የመኖሪያና የመመገቢያ ሕንፃ

ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ የዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛ በወቅቱ በነበረው መንግሥት ለታወጀው የዕድገት በኅብረት ዘመቻ ዋና ማዕከል ከመሆኑም ሌላ በውስጡም የመሠረተ ትምህርት ይሰጥበት ነበር። ቀድሞ በማሠልጠኛው ውስጥ ይሰጥ የነበረው መንፈሳዊ ትምህርት እንዲቋረጥና ተማሪዎችና መምህራኑም እንዲባረሩ ተደረገ። በዚህ መልኩ የተዘጋው ማሠልጠኛ መንፈሳዊነቱ ቀርቶ ሥጋዊ፥ የእግዚአብሔር ቃልና ነገረ ቤተክርስቲያን ቀርቶ ፖለቲካና የክህደት ትምህርት ይሰጥበት ጀመር።

ይሁን እንጂ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ከተሾሙ በኋላ ማሠልጠኛው እንደገና ለቤተክርስቲያን እንዲመለስ በመጠየቃቸውና ጥያቄአቸውም በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ጭምር ድጋፍ በማግኘቱ ሥፍራውን ለተለያዩ ጉዳዮች ይፈልጉት ከነበሩት ልዩ ልዩ የመንግሥት ነክ መሥሪያ ቤቶች ጋር በመደራደር ፈቃድ በማግኘታቸው በተጠናከረ መልኩ ቀድሞ ይሰጥ የነበረውን ግልጋሎት እንዲያበረክት አስችለውታል። ይህም በ1971 ዓ.ም. ሐምሌ ወር ነው።

ይሁን እንጂ ማሠልጠኛው በውስጡ ቤተክርስቲያንና የቤተክርስቲያን አገልግሎት ጭምር (ለምሳሌ ቅዳሴ፥ ክርስትና፥ ወዘተ.) ያልነበረበት በመሆኑ መንፈሳዊውን ትምህርት በተግባር ለመፈተን አስቸጋሪ ስለሆነ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በ1974 ዓ.ም. ቤተክርስቲያን እንዲሠራና የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጥበት አድርገው ማሠልጠኛውን በመንፈሳዊ በኩል በንድፈ ሃሳብና በተግባር የተዋሐደ ትምህርት እንዲሰጥበት አድርገዋል። ከዚህ ከቤተክርስቲያኑ መሠራት ጋር አብሮ የቅዱስ ገብርኤል ጽላት በመግባቱ ማሠልጠኛው ከቀድሞ ስሙ «የሐመረ–ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የካህናት ማሠልጠኛ እንዲባል ሆነ። በዚህም መሠረት እንደገዳምነቱ በገዳም ሥርዓት ይመራል። የንግህና የሠርክ የማሕበር ጸሎት፥ የማኅበር ማዕድ፥ የማኅበር ሥራዎች ይከናወኑበታል። በማሠልጠኛነቱ ደግሞ ቀድሞ ይሰጡ ከነበሩት ትምህርቶች



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

በተጨማሪ ጥንታውያኑ የወንበር ትምህርቶች ማለት የአብነት ትምህርቶች ከመጻሕፍት ትርጓሜ በቀር በሙሉ ይሰጣሉ። እነዚህ ባለፈው እትማችን በጨረፍታ ልንነግራችሁ እንደሞከርነው ሁሉ የጥንቱን የቤተክርስቲያናችንን የትምህርት አሰጣጥ ትውፊት በነበረበት መልኩ በማቆየት ተማሪዎች የአባቶቻቸውን የማስተማሪያ ጥበብ በመውረስ ተምረው አልፈውበት የበለጠም እንዲወዱት እንዲጠብቁትም በማስቻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው። በቀድሞው ሥርዓትና ልማድ ከሚሰጡት ትምህርቶች መካከል ቅኔ፥ ዜማ፥ ቅዳሴ፥ ድጓ፥ ጾመድጓ፥ አቋቋም፥ የቃል ትምህርቶች (ውዳሴ ማርያም፥ መልክአ ማርያምና መልክአ ኢየሱስ)፥ ሰዓታትና ሌሎችም ሲሆኑ፥ በዘመናዊው መልክ ደግሞ በማሠልጠኛው ውስጥ ከሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች መካከል ትምህርተ ሃይማኖት፥ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን፥ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ፥ የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ ኦርቶዶክሳዊ የስብከት ዘዴ፥ ኦርቶዶክሳዊ መዝሙሮች፥ ሥርዓተ ጸሎት፥ ክብረ ቅዱሳን፥ የእርሻ ትምህርትና የሒሳብ ትምህርት ዋነኞዎቹ ናቸው።



የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በስተ ምዕራብ

በገዳሙና በማሠልጠኛው ውስጥ ሥልጠናውን ለመካፈል ከሚመጡት ኮርሰኞች በተጨማሪ እዚያው በአዳሪነት የሚማሩ ተማሪዎች አሉ። እነዚህ በአካባቢው ካሉት ረዳትና አሳዳጊ የሌላቸውና አጓለማውታ ልጆች መካከል ናቸው። ኮርስ ከሚወስዱትም የእነዚህ የአዳሪዎቹ ቁጥር ይበዛል። በወቅቱ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ከተለያዩ የውጭ ድርጅቶች የምግብና የልብስ ዕርዳታ በመለመንና ለኮርሰኞቹ ቤተክርስቲያን ከምትመድበው በጀት በማብቃቃት እንዲሁም ደግሞ ቤተክርስቲያኒቱ ከምታደርገው ድጋፍ በሚያገኙት ነገር እነዚህን ሕፃናት በማሳደግና በማሰልጠኛው እየተማሩ እንዲቆዩ በማድረግ ከተለያዩ የእምነት ድርጅቶች ወጥተው በክርስትና እንዲያምኑና እንዲጠመቁ በማብቃት ለቤተክርስቲያን አገልጋዮች እንዲያፈራ አድርገውታል። በማሠልጠኛው የሚሠጡትን የአብነት ትምህርቶች በአብዛኛው የሚማሩትም እነዚሁ ከአካባቢው የተገኙ ወጣቶችና ሕፃናት ናቸው።

በገዳሙና በማሠልጠኛው ውስጥ ከፍ ብሎ ከጠቀስናቸው መንፈሳዊ ትምህርቶች በተጨማሪ በቃል የሚሰጠው የእርሻ ትምህርት በተግባር የሚገለጥበት ሰፊ የጓሮ አትክልት መስክ አለ። ባለፈው እትም በዝርዝር ያቀረብናቸው የገዳሙ ዕፀዋት ሁሉ ዘወትር ከ9:00–12:00 ሰዓት በሚደረገው የመስክ ሥራ በኮርሰኞችና በገዳሙ አዳሪ ተማሪዎች ድካም የተገኙ የሥራ ውጤት ናቸው። ከዚህ አንፃር ከሌሎች የቤተክርስቲያኒቱ የካህናት ማሠልጠኛዎች መካከል በምሳሌነቱ የሚጠቀሰውና ተወዳጅ የሆነው ይህ ገዳምና ማሠልጠኛ ከዚህ ሌላ ዘወትር በጸሎት ሰዓት በሠርክ በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚሰጠው ተግባራዊ የስብከት ትምህርት በቃለ ወንጌል የተጠሙ ነፍሳትንና የጎሰቆለች ሕይወትን በእጅጉ የሚለውጥ በመሆኑ ማሰልጠኛውንና ገዳሙን በሚያውቁት ሁሉ ዘንድ የተለየ




የድጓ ተማሪዎች በቅጸላ ላይ እንዳሉ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ትዝታ እንዲኖረው አድርጓል። ከሁሉም በላይ የገዳሙና የማሠልጠኛው ሕግ ፍቅርና አንድነት በመሆኑ ከኮርሰኛም ሆነ ከአዳሪ ተማሪዎች መካከል የተጣሉ ቢኖሩ ወዲያው የሚታረቁ ስለሆነ ባይታረቁም ስለሚባረሩ ፀብ በገዳሙና በማሰልጠኛው ውስጥ የተጠላ ነው። የገዳሙና የማሠልጠኛው አባላት የሆኑ አበው መነኮሳት ከአበምኔቱ ጀምሮ እስከ ሕፃኑ ድረስ ለሰው ያላቸው አክብሮትና ፍቅር በእርግጥ የወንጌል ተማሪዎች መሆናቸውን ከማረጋገጡም በተጨማሪ ወንጌልን



የገዳሙ የእንግዶች ማረፊያ ጽርሐ–ጽዮን

በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ለመማር የሚያስችል ስለሆነ ወደ ማሠልጠኛው በገቡትም ሆነ በበዓላት ገዳሙን ለመጎብኘት ዕድል በአጋጣማቸው ሰዎች ሁሉ ዘንድ የማይረሳ ትውስታ አለው።

ለተመልካች የሚያስደንቀው ሌላው ነገር ዕድሜአቸው ከ10 ዓመት የማይበልጡ ሕፃናት መጽሐፍ ቅዱስን በቃላቸው አጥንተው እጆቻቸውን አጣጥፈው በመቆም አንድ አንቀጽ አንብበው በአማረ ሁኔታ ልቡናን የሚሰብርና ሕይወትን የሚለውጥ ትምህርተ ወንጌል ሲያሰሙ ማየት ነው። በገዳሙና በማሠልጠኛው ክብረ በዓል በሚሆን ጊዜ የዕለቱን ወረብ የሚያቀርቡት እንደተለመደው ሁሉ አበው ካህናት አይደሉም። እጅግ በሚያምር ቅላጼና በተዋበ አቀራረብ ለዓይን የሚማርክ ልጅሮ የሚጥም አድርገው የሚያዘጋጁት እነዚሁ ሕፃናት ናቸው።

ማሠልጠኛው ኮርሰኞችን በሚያስመርቅባቸው ጊዜያት በሥነ–በዓሉ ላይ እነዚህ ሕፃናት የቤተ ክርስቲያናችን ድንቅ ሀብት የሆነውን ቅኔ በቃለ እግዚአብሔር በሰላ አንደበትና በስብሐተ እግዚአብሔር በለዘበው ማንነታቸው ያለማቋረጥ ሲያዘንሙት መመልከት ሌላው ግሩም ነገር ነው። ያን ጊዜ በቤተክርስቲያናችን እንኮራለን። ተስፋችንም ጽኑዕ ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ በገዳሙና በማሠልጠኛው ውስጥ በቋሚ መምህርነት የሚያገለግሉት መምህራን የራሱ የገዳሙና የማሠልጠኛው ውጤት መሆናቸው ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው።

በገዳሙ ውስጥ ከእነዚህ ሕፃናትና ዲያቆናት ወጣቶች በተጨማሪ በተለ የሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም

ከአለፈው የቀጠለያዩ የዕድሜ ደረጃ የሚገኙ አበው መነኮሳት አሉ። እነዚህ ደግሞ የገዳሙ የሕይወትና የመልካም ውጤት ምስክሮች ናቸው። ለገዳሙ እንግዳ ሆኖ ለሚሄድና ቤተሰብ ለሆነም ቢሆን ያላቸው ፍጹም ክርስቲያናዊና አባታዊ ፍቅር ከገዳሙ ውጡ ውጡ የማያሰኝና የራሱ የሆነ የተለየ ግምት የሚሠጠው ነው። ከሕይወት አንፃር እንደቀደምት ገዳማት ሁሉ በፍቅር የታጠረ በመሆኑ ክፉ ነገር አይሰማበትም። እንደዘመናውያን ደግሞ በማንኛውም ነገር የተሟላ የራሱ ወፍጮ፣ ስልክ፣ የእንግዳ መቀበያ ከነሙሉ ድርጅቱ፣ የተሟላ የኤሌክትሪክ አገልግሎትና ሁለት መኪናዎች ያሉት መሆኑ ሲታይ ገዳሙና ማሠልጠኛውን የበለጠ እንዲታወቅ እያደረገው ነው።

በተለይ ደግሞ በትንሣኤና በልደት ሌሊት ከቅዳሴ በኋላ በገዳሙ የምግብ አዳራሽ ከትንሹ እስከ ሊቀ ጳጳሱ ድረስ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው በጋራ የጋራ ቋንቋቸው የሆነውን ስብሐተ እግዚአብሔር በመዝሙር ሲያቀርቡ ከማዕድ በኋላ ደግሞ ተመሳሳይ ምስጋና ቀርቦ በፍቅር ሲበላ፣ ሌላው እኔ ካላስተናገድኩ ሲል ያለውን እሽቅድምድም ከመመልከት በተጨማሪ ደግሞ ጠላውን ሲጠምቁ፣ ዳቦውን ሲደፉ፣ በተለይ ደግሞ የገዳሙን ዳቤ የሚያዘጋጁት እነዚህ አባቶችና ወንድሞች መሆናቸውን ማየት፣ ከፍቅርና ከአንድነት ማዕድ መሳተፍ የሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤልን ገዳም አያስረሳም።

ይህ ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛ ከ1980 ዓ.ም. ጀምሮ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ ከዩኒቨርሲቲና ኮሌጆች የተውጣጡ ተማሪዎችን በማሠልጠን በዕውቀታቸው የቤተ ክርስቲያኒቱን የትምህርተ ወንጌል አገልግሎት እንዲያግዙ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። በማድረግም ላይ ይገኛል። በዚሁ መሠረት በአጠቃላይ አንድ መቶ አስራ አምስት (115) የዩኒቨርስቲና ኮሌጅ ተማሪዎችን እንዲሁም ከሁለት ሺህ (2000) በላይ የሚሆኑ በማሠልጠኛው የሚሰጠውን የሦስት ወራት ኮርስ የወሰዱ ካህናትና ወጣቶችን በማሠልጠን ከፍተኛውን የትምህርት ወንጌል ልኡካን ቁጥር ለቤተ ክርስቲያኒቱ አበርክቷል።

የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛ ብሔራዊ ብቻ ሳትሆን ዓለም አቀፋዊ የካህናት ማሠልጠኛም ናት። ይህን



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ንም ውጤቶቿ በተግባር ይመስክራሉ። ታላቁ አባት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እግዚአብሔር መሣሪያ በማድረግ በዚህች ገዳምና ካህናት ማሠልጠኛ ሦስት እንግሊዛውያንን በማሠልጠንና በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ አንብሮተ እድ የቅስና ማዕረግ በማሰጠት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓትና ትውፊት በለንደን በደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንና በተለያዩ አካባቢዎች በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ። ከዚሁ ጋር ዛሬም ቢሆን በቤተክርስቲያናችን ይህ መልካም ጅምር ትኩረት ተሰጥቶት የሚቀጥልበት ሁኔታ እንደሚመቻች ተስፋችን ነው።

ከዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የካህናት ማሠልጠኛ የሚወጡት ደቀመዛሙርት ዛሬ በሀገራችን እንግዳ ትምህርት በማስተማር ምእመናንን ለሚያስቸግሩ መናፍቃን ፍቱን መድኀኒት ሆነው በመገኘታቸው ቅድስት ቤተክርስቲያናችንም በተለይ በክረምት በገዳሙና በማሠልጠኛው ለሚደረገው የዩኒቨርሲቲና የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ሥልጠና የበለጠ ትኩረት እንደምትሰጠው ነሐሴ 30 ቀን 1984 ዓ.ም. በገዳሙ በነበረው የምርቃት በዓል ላይ በቅዱስነታቸው የተገለጠ መሆኑን በማስታወስ ለወደፊቱ የገዳሙንና የማሠልጠኛውን የተሻሻለና የአማረ ገጽታ እንደምናይ እናምናለን።

ሌላው በገዳሙ የተተከሉት የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬ ገዳሙን በምጣኔ ሀብት የሚያግዙ በመሆናቸው ሌሎች ማሠልጠኛዎች በምሳሌነቱ እንዲጠቀሙ ያደርገታል። ብዙ አይሁን እንጂ ከእነዚህ አትክልት ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ገዳሙን ካሉበት ችግሮች አንዱን እንኳ እንዲሸፍን የሚረዳው መሆኑ ግልፅ ነው። ስለእነዚህ ዕፀዋት ሲነሣ የማይረሳ አንድ ታሪክ አለ። በገዳሙ ውስጥ ከተተከሉት ዕፀዋት ለምሳሌ ከሙዝ፥ ከፓፓዩውና ከብርቱካኑ ፍሬ መሬት የወደቀ ማንሣት ወይም ያለፍቃድ ቀጥፎ መመገብ በእጅጉ የተከለከለ ስለሆነ አትክልቱ «በለስ» የሚል መጠሪያ አላቸው። ይህ መባሉ ያለ ምክንያት አይደለም፤ የገዳሙን ደንብ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው በገዳሙ ቀኖና መሠረት የሚቀጣ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ሁሉም ሰው ለገዳሙ ሕግ የተገዛ ነው። ከዚህ አስጊ ነው። ከዚህም ሌላ በአካባቢው በየዓመቱ የሚነሣ የወባ ወረርሽኝ በመኖሩ ገዳሙ በጤና ጥበቃ በኩል ችግር አለበት።

ስለዚህ ከሚያፈራው ፍሬና ለቤተ ክርስቲያናችን ከሚሰጠው አገልግሎት አንፃር የበለጠ ሊተኮርበት የሚገባ ነው በማለት እንጠቁማለን።



ተማሪዎች በምግብ አዳራሹ የአንድነት ማዕድ ሲሳተፉ

የተነሣ መወነጃጀልና መካሰስ በአጠቃላይ መለያየትና አለመግባባት የለም።

ከዚህ ጋር አያይዛ ሐመር የምትለው ነገር አላት። በዝዋይ ሐይቅ የተከበበው ይህ የሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም በዙሪያው እጅግ ታሪካዊ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ባሉባቸው ደሴቶች የሚጐራበት በመሆኑ በውስጡ የተሟላ አደረጃጀት ቢኖረውና የተማሪዎቹ መኖሪያም ሆነ መማሪያ የተሟላ ቢሆን እነዚህን ድንቅ የቤተ ክርስቲያናችን ሀብቶች ለመጎብኘት ለሚመጡ ጎብኚዎች ማረፊያ ከመሆኑም ሌላ ተወዳጅነቱን ከአሁን በበለጠ ያሳድግለት ነበር። ምንም እንኳ ከሌሎች ማሰልጠኛዎች አንፃር የተሻለ ነው ቢባልም በተለይ ተማሪዎቹ የሚኖሩበት ቤት የመኝታ አልጋ የሌለው በመሆኑና ሕንፃው በ1959 ዓ.ም. የተሠራ የብሎኬት እንደመሆኑ ለተባይ መራቢያ ምቹ እንዲሆን አድርጎታል። ይህም ለአዳሪ ተማሪዎችም ሆነ ለኮርሰኞች ጤንነት

በአጠቃላይ ፍጹም ነው ባይባልም በውስጡ የሚሰጠው ትምህርት፥ የሚታየው ፍጹም እውነተኛ የክርስትና ሕይወት እንዲሁም ደግሞ አደረጃጀቱና አሠራሩ ለቤተ ክርስቲያናችን አለኝታ መሆኑን ያረጋግጥልታል። ለዚህ ነው በአሁኑ ጊዜ በእጅጉ ተወዳጅ ሊሆን የቻለው። ከዚህ አንፃር ሌሎቹም ማሠልጠኛዎቻችን ይህንን አብነት አድርገው በሚያፈሩት ፍሬና በሚያሳዩት የሥራ ውጤት የበለጠ ሊጠናከሩ ይገባል እንላለን። በዚሁ ስለ ዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ያዘጋጀነውን ስንፈጽም እግዚአብሔር ፈቅዶ በሌላ ዝግጅት እንደምንገናኝ ተስፋ በማድረግ ነው።

ወለእግዚአብሔር ስብሐት

አሜን ✣



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

በዚህ ዓምድ ክርስቲያኖች በማኅበራዊ ኑሮአችን ልንመስል የሚገባንን፥ በኅብረተሰብ መካከል አገላለጣችን ምን መሆን እንዳለበትና የኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ኑሮ በምን ላይ ተመሥርቶ የሚመራ ሊሆን እንደሚገባው ለማውሳት ይሞከራል።

## ቅዱስ ጋብቻ

ከዲ. ደጀኔ ሽፈራው

በዓለማችን የተለያዩ አስደናቂ፥ አስደሳችና አሳዛኝ ታሪክ የሚነገርላቸው ታላላቅ ሰዎች አሉ። በአንፃሩ ደግሞ ማንም የማያስታውሳቸው እንኳን ታሪካቸው መፈጠራቸውም ከእግዚአብሔር በቀር በሰው ዘንድ የማይታወቅላቸው ሰዎችም አሉ። ሁሉም ግን ከጋብቻ የተገኙ ናቸው። ጋብቻ ደግሞ የሰው ዘር ምንጭ ከመሆኑም ሌላ የማኅበራዊ ኑሮ መሠረትም ነው። ክፉዎችም ደጎችም ይገኙበታል። በዚህ ጽሑፋችን የክርስቲያኖች ጋብቻ በማኅበራዊ ኑሮአቸው ውስጥ ሊኖረው ስለሚገባው ሥፍራና ሊመራበት ስለሚገባው አምላካዊ ሕግ (ሥርዓት) ለማውሳት እንወዳለን።

ጋብቻ ክቡር ቅዱስ ነው። የሚከብረውና የሚቀደሰውም በእግዚአብሔር ነው። ምናልባት ብዙዎች እንደተራ ነገር ወይም እንደ ልማድ ይቆጥሩት ይሆናል። ይህም አመለካከት በዕውቀት ማነስ ስለሆነ በተቻለን መጠን ለሕዝባችን ስለ ጋብቻ ክቡርነትና ቅዱስነት በእግዚአብሔር ቃል በቂ ግንዛቤ ማስጨበጥ አለብን። ይኸውም ንጽሕና የሚገባው ሰውነት በኃጢአት እንዳይቆሸሽ ቅድስና የሚገባው የሰው ልጅ በበደል እንዳይረክስ ነው።

ማንኛውም ሰው ስለ ጋብቻ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ቋሚ ሕግ ለማጥናት እንዲችልና ጋብቻ የፈቃድ መስሎት ሲያገባ፥ ሲፈታ፥ ሲዳራ እንዳይኖር ሰው ለራሱ ሲል በግድ ሊጠብቀው የሚገባ ስለጋብቻ ከእግዚአብሔር የተሰጠ የማይሻር ሕግ መኖሩን መረዳት አለበት።

ጋብቻ የተጀመረው ዓለምን በፈጠረ በራሱ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ጥርጥር የለውም። «እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ... ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው። ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሉአት» ዘፍጥ.1፥22። በዚህ ዓይነት ጋብቻችን የተባረከ እንደሆነ የበረከተ ሥጋ የበረከተ ነፍስ ጌቶች እንሆናለን «የሹመት ትርፉ ወዳጅ የጋብቻ ትርፉ ልጅ» እንዳሉት አበው በመብዛታችንም ብዙ አንጨነቅም። በዛሬዋ ዓለማችን የሰው ዘር መብዛትና ምድርን መሙላት ለብዙዎች ራስ ምታት ሆኖባቸዋል። እንደ ጌታ ቃል የሰማይ ወፎችን የሜዳ አበቦችንም መመልከት ተስኖአቸው ስለሚበሉት ስለሚጠጡትና ስለሚለብሱት ስለሚጨነቁ ነው።

በአንድ ቤተሰብ መካከል ቢሆንም የቁጥር መጨመር ትልቅ ሥጋት እየሆነ ከመጣ ውሎ አድሯል፤ እንዲያውም በማኅፀን ያለን ነፍስ በተለያየ ዘዴ ማስወገድ እንደ ጽድቅ የታየ ይመስላል። ኃጢአቱ ጽድቅ ሐሰቱ እውነት ከሆነ ማለት ነው። ያም ሆነ ይህ በሰዎች ስጋትና ጭንቀት ትውልዱን ከመብዛት መግታት አልተቻለም። በፈቃደ እግዚአብሔር ላይ ያልተመሐረተና በእግዚአብሔር ያልተባረከ ጋብቻ መዘዙ ብዙ ነው። በዚህ ያልቆሰለና በደዌው ያልተለከፈ ቢኖር በጣም ጥቂት ነው።

የሰው ተፈጥሮ ክቡር ስለሆነ በተሰጠው አስተዋይ አእምሮ ማንነቱን ተረድቶ በተግባሩ ከክብሩ እንዳይዋረድ፥ ከንጽሕናው እንዳይቆሸሽ፥ ከቅድስናው እንዳይረክስ መጠንቀቅ አለበት። እግዚአብሔር ፍጥረትን መፍጠር በጀመረ በስድስተኛው ቀን አዳምን ከሁሉ አክብሮ ፈጥሮ ከሰማይ በታች ላለው ፍጥረት በጸጋ ገዥ አድርጎ አነገሠው። መላእክትን የሚመስልባትንም ባህርይ አድሎታል። ይህም ማለት ረቂቅ አድርጎ እምኀበ አልቦ ፈጠረው ማለት አይደለም።

መላእክት ይህን ሥሩ ይህን አትሥሩ የሚል ሕግ ሳይጻፍላቸው በተፈጥሮ በተሰጣቸው ዕውቀት እግዚአብሔርን ፈርተው አምልኮቱን አጽንተው ክፉና በጎውን ለይተው ከክፉ ተጠብቀው በጎውን ሠርተው ስሙን እየቀደሱ ክብሩን እንዲወርሱ እንደተፈጠሩ ሁሉ ሰውም በዚህ ሥርዓት በሕገ ልቡና እንዲኖር ዐዋቂ ሆኖ ተፈጠረ ማለት ነው። ዕብ. 1፥11። በዚህ መመራት ተስኖት ቢበድል ሕገ ኦሪትም ሕገ ወንጌልም በየተራ ተሠራለት።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

መታመም፥ መሞት፥ መፍረስ፥ መበስበስ ከሚሰማማው ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ (ከእሳት ከነፋስ፥ ከውሃ፥ ከመሬት) እና ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ (ከለባዊት፥ ከነባቢት፥ ከሕያዊት) ማለት ከምታስብ ከምትናገርና ሕያዊት ከሆነች ነፍስ የተፈጠረ ሰው 1ኛ. በፍትወት እንዳይቸገር 2ኛ. ያለዘር እንዳይቀር 3ኛ. ብቻውን እንዳይሆንና እንድትረዳው እግዚአብሔር አምላክ ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራለት። ወደ አዳምም አመጣት፤ አካሉ በመሆኗም የቀደመው ሰው አዳም «ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል» አለ። ዘፍጥ.2፥22። እግረ መንገዳችንንም የሴትን ትርጓሜ ማስተዋሉ ይጠቅማል።

የአዳም ልጆች ሁሉ በዚህ ተመርተው ሚስቶቻቸውን እንደ አካላቸው በማየት ሊከባከቧቸው ይገባል። ይህም ሲሆን እንደ ሌላ ሁለተኛ አካል ሳይሆን እንደ ራስ አካል በመመልከት ነው። «ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» እንተደባለው። ወንድ ስለ እርሷ እናት አባቱን የተወላትን ሚስቱን እንደ ወላጆቹ አክብሮ መኖር አለበት። ሚስትም ስለእርሷ አባት እናቱን ትቶላታልና እንደ አባት እንደ እናቱ እንድ ትሆንለት ያስፈልጋል። እዚህ ላይ አባት እናትን መተው ማለት ጨርሶ መጣል አለመጦር ማለት አይደለም። የወላጆችን ቤትና ኑሮ ትቶ የራስን ጐጆ መቀለስና የራስን ኑሮ መመሥረት ከጥገኛነት ወጥቶ በራስ መተዳደር ማለት መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም። ዘፍጥ.2፥21።

ከሚስቱ ይተባበራል የሚለው በጋብቻ መዋሐድን፥ አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለው ደግሞ አንድ አካል መሆንን ያመለክታል። ዋናው ነገር ግን በዚህ ውሕደት መካከል እግዚአብሔር መኖር አለበት። ይሄኔ ነው ጋብቻው ወይም ውሕደቱ ክቡር ቅዱስ የሚሆነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊፈትኑት የመጡት ፈሪሳውያን «ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶአልን?» ባሉት ጊዜ በዘፍጥ.2፥24 የተጻፈውን ገልጦ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን እንግዲህ ሰው አይለየው» ሲል መልሶላቸዋል። ወንድ ከአንድነት በኋላ ከሳች ጠቆረች ታመመች ብሎ በጥቃቅን ምክንያቶች ሚስቱን መፍታት አልተፈቀደለትም። የባልና ሚስት ሥርዓት ፈቃደ እግዚአብሔር በመሆኑ እንደሥጋ ፈቃድ ሲፈቱ ሲያገቡ መኖር ሕገ እግዚአብሔርን ማፍረስ ነው። በጋብቻ ሁለቱ አካል ድንቅ በሆነ ምሥጢራዊ መንፈሳዊ ጥበብ አንድ አካል ይሆናሉ። እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ያጣመረውን መለያየት አንድን ሰው በስለታም ሠይፍ ለሁለት እንደ መክፈል ይቆጠራል። ማቴ.19፥5።

ምናልባት፥ «ሰው አይለየው» የሚለውን ንባብ ስንመለከት እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለየው ይችላል ወይ? የሚል ጥርጣሬ ሊያድርብን ይችላል። ይሁን እንጂ የራሳችንን ድካም አስወግደን በእምነት ጸንተን ጋብቻችንን በቅዱስ ቁርባን አትመን በጾምና በጸሎት አጥርነት የምንጠብቀው ከሆነ እርሱ ያዋሐደውን ሰው ሊለይ አይችልም። የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር ጸሎት ከጠበቀ አጥር ስለምትበልጥ በጸሎትና በሰጊድ መትጋት ነው።

ነቢዩ ሚልክያስም፥ «ሚስትህ ባልንጀራህና የቃል ኪዳንህ ሚስት ሆና ሳለች እርስዋን አታልለሃታልና እግዚአብሔር በአንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር ነው» በማለት ከቃል ኪዳን በኋላ ለሚፈጸመው ክህደታዊ የማታለል ርኩስታዊ ተግባር በውሕደቱ ጊዜ ስሙ የተጠራ እግዚአብሔር ስለነበረ ስሙ ምስክር እንደሚሆን ገልጧል። ይህም ማለት ሰው አላየኝም ብለው ጨለማን ለብሰው ጨለማን ተንተር ሰው የሚዋልጉ ሁሉ ከእግዚአብሔር መሰወር አይችሉም ማለት ነው። ሚል.2፥14። እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖች ፊት ሁሉ የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም ዕብ.4፥13። ልበ አምላክ የተባለ ዳዊትም በበኩሉ «የእግዚአብሔር ፊት ክፉን በሚያደርጉ ላይ ነው» ማለቱ በምንም ዓይነት ከእርሱ ፊት መሰወር እነደማይቻል ያረጋግጥልናል። መዝ.33፥16።

ወደ ሰማይ ብንወጣ፥ እጉድጓድ ብንገባ፥ ክንፍ አውጥተን ብንበር፥ ወደ ጥልቅ ባሕር ብንሰጥም ጨለማን ተገን ብናደርግ ጨለማ በእርሱ ዘንድ አይጨልምምና የትም መሰወር አንችልም። መዝ.138፥8። በመሆኑም ኪዳንን (ውልን) በመጠበቅ በእምነት ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ደስታን እንጐናጸፋለን። ያለእምነት ግን ሁለቱንም ማግኘት አይቻልም። ዕብ.16፥7 ትርፉ የሁለት ዓለም ስደተኛ መሆን ነው።

«ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል። መፋታትን እጠላለሁ ይላል የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር» ብሎ ነቢዩ ሚልክያስ እንደነገረን መንፈሳችንን በዝሙት ሳናረክስ እግዚአብሔር የጠላውን መፋታትን አርቀን ድንቅ በሆነው መንፈሳዊ ምሥጢር በአንድ አካልነታችን ጸንተን እንኑር።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ሚል.2፥16። የልጅነት ሚስትህን ሲል የመጀመሪያ ሚስትህን ማለቱ ነው እንጂ ሁሉ በልጅነቱ ያገባል ማለት አይደለም። በኤፌ.5፥36 ቅዱስ ጳውሎስ፥ «ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል። ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህም ምሥጢር ታላቅ ነው» በማለት አንድ የመሆንን ነገር ምሥጢር ብሎታል። ኤፌ.5፥31። ምሥጢር የሚለው ቃል ጽርአዊ ሲሆን ግእዝ መስሎ ከግእዝ ጋር አንድ ሆኖ ይገኛል። ትርጉሙም ጆሮን ከመስማት ዓይንን ከማየት አፍን ከመናገር መግታት መከልከል እንደማለት ሆኖ እናገኘዋለን። መከል ከልም ሲባል ፈጽሞ መከልከል ሳይሆን የሚከተለውን አስተያየት ይዞ ይገኛል።

ሀ. ምሥጢር ማለት በመሠረቱ ለባለቁርጥ ዘመድና ወዳጅ ብቻ የሚነገር ማንም ሊሰማው የማይገባ በወዳጆችም ዘንድ ተጠብቆ የሚቀር ለማንም የማይናኝ ነገር ማለት ነው።

ለ. ምሥጢር ማለት በእጅ የማይጨበጥና በዓይን የማይታይ በልብ ብቻ የሚመረመር ተመርምሮም የማይደረስበት በእምነት ብቻ የሚታይ በእምነት ብቻ የሚቀበሉት፥ የሚጨበጥ፥ ገንዘብም የሚሆን ረቂቅ ማለት ነው። የባልና የሚስትም አንድነት እንዲህ በመሆኑ ነው ቅዱስ ጳውሎስ ምሥጢር በማለት የደመደመው። ምሥጢር በልብ መጠበቅ እንዳለበት ምሥጢር የሆነ ጋብቻም በእምነት መጠበቅ አለበት። አደራ ለማንም አትንገር የተባለውን ምሥጢር ያወጣ በሰው ዘንድ እንደሚጠላ ምሥጢር የተባለ ጋብቻንም ያፈረሰ በእግዚአብሔር የተጠላ ነው።

ጋብቻ በአንድ ይጸናል እንጂ ሁለተኛ ቁጥርን አይነካም። ማለት ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት ለአንዲት ሴት አንድ ወንድ ነው እንጂ ለአንድ ወንድ ሁለት ሴት ለአንዲት ሴት ሁለት ወንድ አልተፈቀደም ባል ከሚስቱ ሚስት ከባሏ መተላለፍ የለባቸውም። ባል በሚስቱ ብቻ ሚስትም በባሏ ብቻ ተወስነው ይኖራሉ። «ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት» የሚል ተጻፈ እንጂ ሚስቶች ይኑሩት ባሎች ይኑራት የሚል አልተጻፈም። 1ቆሮ.7፥2። ለአዳም አንዲት ሔዋንን እንደፈጠረለት፤ ለሔዋንም አንድ አዳምን እንደፈጠረላት ዘፍጥ.2፥22 ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል እንጂ።

ወንድ ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ መጠበቅ ማድረግ ይገባዋል። ሴትም ለባሏ የሚገባውን መጠበቅ ማድረግ ይገባታል። 1ቆሮ. 7፥3። ከዚህ ውጭ የአንቺን አላውቅልሽም፥ የአንተን አላውቅልህም የእኔ ብቻ ይፈጸም የሚል አለመግባባት መከሰት የለበትም። ሁለቱም አንዱ ለሌላው የሚያደርገውን ለራሱ ለአካሉ እንዳደረገ ማመን አለባቸው።

ሴት ባሏ ያዘዛትን ልትፈጽም እንጂ በባሏ ላይ የሌላ ትእዛዝ ፈጻሚ ልትሆን የወደደችውን ልታደርግ በራሷ ላይ ሥልጣን የላትም። በእርሷ ላይ የማዘዝ ሙሉ ሥልጣን ያለው ባሏ ብቻ ነው። እንዲሁም ወንድ በሚስቱ ላይ የሌላይቱ ታዛዥ ሊሆን የሌላይቱን ፈቃድ ሊፈጽም በራሱ የማዘዝ ሥልጣን የለውም። በእርሱ ላይ ሙሉ ሥልጣን ያላት የምታዝዝበት ሚስቱ ናት። 1ቆሮ.7፥4። ስለ እኔ ምን አገባው፤ ምን አገባት ማለት ወደው የገቡትን ኪዳን አጥርና ቀለበት ለማፍረስና ለመስበር መነሳት ነው።

ለጾምና ለጸሎት ከተወሰነ ቦታና ጊዜ በቀር ባልና ሚስት መለያየት የለባቸውም። ሰይጣን ድል እንዳይነሳቸው ተጣባብቀው መኖር ይገባቸዋል። ባጠገባችን የምናየውንና የምናያትን ስናጣ በዙሪያችን የሚዞረው ባላጋራችን ዲያብሎስ መራራውን አጣፍጦ በምኞት ገመድ እየጐተተ ሊያሰናክለን ይችላል። 1ጴጥ.5፥8። አንድ ሰው ብልህ የሚባለው ደካማ ጐኑን ሲያውቅ ነው። እኛም ይኸንን ደካማ ጐናችንን እያወቅን እግዚአብሔር ይጠብቀኛል ማለት በራስ ፈቃድ ከፎቅ ላይ ብዘል እግዚአብሔር ያድነኛል ብሎ እንደ መቀለድ ነው። ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ቢገጥመን ግን ሣራን ከአቤሜሌክ እግዚእ ኀረያን (የተ/ሃይማኖትን እናት) ከሙቶሎሚ እጅ ያዳነ አምላክ እኛንም ይጠብቀናል። እስከዚያው፥ «ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ። ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ አብራችሁ ሁኑ» እንደተባለ በዚሁ ጸንተን መኖር ነው። 1ቆሮ.7፥5። አትከላከሉ ማለቱም ፈቃድ ፈጻሚዎች ሁኑ ማለት ነው። አለበለዚያ ወደ ሌላ የሚመራ ሰይጣናዊ መንፈስ ይቆራኘናል። ስለዚህ ሰይጣን ይህን ምክንያት አድርጎ በመካከል እንዳይገባ ብርቱ ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

ባል የክርስቶስ፥ ሚስት የቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው። ቤተክርስቲያን ለክረስቶስ እንደምትታዘዝ ሚስትም አሳዳሪዋ ስለሆነ ለባሏ መታዘዝ ይገባታል። እንዲሁም ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ራሱንም ለሞት አሳልፎ እንደሰጣት፥ ሥጋውን እንደመገባት እንዲሁም ወንድ አካሉ ናትና ሚስቱን መውደድ መርዳት መጠበቅ ይገባዋል። ኤፌ.5፥22። ሰው ለወደደው ይታዘዛል። የሚታዘዘውንም ይወዳል። ስለዚህ መታዘዝና መውደድ የማይነጣጠሉና የማይተናነሱ ናቸው። ጌታም በወንጌል: «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል። አባቴም ይወደዋል» ማለቱ ለዚህ ነው።



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ዮሐ.14፥23። ቃሌን ያለው ትእዛዙን ነው። እንግዲህ ሰው እግዚአብሔርን ካልወደደ ትእዛዙን መጠበቅ አይችልም። እግዚአብሔርም ትእዛዙን የማይጠብቀውን አይወደውም።

በዘመናችን እንደምናየው ለሴት በሥጋዊ ጌጥ ከማጌጥ ይልቅ ለባሏ በመታዘዝ ባሏን በመፍራት በመወደድ ጌታዬ እያለች በመጥራት ሳትፈራና ሳታፍር መልካም ሥራ በመሥራት ንጹሕ ልቡናዋን ገልጣ እያሳየች በትሕትናና በመንፈሳዊ ኃይል በመገዛት ብታጌጥ ይበልጥ ባታል። ከመግዛት ይልቅ መገዛት ይቀላልና። ለምሳሌ በዓለም ብዙ ነገር የምናየው ሰዎች ገዥነቱ ስለከበዳቸው ነው። ወንድም የምድር ሀብትና ክብር ብቻ ሳይሆን የሰማይ ሕይወትና ክብር ተሳታፊው ስለሆነች ሚስቱን ሳይንቅ እንደ ዓይን ብሌን መጠበቅ አለበት። 1ጴጥ.3፥1–7። ባልና ሚስት አንድ ልብ አንድ ቃል ሆነው በመተማመን መኖር ይገባቸዋል እንጂ በአሳብ መለያየት መተማማት የለባቸውም። ሣራ ለአብርሃም ጌታ ብላ እየጠራች ታዘዘችለት። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፥ «እናንተም ከሚያስደነግጥ ነገር አንዳች እንኳን ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ ልጆቿ ናችሁ» ባለው መሠረት ሴቶች ሣራን ወንዶች ደግሞ አብርሃምን ሆኖ መገኘት ነው። 1ጴጥ.3፥16።

ባልና ሚስት በሞት ካልሆነ በስተቀር መለያየት የለባቸውም። በሞት መለያየት ቢደርስባቸው ግን ወደኋላ የቀረው ንጽሕናውን ጠብቆ መኖር የማይቻለው ከሆነ ሁለተኛ በሕግ በሥጋወ ደሙ ማግባት ይችላል። «ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና ባልዋ ቢሞት ግን ለባል ከሆነው ሕግ ተፈትታለች። ስለዚህ ባልዋ በሕይወት ሳለ ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ ትባላለች። ባልዋ ቢሞት ግን ከሕጉ ዐርነት (ሐርነት) ወጥታለችና ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ አይደለችም። ሮሜ.7፥12።

ባልና ሚስት በልዩ ልዩ ምክንያት መፋታትና ቃል ኪዳናቸውን ማፍረስ አይገባቸውም። «ነገር ግን በጌታ ዘንድ ሴት ያለ ወንድ ወንድም ያለ ሴት አይሆንም» 1ቆሮ. 16፥11። ይህም ማለት የከበረውን ቃል ኪዳንና የተቀደሰውን ጋብቻ እንደ ቀላል አፍርሶና አርክሶ በእግዚአብሔር ፊት መቆም የማይሆን ነገር ነው። ከዝሙት በስተቀር በድንገተኛ ግጭት በዕለት ቁጣ ቢለያዩ ይታረቁ አንተራረቅም ቢሉ ግን በየራሳቸው ንጽሕናቸውን ጠብቀው መኖር አለባቸው እንጂ በየራሳቸው ሌላ ማግባት የለም። «ሚስትም ከባልዋ አትለያይ ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር ወይም ከባልዋ ትታረቅ። ባልም ሚስቱን አይተዋት ብዬ የተጋቡትን አዛቸዋለሁ። እኔ ግን አላዝም ጌታ እንጂ። 1ቆሮ. 7፥10። እዚህ ላይ ይቅር መባባል አቅቷቸው የሚለያዩ ከሆነ ከጌታ ትእዛዝ ውጭ ከመሆናቸው ሌላ በስመአብን እንኳ መጸለይ (መድገም) አይችሉም። ምክንያቱም «እናንተ ይቅር ባትሉ በሰማያት ያለው አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም» ተብሎአል። ማር.11፥26።

እንግዲህ የጋብቻ ነገር በመጠኑ ይኸንን ከመሰለ ጋብቻችንን በቤተ ክርስቲያን ጸሎት በሥርዓተ ተክሊልና በቅዱስ ቁርባን እናድርግ። ጋብቻውን የሚያጸናው የሚቀድሰው ጸሎትና ቅዱስ ቁርባን ነው።

ተክሊል ማለት ክብር ማለት ነው። ምክንያቱም በዚህ ሕግ ወንድ የባሏ ክብር ናት የተባለች ረዳቱን በጽኑ ኪዳን (በማይፈርስ ውል) የሚቀበልበት ስለሆነ ነው። 1ቆሮ.11፥7። ይኸውም ከለለ አከበረ ጋረደ ካለው ግስ የወጣ ዘር ነው።

ይህም ክብር የሚደረግላቸው ሰውነታቸውን ከዝሙት ከርኩሰት ጠብቀው «ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልዕዋ ለምድር» ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ያለውን አምላካዊ ትእዛዝ ለሚፈጽሙ ብቻ ነው። ለጊዜው ሰውነታቸውን ሠርተው ቀጥተው ለዚህ ክብር ያደረሱ ሰዎችም ከዚህ ከደገኛ ክብር እንዳይወድቁ እስከ መጨረሻው መጠንቀቅ አለባቸው። ዛሬ ዓለማችን በእጅጉ የመትቀጣበትንም መቅሰፍት (ኤድስ) ያስከተለው በዚህ ክቡር ሕግ በቅዱስ ጋብቻ አለመወሰንና ምሥጢራዊ በረከቱንም እንደዋዛ መቁጠር ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክረስቶስ፥ «እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየው» በማለት የጋብቻን ሕግ አጽንቶታል። ማቴ.19፥6። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህ ነገር ደገኛ ነገር ነው እኔስ ይህን የሙሽራውንና የሙሽራዪቱን ተዋሕዶ ለክርስቶስና ለምዕመናን ምሳሌ አድርጌ እናገራለሁ ብሏል። ኤፌ.5፥32።

እንግዲህ የዚህን ረቂቅ ምሥጢር ምሳሌነት የወረሱ ለታላቁ ክብር የደረሱ ሰዎች እስከ መጨረሻው ክብራቸውን መጠበቅ ተዋሕዶዋቸውን ማጥበቅ ይገባቸዋል። ያልበቃንም ከዚህ ክብር ለመድረስ ከኃጢአት በመመለስ ከበደል በመራቅ መዘገጃጀት አለብን። ይኸውም፥ «በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ» ይላልና። «እነሆ የተወደደ ሰዓት አሁን ነው፡ እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው።» እንደተባለ ነገ ተነገ ወዲያ ሳንል አሁኑኑ እንቅረብ። ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን አመንዝራነት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ፥ «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን ሴሰኞችንና አመንዝሮችን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል» ብሎ በግልጥ ነግሮናል። ዕብ.13፥14።

በገሊላው ቃና ሠርግ ከእነ እናቱ የተገኘ አምላክ ዛሬም በመካከላችን ይገኛል። የያኔውን ጋብቻ የባረከ የእኛንም ይባርክልናል። በሠርጉ ቤት በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ውሃውን ወደ ወይን ጠጅነት ለውጦ ሙሽሮቹን ከኃፍረት ያዳነ አምላክ ዛሬም ስለቸርነቱና ስለ እናቱ አማላጅነት ለቅዱስ ጋብቻ አብቅቶ የጐደለንን ይሞላልናል። በመስቀል ላይ የተቆረሰውን ሥጋውንና ደሙን ይመግበናል፤ የተባረኩ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ፍሬዎችንም ይሰጠናል። «የጻድቃን ልጆች የተባረኩ ናቸው» ተብሏልና። መዝ.111፥2።

ስለ ጌታችን በምንናገርበት ጊዜ ቅድስት ድንግል ማርያምን ለመለየት አንችልም። ምክንያቱም ወልዳ ያስገኘች አዝላ የተሰደደች በማስተማር ጊዜው ከአገር አገር አብራው የተንከራተተች ናት። በተሰቀለበት ዕለትም ከእግረ መስቀሉ ሥር አለተለየችምና።

በገሊላ ቃናው ሠርግ ጌታን ከእነናቱ እንደጠሩ በሥርዓተ ተክሊሉ ጸሎታችን ላይ «አባታችን ሆይ» ብለን ጌታን «እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ» ብለን እናቱንም እንጠራለን።

በዚህም የቸርነቱና የአማላጅነቷ ተጠቃሚዎች እንሆናለን። በጋብቻችንም ዕለት ሆነ በትዳር ሕይወት ውስጥ በምናደርገው ጉዞ በሚገጥመን ችግር ሁሉ ጌታ ከእነ እናቱ አይለየንም። ትናንት የተደረገው ሁሉ ዛሬም ለእኛ ይደረግልናል። ወደፊትም ሲደረግ ይኖራል ብለን እናምናለን። ምክንያቱም ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለ፥ «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት የነበረ ዛሬም ያለ ወደፊትም ለዘላለም የሚኖር ነውና። ዕብ.13፥8። ብሏል።

እንግዲህ እኛም በዚህ ተመርተን የምንፈጽመው ጋብቻ ቅዱስ ይሆናል። በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስም እናገኛለን። በአንድነትም የሰማይ ሕይወትና ክብር ተሳታፊዎች በመሆናችን የግድ መትጋት አለብን። ይህንንም ሁሉ ለመፈጸም የእግዚአብሔር ቸርነት የቅድስት እናቱ አማላጅነት አይለየን።

ረስተነው!

ለመሆኑ በዘመናችን ትውልድስ ጋብቻ እንዴት ይታያል? ያለጋብቻ መኖርና ከሥርዓት ውጭ የሚፈጸም ጋብቻ የሚያስከትለው ጠንቅስ ምን ይሆን? በሚቀጥለው እትማችን ይእነዚህን ጥያቄዎች መልስ አዘጋጅተን እናቀርባለን። ✣

# ሦስቱ አርእስተ ኃጣውዕ

ማቴ.4፥1–11።

በዚህ ምዕራፍና ቁጥር ያለው ንባብ የሚነግረን ጌታ ከተጠመቀ በኋላ በኢያሪኮ አካባቢ ወደሚገኘው ትልቅ (ቋራንዳርዮን) የአርባ ቀን ተራራ ተብሎ ወደሚታወቀው ተራራ ወጣ። በዚያ ደረቅ ተራራ ላይ ለመጾም ሔደ። በዚያም አርባ መዐልትና አርባ ሌሊት ጾመ። ከዚህ በኋላ ተራበ። በዚህ ጊዜ ጸላኤ ሠናያት በተከታታይ ሦስት ፈተናዎች ፈተነው። በመጀመሪያ ጌታ ርቦት ነበርና ሰይጣን መጥቶ ድንጊያ አቀረበለት። እነዚህን ባርከህ ወደ ዳቦነት ለውጥ አለው፤ ጌታም በዚህ ጊዜ የሰይጣን ታዛዥ በመሆን የሚገኘውን እንጀራ በመንቀፍ በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 10፥3። ያለውን ቃል ጠቅሶ ሰው በእግዚአብሔር ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ የማይኖር መሆኑን አስታወቀው። በዚህ ጊዜ ፈታኙ ፈተናውን ለውጦ ከቤተ መቅደስ ጫፍ ዘሎ እንዲወርድ በመዝሙር ስለእርሱ የተጻፈውን ጠቅሶ ጠየቀው። ይህም በሰይጣን ትእዛዝ ሊሆን እንደማይችል አሁንም ዘዳግም 6፥16። ጠቅሶ አስረዳው። በሦስተኛውም የዓለምን ግዛት የሚሰጠው መሆኑን ይህም የሚሆነው የሰገደለት እንደሆነ መሆኑን ሳይፈራ ተናገረ። በዚህ ጊዜ ጌታ በስሙ ጠርቶ፥ «አንተ ሰይጣን ከኔ ወግድ» አለው። በዚህ ጊዜ ጥሎት ሸሸ።

ከዚህ ምንባብ የምንማረው አንድ ታላቅ ትምህርት አለ። እግዚአብሔር አምላካችን ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ በመካከላችን በተገኘ ጊዜ የሰው ዘር በብዙ ምክንያት ለሰይጣን ሲሰግድ አግኝቶታል። ግማሹ በዳቦ ምክንያት ሌላውን በሥልጣን፥ ሌላውን በሀብት አይበቃኝም በማለት በስግብግብነት። በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረውን የሰው ሕይወት ለሚመለከት ሁሉ ይህ ሕይወት አሰቃቂ መሆኑን ይረዳል። በሐዲስ ኪዳንም ዘመን ብዙ ሰዎች ለዳቦ፥ ለሥልጣንና ለሀብት ሲሉ ለሰይጣን ታዛዥ ሆነዋል፤ ወንጀሎችን ፈጽመዋል። ለምሳሌ ይሁዳ፥ ሄሮድስ፥ የካህናት አለቆች፥ ጻፎች፥ ፈሪሳውያንና ሌሎችም። ሌሎች ደግሞ ዳቦው፥ ሥልጣኑና ሀብቱ ይቅርብን እንጂ ለሰይጣን አንሰግድም፥ አንገዛም፥ የሰይጣንንም ምክር አንቀበልም ብለው በዓለም ውስጥ ጊዜያዊ ፈተና ተቀብለው ሰይጣንን አሸንፈዋል። የሰይጣን ምክር አያዋጣምና ሰይጣን ለማስጐምጀትና ለማዋረድ እንጂ ለደህና ነገር ስለማይመክር ይህም በአዳምና በሔዋን ይታወቃል።

ይህን ቃል የምታነቡ ወንድሞች፥ እህቶች፥ እናቶችና አባቶች የክርስትና እምነት ሰውን ነፃ ያወጣው ሰይጣናዊ ፍላጐቱንና ምኞቱን ገድሎ ነው። የእኛም ሕይወት በክርስቶስ ነፃ የወጣ ስለሆነ ሰይጣናዊ ፍላጐታችን እንደገና ሕያው ሆኖ የሰይጣናዊ ፍላጐት ተገዥ እንዳንሆን ጥንቃቄ ያስፈልጋል። በዚህ በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ብዙ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እንጀራ ለማግኘት ሲሉ የሰይጣን ታዛዦች ሆነዋል። ወጥተው ወርደው፥ ሠርተው እግዚአብሔርን አስባርከው በመብላት ፈንታ ሠርቀው ቀምተው አወናብደው ለመብላት የተሠማሩ ሁሉ የሰይጣን ታዛዦች ሆነዋል። እግዚአብሔር ሳይፈቅድላቸው ጉልበታቸውንና ሥልጣናቸውን ለማሳየት የሚዘሉ ብዙዎች ናቸው። ብዙዎቹም እየወደቁና እየተሰበሩ ይታያሉ። እግዚአብሔር የሰጣቸውን በቃኝ ባለማለት ተጨማሪ ለማግኘት ሲሉ ለሰይጣን የሚሰግዱም በዚህ በአለንበት ክፍለ ዘመን ጥቂቶች አይደሉም። ሰይጣን ግን ቢያዘልልም ቢያሰግድም ሰውን ለማሳሳትና ከእግዚአብሔር ለማጣላት እንጂ ለደህና ነገር አይደለም። እንግዲህ እኛም ዛሬ የሰይጣንን ምክር አንስማ፤ ትእዛዙንም አንቀበለው። ወደ ንስሐ እንመለስ፤ ሥጋውንና ደሙን እንቀበል። ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት፥ ኅብረት ይኖረናል። ✣

ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ

ለናሙና ካዘጋጇቸው የጽሑፍ ስብከቶች የተወሰደ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

# በረከት ወንጌል

በዚህ ዓምድ ሥር የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የሚያስተምረንን ሕይወት በተከታታይ እናቀርባለን።

## ጸሎትህ ተሰምቶልሃል

ከዲ. ተክለወልድ

ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ለእግዚአብሔር ስለተፈጠረ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ይፈልጋል። መገናኛውም ጸሎት ስለሆነ ይጸልያል። ቀደምት አበው (የቀደሙ አባቶች) ጸሎት በሰቂለ ኅሊና በእንቃዕድዎ ልቡና በሰፊሃ እድ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደሆነ ነግረውናል። ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የመገናኛ ምልክትና ማጸኛ ነው። ጸሎት ኅብረትን፥ ምስጋናን፥ ስግደትን፥ ንስሐን፥ ልመናን፥ ምልጃን ያጠቃልላል። ሰዎች በልዩ ልዩ አቋቋም ቦታና ጊዜ ሊጸልዩ ይችላሉ። ዋናው ነገር ግን የልብ መሰበር ነው። ነቢዩ ዳዊት እንዳለ፥ «የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም» መዝ.50፥17። ቃሉም ትህትናን ገንዘብ ማድረግ እንዲገባ ያስተምረናል።

በሕይወቱ ውስጥ ጉድለት ያለበት ሰው ሁሉ የጨለመው እንዲበራለት፥ የጠመመው እንዲቃናለት፥ የጠወለገው እንዲለመልምለት፥ የተዘጋው እንዲከፈትለት፥ የተዘራው እንዲበቅልለት፥ የተተከለው እንዲጸድቅለት፥ የተወለደው እንዲያድግለት፥ የተበተነው እንዲሰበሰብለት፥ የተሰበሰበውም እንዲባረክለት ልመናውን በጸሎት ለእግዚአብሔር ያቀርባል። እግዚአብሔርም የልጆቹን ጸሎት በደስታ ይሰማልና ጸሎት ብዙ ኃይል አለው። 1ጴጥ.3፥12:ያዕ.5፥17። ጸሎቱ የተሰማለት ሰው ፈጥኖ ከሐዘኑ ይጽናናል። ከጭንቀቱ ይረጋጋል። ከትካዜ ባሕር ይወጣል፥ ከድካሙ ይበረታል።

በትእዛዙና ሕግጋቱ ሲመዘን ያለነቀፋ የሄደና በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የነበረ ካህን ዘካርያስ በአዲስ ኪዳን ዋዜማ እንደ ካህናት ሥርዓት ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ጽንሐውን ይዞ በሚያጥንበት ጊዜ ከዕጣኑ መሠዊያ በስተቀኝ መልአኩን በማየቱ ደነገጠ፤ ፍርሃትም ወደቀበት። ሉቃ.1፥11–13። ተፈጥሮአቸው ከማይጠፋ እሳትና ነፋስ የሆኑ ቅዱሳን መላእክት ኃይላቸው ታላቅ ስለሆነ የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ግርማ አላቸው። መዝ.12፥20:13፥4። እንኳን ሰው ምድር በፊታቸው ትንቀጠቀጣለች። እጅግም የሚያስፈሩ ናቸው። መልካቸው እንደ መብራት ልብሳቸውም እንደ በረዶ ነጭ ነውና። ማቴ.28፥2።

በዚህ ሁኔታ ለዘካርያስ የተገለጠው መልአክ፥ «ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ» ብሎ ካረጋጋው በኋላ ሚስቱ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ስሙም ዮሐንስ እንደሚባል ለዘካርያስም ተድላና ደሰታ እንደሚሆንለት በመወለዱም ብዙዎቹ ደስ እንደሚላቸው በጌታ ፊት ታላቅ እንደሚሆን የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ እንደማይጠጣ በእናቱም ማኅፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚ ቃኝ፥ ከእስራኤልም ልጆች ብዙዎቹን ወደ አምላካቸው እንደሚመልስ የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዳ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ እንደሚሄድ ለዘካርያስ በዝርዝር ነገረው። ይህ ሁሉ ሲሆን በዕጣኑ መሥዋዕት ጊዜ በውጭ ይጸልዩ የነበሩት ሕዝብ በዘካርያስ መዘግየት ከመደነቅ በቀር ምንም አላወቁም። ዘካርያስ፥ «እኔ ሽማግሌ ነኝ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን ዐውቃለሁ» በማለቱ መልአኩ መልሶ፥ «እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ እንድናገርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር። እነሆም በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም» ስለአለው ወዲያው ዲዳ ሆነ። ከመቅደስም በወጣ ጊዜ ለመናገር ባለመቻሉ ሕዝቡ ራእይ እንዳየ አስተዋሉ። እግዚአብሔር ለወዳጆቹ በራእይ ይገለጣልና በሕልምም ያነጋግራቸዋልና። ዘኁል.12፥6። ሉቃ.1፥8–23።

በብሉይ ኪዳን ታሪክ ነቢዩ ዳንኤል በኡባል ወንዝ መካከል ቅዱስ ገብርኤልን ጤግሮስ በተባለው



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

በታላቁ ወንዝ አጠገብ በፍታ የለበሰውንም ጥሩም የአፌዝን ወርቅ በወገቡ የታጠቀውን አካሉም እንደ በረሌ፥ ፊቱም እንደ መብረቅ እግሮቹም እንደ ጋለ ናስ የሚመስለውን የቃሉም ድምፅ እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ የነበረውን መልአክ ባየ ጊዜ እንደ ፊራ እንደተንቀጠቀጠ፥ እንደ ደነገጠ እና እንደሰገደ የዘካርያ ስም ፍርሃትና ድንጋጤ ከዚሁ አንፃር ነበር። በዚህም አባቶቹን ነቢያትን መስሎ ተገኝቷል። ዳን.8፥16: 10፥8። አባቱን የማይመስል ልጅ ግን ዲቃላ ነው። ዘዳግ.23፥2። ዕብ.12፥8። ዲቃላ ያይደለ የሕግ ልጅ ዘካርያስ መላእክትን ማክበር እንደ አባቶቹ ገንዘብ አደረገ።

ነቢዩ ዳንኤል በማታ መሥዋዕት ጊዜ ስለራሱና ስለሕዝቡ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ሲጸልይና ሲና ዘዝ ጸሎቱ ስለተሰማለት መሥዋዕቱ ስለሠመረለት ቅዱስ ገብረኤል እየበረረ መጥቶ ዳሰሰው፥ አስተማረው፥ ተናገረው። በአዲስ ኪዳን መግቢያ በር ላይ የነበረውም ጻድቅ ካህን ዘካርያስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ስለራሱም ሆነ ስለሕዝቡ ሲጸልይና መሥዋዕተ ዕጣን ሲያሳርግ መልአኩ ተገልጦ አነጋገረው። ዳን.9፥20። ሉቃ.1፥13። ዕጣን ጸሎትን የሚያሠምር የመዓዛ መሥዋዕት ነውና። ራእ.8፥3–4።

ሥጋንና እንጀራን ከመብላት የወይን ጠጅን ከመጠጣትና ዘይትም ከመቀባት ተከልክሎ ሰውነቱን በጾምና በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት አዋርዶ ለነበረው ነቢይ ለዳንኤል መልአከ እግዚአብሔር ተገልጦ የተወደድህ ሰው ዳንኤል ሆይ አት ፍራ ልብህ ያስተውል ዘንድ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል። እኔም ስለቃልህ መጥቻለሁ በማለት ፍርሃትን አርቆ እንዳበሰረው ለዘካርያስም «ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ» ብሎ ጸሎቱ ቅድመ እግዚአብሔር መድረሱን ነገረው። ዳን.10፥12። ሉቃ.1፥13። በዘመነ ሐዋርያት ለቆርኔሌዎስ «ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ» ተብሎ በመለአክ ቃል እንደተነገረው ማለት ነው። የሐዋ.10፥4።

ባለጠግነቱ ጥበቡና ዕውቀቱ ጥልቅ ፍርዱ የማይመረመር ለመንገዱም ፍለጋ የሌለው እግዚአብሔር ለሣራ ካረጀች ካፈጀች በኋላ ይስሐቅን፥ ለመካኒቱ የማኑሄ ሚስት በብሥራተ መልአክ ኃያሉ ሶምሶንን፥ በልጅ ዕጦት ብስጭት ከስታ ጠቁራ ከመብል ከመጠጥም ተከልክላ ለነበረች ለሕልቃና ሚስት ለሐና ነቢዩ ሳሙኤልን እንደሰጠ ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥም የሆድ ፍሬ ዋጋ ሊከፍላቸው የልጅ ስጦታ ሊሰጣቸው ፈቀደ። ዘፍጥ.18፥14። መሳ.13፥2። 1ሳሙ.1፥19። ሮሜ 11፥33። ነቢዩ ዳዊት እንዳለው «እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው የማሕፀንም ፍሬ ዋጋ ናቸው» መዝ.126፥3። ዘፍጥ.30፥2።

ዘካርያስ ሕገ እግዚአብሔርን አክብሮ የመቅደስን አገልግሎት አጽንቶ እምነትን ከምግባር አዋሕዶ በመገኘቱ በፍሬ ምግባር ላይ ፍሬ ማኅፀን እንደሚጨመርለት የሚገልጠውን ቃል ሰማ፤ ይህም በጸጋ ላይ ጸጋ በበረከት ላይ በረከት መሆኑ ነው። በብሉይ ኪዳን ልጅ አለመውለድ ልዩ ትርጉም ነበረውና የዘካርያስም ኀዘኑ ይኸው ነበረ። ይሁን እንጂ መልአኩ፥ «ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች። ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ተድላም ይሆንልሃል» አለው። በተለይም የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር የሚሆን ወንድ ልጅን መውለድ ታላቅ ደስታ ነበረ። የያዕቆብ ሚስት ልያ ለባልዋ ደጋግማ ወንዶች ልጆች በመውለድዋ «ደስታ ሆነልኝ ሴቶች ያመሰግኑኛልና» ብላለች። ዘፍጥ.30፥13። 1ቆሮ.11፥3።

የይስሐቅ መወለድ የአብርሃምና የሥራ፥ የሶምሶን መወለድ የማኑሄና የሚስቱ፥ የሳሙኤል መወለድ የሕልቃናና የሐና ደስታ ነበረ። የዮሐንስ ግን ልዩ ነው። ምክንያቱም ደስታው በወላጆቹ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ለብዙዎች ሰዎች ጭምር እንደሚሆን መነገሩ ነው። ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬያት አንዱ ደስታ በመሆኑ ዮሐንስን ደስታ ነው ለማሌት ይቻላል። ገላ.5፥22። ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ፍሬ ደስታ ዮሐንስን እንዲያፈሩ እግዚአብሔር የተከላቸው ዛፎች ናቸው «መልካም ዛፍ መልካም ፍሬ ያፈራልና» ማቴ.6፥17። መልካም ዛፍ የደጋግሰዎች ቅጠል የሃይማኖታቸው ፍሬ የምግባራቸው ምሳሌ ነው።

የዘካርያስና የብዙዎች ሰዎች ተድላና ደስታ የሚሆን ዮሐንስ ወደፊት ጌታን በማጥመቅ መጥመቀ መለኮት በመሰኘት ታላቅነቱ የሚገለጥ ነውና «በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና» ተባለ። ይህ ታላቅነት የሚገኘው ራስን በሰውና በፈጣሪ ፊት በትህትና በማሳነስ ነው። ማቴ.20፥26: 23፥12። ሉቃ.22፥26። ያዕ.1፥9: 4፥10። ምሳ.29:23። ከማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ በመሆኑ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ እንደማይጠጣ ተነገረለት። ይህ ምልክት በእሥራኤል ዘንድ ልማድ ነበረ። «ሰው ወይም ሴት ለእግዚአብሔር ራሱን የተለየ ያደርግ ዘንድ የናዝራዊነት ስዕለት ቢሳል ከወይን ጠጅና ከሚያሰክር መጠጥ ራሱን የተለየ ያድርግ» ይላል። ዘኍል.6፥2። ሶምሶን ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ እንደሚሆን ተነግሮለት ነበር። መሳ.13፥7። ዋናው ነገር



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ለአገልግሎት የተመረጠና የተለየ ሰው መሞላት ያለበት በእግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በወይን ጠጅ አይደ ለም። ሉቃ.21፥34። ሮሜ 13፥13። ኤፌ.5፥18።

ነቢዩ ዳዊትን በእናቱ ማሕፀን ሳለ ሰውሮ ግሩምና ድንቅ ሆኖ እንዲ ፈጠር ያደረገ፤ ነቢዩ ኤርምያስንም ገና በማሕፀን ሳይፈጥረው ያወቀው በማኅፀንም ሳለ የቀደሰው አምላክ ዮሐንስም በእናቱ ማኅፀን እያለ በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ እንዲቀ ደስም ፈቃዱ ሆነ። መዝ.138፥13። ኤር.1፥5። ሉቃ.1፥15። እግዚአብ ሔር የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ከወሰነላቸው፥ ከጠራ ቸው፥ ካጸደቃቸውና ካከበራቸው መካከል ታላቁ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት ነው። ሮሜ.8፥29። ጌታም በወንጌል፥«ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐነስ የሚበልጥ የለም» ማለቱ ለዚሁ ነው። ማቴ.11፥11።

ዮሐንስ በድንቁርና ጨለማ ያሉትን ወደ ዕውቀት ብርሃን ክርስቶስ እንዲመራ፥ በኃጢአት ያሉትን በንስሐ ወደ ጽድቅ እንዲመልስ፥ በአምልኮተ ጣዖት የተጠመዱትን ፈትቶ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር እንዲያመጣ የተመረጠ ነውና «ከእሥራኤል ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ አምላካቸው ይመልሳል» ተባለ። እሥራኤል አብዛኞቹ በኃጢአትና በበደል ምክንያት ከጌታ ተለይተው ነበርና ነው። በደል ከእግዚአብሔር ይለያል ኃጢአትም ከእግዚአብሔር ቸርነት ያርቃል። ይህም ምሕረቱ፥ ቸርነቱ፥ በረከቱ፥ ረድኤቱ፥ ርኅራ ኄውና ይቅር ባይነቱ ይሰወራል፥ ይርቃል ማለት ነው። ኢሳ.59፥2።

በነቢዩ በኢሳይያስ እንደተነገረ ቃለ ዓዋዲ ዮሐንስ ለጽድቅ ምድረ በዳ እና በረሃ የሆነውን የሰው ልቡና ጠርጐ አስተካክሉ ምቹ ጐዳና ፍኖተ እግዚአብሔር እንዲሆን የሚያመ ቻች፥ በኃጢአት ተሸርሽሮ ሸለቆ፥ በትዕቢት አብጦ ተራራ፥ በክፋት ጸንቶ ጠማማ የሆነውን ልብ የተስተካከለ ትሁትና ቀና አድርጐ መሢሕ ክርስቶስን እንዲቀበል የሚያ ሰናዳ፥ ነቢዩ ሚልክያስም እንደተና ገረ በድንገት ወደ መቅደሱ ለሚመጣ ጌታ መንገድን በፊቱ የሚያስተካክል በመሆኑ የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንደሚያሰናዳ ተነገረለት። መንገድ ጠራጊ መባሉም ለዚህ ነው። ኢሳ. 40፥3። ሚል.3፥1። ሉቃ፥1፥17።

ጌታ በወንጌል ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድትገቡ ታላቅም እንድት ሆኑ ተመለሱ እንደ ሕፃናትም ሆናችሁ ራሳችሁን አዋርዱ ባለው መንገድ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት ወንጌል ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ የሚሰ ብክ፥ ብዙዎች በትህትና ተዋርደው ለክፋት ነገር ሕፃናት እንዲሆኑ የሚመክር፥ እግዚአብሔርን የመፍ ራት ጥበብ የጐደላቸውን መንግሥቱ ንና ጽድቁን ወደ መፈለግ ጥበብ የሚመልስ፥ ከኃጢአት አዋቂነት ወደአለማወቅ ሕፃንነት የሚለውጥ በመሆኑ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልሳል ተባለ። የጻድቃን ጥበባ ቸው መሠረቱ እግዚአብሔርን ማፍ ራት ነው። ምሳ.1፥7። ማቴ3፥1። ማቴ.18፥3። 2ቆሮ.11፥20። ፍርሃት ሲባልም መጋቢነቱን፥ ፈጣሪነቱን፥ ጌትነቱን፥ ኃያልነቱን ዐውቆ በመንግሥቱ ሽረት በባህርዩ ሞት የሌለበት ጻድቅ ፈራጅ መሆኑን ማመን ነው።

ሣራ፥ «ካረጀሁ በኋላ በውኑ ፍትወት ይሆንልኛልን? ጌታዬም ፈጽሞ ሸምግሎአል» እንዳለች ዘካርያስም እኔ ሽማግሌ ነኝ፥ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ? በማለቱ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ይህ ቃሌ እስኪፈጸም ድረስ ዲዳ ትሆናለህ አለው። ሆኖም ዘካርያስ ተገሠጸ። «አባት የሚወደውን ልጅ እንደሚገ ሥጽ እግዚአብሔርም የወደደውን ይገሥጻልና።» ዘፍጥ.18፥12። ምሳ.3፥11። ሉቃ.1፥18። ተግሣጹ በዘካርያስ ልብ የተከሰተው ጥርጥር እንዲወገድ ነው። ሕዝቡ ለከበረ አባታችን ራእይ ተገልጦለት ነው አሉ እንጂ እንደ ደካሞቹ በኃጢአቱ ምክንያት ይሆን? ብለው አልተጠራ ጠሩም። ለመፍረድም አልቻኮሉም። እርሱም የአገልግሎቱ ወራት እስኪፈጸም ድረስ ከቤተ መቅደስ አልተለየም።

እንግዲህ ከዚህ የምንማረው ምንድነው? እኛስ ጸሎታችን እንዲሰ ማልን ምን እናድርግ? ከሐዘን ይልቅ ደስታን፥ ከጦርነት ይልቅ ሰላምን፥ ከመርዶ ይልቅ የምሥራችን የምንሰ ማው ምን ስንሆን ነው? ከሥር ጀምሮ ታሪኩን እንደተመለከትነው የሚያስ ፈልገው ነገር ዘካርያስንና ኤልሳቤጥን ሆኖ መገኘት ነው። ይኸውም በጌታ ሕግጋትና ትእዛዛት መኖር፥ ከጌታ ቤተመቅደስ አለመለየት፥ ከዕጣኑ መሥዋዕት አለመራቅ ነው። ዕጣኑ የዘላለም መሥዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ከቅዱስ ቁርባን አለመለየትን ያመለክታል። ዘካርያስ በቤተመቅደስ



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ቢዘገይም ሕዝቡ በትዕግሥት እንደ ጠበቁት ቅዳሴው ቢረዝምም ካህናቱ ከመቅደስ ወጥተው እስኪያቆርቡን በትዕግሥት መጠባበቅ አለብን። እንዘካርያስ ተስፋ ሳይቆርጡ እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ የሚፈልጉትን ለማግኘት እስኪያረጁ ድረስ እንደጸለዩ እኛም እስከመጨረሻው ተስፋ ሳንቆርጥ እንጸልይ። ስንጸልይም በአጭሩ አራት ነገሮችን እናስተውል።

1. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክረስቶስ በማቴ.21፥22 «አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ» ባለው መሠረት ያደርግልኝ ይሆን? ወይስ አያደርግልኝ ይሆን? እያልን ሳንጠራጠር በእምነት እንጸልይ። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጐድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን። ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን። የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕር ማዕበል ይመስላልና። ሁለት አሳብ ላለው በመንገዱም ሁሉ ለሚወላውል ለዚያ ሰው ከጌታ ዘንድ አንዳች የሚያገኝ አይምሰለው» በማለት አስተምሮናል። ያዕ.1፥5። የጥርጥር ማዕበል በልባችን ውስጥ የተነሣ እንደሆነ ኑሮአችን ሁሉ ማለት ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው በሁከት የተሞላ ይሆናል። የምንሻውንም አናገኝም። ይህ እንዳይሆን ነው የእምነት ጸሎት የሚያስፈልገው። እንዲያውም እግዚአብሔር የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሳ አምላክ ነውና «የጸለያችሁትንና የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ ይሆንላችሁማል» ትዕግሥቱ ካለ መቼም ይሁን መች አያስቀርባችሁም ማለት ነው። ማር.11፥23።

2. የምንለምነውን እንወቅ። የዘብዴዎስ ልጆች እናት ሳታውቀው ለልጆቿ መከራና ሞት እንደለመነች ጌታም «የምትለምኑትን አታውቁም» እንዳላት እኛም አለማመኑን አጥተ ንበት ጌታ ጨከነብኝ ስንል እንዳንገኝ ምን እንደምንለምንና ለምን እንደ ምንለምን ማወቅ አለብን። የሚቀረውን ርስት ምድራዊ ሳይሆን ርስት ዘላለማዊ መንግሥቱን፥ የሚጠፋ ሀብትን ሳይሆን የማይጠፋ ሀብትን መንፈስ ቅዱስን፥ ሥጋዊ መብልን መጠጥን ሳይሆን መንፈሳዊውን ሥጋ ወደሙን እንለምን ይሰጠናል። «ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል» ተብለናልና። ማቴ.6፥33። መንግሥቱን ሲል ሃይማኖትን ጽድቁን ሲል ምግባርን ነው።

«የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ» መባሉ ለዚህ ነው። ሉቃ.12፥13።

3. እንደ ፈቃዱ እንጸልይ። ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው። እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል የምንለም ነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመንነውን ልመና እንተቀበልን እናውቃለን» ባለው መሠረት የእርሱ ፈቃድ መንፈሳዊውን ነገር እንድንለምነው ነው። 1ዮሐ.5፥14። የሚቹን ሞት አይፈቅድምና ከዘላለም ሞት አድነን ብለን እንለምነው። ሕዝ.18፥32። ለዚህም ከኃጢአት መመለስ በደልን ማራቅ ተገቢ ነው።

4. በጸሎታችን ኃጢአታችንን እንናዘዝ «ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት» አይሆንምና አስቀድመን በሕይወታችን ውስጥ ያቈምነውን ኃጢአት በንስሐ ማስወገድ ይገባናል። በተቋረጠ መስመር ስልክ መደወልና በኃጢአት ሆኖ መጸለይ አንድ ነው። ነቢዩ ኢሳይያስ፥ «የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም። ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም። ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች። እንዳይሰማም ኃጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል» ብሎናል። ኢሳ.59፥1። ስለዚህ ራስህን ለካህን አሳይ ባለው መንገድ ኃጢአታችንን ተናዝዘን በንስሐ ታጥበንና ነጽተን እንጸልይ። አበው «ልብስ ሲያድፍ በውሃ፥ ሰውነት ሲያድፍ በንስሐ ይነጻል» ይላሉ።

ያን ጊዜ በምድር የታሰረው በሰማይ የተፈታ ይሆናል። ካህናቱ ይቅር ሲሉን በእርሱ ዘንድም ይቅር እንባላለን። ማቴ.8፥4። ማቴ.16፥19። ማቴ.18፥18። ዮሐ.20፥23። ከሁሉም አስቀድመን ግን የሰማዩ አባታችን ይቅር ይለን ዘንድ የበደሉንን ሁሉ ከልብ ይቅር ማለት አለብን። ማር.11፥26። «ሲበድሉ ማሩኝታ ሲበደሉ ይቅረታ የክርስቲያንነት ምልክት ነውና።»

መቼም ሁላችንም በዚህ የምን መራ ከሆነ ጸሎታችን ተሰምቶ ከማኅጸን የተባረከ ልጅ ከሜዳ የተባረከ ፍሬ እናገኛለን። የሰማዩ አባታችን እንኳን ለምነነው ሳንለም ነው የሚያስፈልገንን የሚያውቅ ነው። ማቴ.6፥8 በኤርምያስ አድሮ፥ «ለእናንተ የማሰባትን አሳብ እኔ ዐውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የከፋ ነገር አይደለም። እናንተም ትጠሩኛላችሁ። ሄዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ። እኔም እሰማችኋለሁ። እናንተ ትሹኛላችሁ በፍጹም ልባችሁ ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ ከእናንተም



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

ዘንድ እገኛለሁ» ያለ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ተናዝዘን የምንለም ነውን አውቀን እንደ ፈቃዱ በእምነት የምንጸልየውን ጸሎት ይሰማናል። ዘወትርም በበረከቱ፥ በረድኤቱና በቸርነቱ ከመካከላችን አይለይም። ኤር.29፥11።

አበው «የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ» እንዲሉ የጽድቅ ሁሉ ማሰሪያው ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ስለሆነ የዘለዓለም ሕይወተን ለማግኘትና ከእርሱ ጋር አንድነት እንዲኖረን ዘካርያስ የአገልግሎቱ ወራት እስኪፈጸም ድረስ ከመሰዊያው ውና ከዕጣኑ መሥዋዕት እንዳልተለየ እኛም የተፈቀደልን የአገልግሎት ዕድሜ በሞት እስኪፈጸም ከመሠዊያው ታቦትና ከዘለዓለሙ መሥዋዕት ከኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አንለይ። ዮሐ.6፥54። ዘካርያስ ሁሉንም ፈጽሞ ወደ ቤቱ እንደሄደ እኛም ዘመናችንን ፈጽመን የማይቀርነውና ወደ መቃብር ቤት መግባት አለብን።

ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ ጸሎታችንን ተሰሚ፥ መሥዋዕታችንን ጉዳይ ፈጻሚ ያድርግልን። ✣

## ሐመር

ሐ/ሃይማኖትንና ምግባርን ይዘሽ፥
መርህ ለጽድቃችን ዋስ ጠበቃ ሆነሽ፥
ርምጃሽ ቀጥሎ ሺ ጊዜ ሺህ ሩጠሽ፥
እኛን እያስተማርሽ ለእኛው ተንጎዳጉደሽ፥
ደመቅ ዳጐስ ያለ ዕውቀትን አካተሽ፥
ጊዜና ሁኔታው ዘመን ሳይቀይርሽ፥
ልዕልናን ሁሌ ገንዘብ አድርገሽ፥
ንኢ ንኢ ሐመር ጊዜሽን ጠብቀሽ።

ምትኩ አበራ
ወልደ ዓምደ ሃይማኖት

# ለበረከትም ሁን!

ዘፍጥ.12፥1–4።

ከባርክ

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሰማያትና የምድር ፈጣሪ እግዚአብሔር ከአንድ ሰው ጋር ሲነጋገር እንመለከታለን። ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ዕድል ያገኘው ይህ ሰው አብራም ይባላል። አብራም ማለት ታላቅ አባት ማለት ነው። ለዚህ ታላቅ አባት ከፈጣሪው ጋር መነጋገር መነሻ የሆነው እግዚአብሔር ያቀረበለት ጥሪ ነው። በሰባ አምስት ዓመቱ የቀረበለት ጥሪ ደግሞ አስደንጋጭ ቢሆንም ተስፋ ስለነበረበት አብራምን ብዙም እንዳላስደነገጠው ከንባቡ እናገኛለን በሰጠው ምላሽ።

ጥሪው፥ «ከአገርህ፥ ከዘመዶችህም፥ ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ» የሚል ነበር። ከተወለደበት፥ ከአደገበት፥ ክፉንም ደጉንም ካየበት ሀገሩ፥ ከወለዱትና ከአሳደጉት በሁሉም ጊዜ አብረውት ከነበሩት ወገኖቹ ይልቁንም ከአባትና እናቱ የሚለይ ጥሪ ነው። ደግሞ የሚጠራውን ሰማው እንጂ አላየውም። እርሱ የማያየውና አስቀድሞም የማያውቀው እግዚአብሔር ይህን በመሰለ ሁኔታ ሲጠራው አብራም ምንም ሳያቅማማ እንደተባለው ማድረጉን ወረድ ብለን ስናነብ እናገኛለን።

እንዲህ የተጠራው አብራም ከጠራው ከእግዚአብሔር የተነገረው ተስፋም ነበረው። «ታላቅ ሕዝብ አደርግሀለሁ፥ እባርክሀለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ፥ ለበረከትም ሁን፥ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ የምድርም ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» ብሎ እግዚአብሔር በቃሉ ይህን ተስፋ ሰጠው። ግሩም የሆነ ተስፋ፥ ድንቅ የሆነ ምርጫ ነው ለአብራም የተሰጠው። ይህ ተስፋ ለሀገሩ ለወገኖቹ ለአባቱና፥ ለእናቱ ከነበረው ፍቅር የበለጠ የእግዚአብሔርን ፍቅር በውስጡ ስለአቀጣጠለበት አላመነታም። ወዲያው ከሀገሩ ወጣ፤ ከወገኖቹም ተለየ፤ እናት አባቱንም ተወ፤ በረከት ፍለጋ፥ እግዚአብሔርን ፍለጋ፥ እግዚአብሔር ወደሰጠው ይኖርባትም ዘንድ ወደወሰነለት ሀገር። የእምነቱ ብርታት በድምፅ ብቻ ያነጋገረውን እግዚአብሔርን ስለአደገበት ምድር ስለካራን እንዲለውጥ አስገድዶት ከአባቱና እናቱ ይልቅ ለእግዚአብሔር አስገዝቶታል።

ይህ አብራም የጣዖት ጠራቢው የታራ ልጅ ቢሆንም የእግዚአብሔር ጥሪ ከጣዖት ንግድ ለይታዋለች፤ ለክብርና ለበረከት ጋብዛዋለች። የአበው ሁሉ አባት እንዲሆን በመመረጡና የቀረበለትን ግብዣ በሃይማኖት በመቀበሉ ከዑር ወደ ከነዓን እንዲሄድ አድርጋዋለች። ደገኛው አባት አብራም በፈቃደ እግዚአብሔር ስሙ የብዙ አሕዛብ አባት ይሆን ዘንድ አብርሃም ተባለ። ዘፍጥ.17፥1–5። ከአበው ሁሉ ይልቅ በደግነቱ የሚደነቀው የሕገ ልቡና ዘመን ፈርጥ የሆነ ይህ አብርሃም ብዙ ጊዜ ከፈጣሪው ጋር ቃል በቃል ለመነጋገር በቅቷል። መጀመሪያ ከዑር ሀገር ከካራን እንዲወጣ ሲጠራ ፈጣሪውን አነጋግሯል። ዘፍጥ.12፥1–5። በሴኬም፥ በአዜብና በቤቴል ቆይቶ በረሃብ ምክንያት ወደግብፅ ወርዶ ከተመለሰ በኋላ በኬብሮን አምላኩን አነጋግሯል። ዘፍጥ.13፥14–17። መሐን ነበርና ወራሽ እንደሌለው አስቦ ልቡናው በኀዘን በተነካ ጊዜ ፈጣሪው



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

እግዚአብሔር አነጋግሮታል። ዘፍጥ.15፥1–21። ስሙ በተለወጠለትና አብርሃም በተባለ ጊዜ ከእግዚአብሔር ተነጋግሯል። ዘፍጥ.17፥1። በመምሬ የአድባር ዛፍ ሥር እንግዶችን ለመቀበል በመጠባበቅ ላይ እያለ አንድነቱን ሦስትነቱን በገለጠለት ጊዜ እግዚአብሔር አነጋገረው። ዘፍጥ.18፥1–2። ሣራ ልጅ እንደምትወልድ ተስፋ በተሰጣት ጊዜ እግዚአብሔር አነጋገረው። ዘፍጥ.18፥14–15። ስለሰዶምና ገሞራ ብዙ ጊዜ ከፈጣሪው ጋር ተነጋገረ። ዘፍጥ.18፥22–ፍፃሜው። ልጁ ይስሐቅን እንዲሠዋለት በጠየቀው ጊዜ እግዚአብሔር አነጋግሮታል። ዘፍጥ.22፥1–18።

አብርሃም ከማንም በላይ ያለሕግ ቅንና ደግ ሆኖ በመገኘቱ ከፈጣሪው ጋራም እውነተኛ በሆነ ፍቅሩና በጽኑ እምነቱ በመተዋወቁ ንግግሩ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ኑሮው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ነበር። ሕይወቱን ሁሉ በድንኳን ውስጥ በመኖር ያሳለፈው አብርሃም በዘሩ ምድር እንደምትሞላ ተነግሮታል። እርሱ እግዚአብሔር ለተለየ ነገር የመረጠው፥ ለድንቅ ክብር ያኖረው፥ ማንም ለማያውቀው ምሥጢር የፈጠረው ሰው ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን በነበሩት አበው ሁሉ ዘንድ ምሳሌነቱ ሲነገር የነበረ የዓለም ሁሉ መመኪያና ተስፋ ነበር። ከዘሩ የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ እንዲወለድ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ በዘሩ ዓለም ሁሉ እንደሚባረክ ተነግሮለታል። ይህም ተስፋ ተፈጽሟል። «ይታደሏል እንጂ ይታገሏል?» ይሉታል እንዲህ ነው።

በሐዲስ ኪዳንም ለእግዚአብሔር መታዘዙ ዮሐ.8፥39–40። ዕራ.11፥17–19። ያዕ.2፥21–24። በሃይማኖቱ የምእመናን ሁሉ አባት መባሉና በክረስቶስ አምነው ዘለዓለማዊ ሕይወት ለሚያገኙት የሰው ልጆች ምሳሌ መሆኑ። ሮሜ.4፥1–3። ገላ.3፥6–7። ያመኑና ምግባርን የሠሩ ሁሉ የአብርሃም የግብር ልጆች መሆናቸው፤ ሮሜ 4፥11–12። ሮሜ 9፥7–8። ገላ.3፥7–9:29። ስለዚህ ጻድቅ ሰው ጎልተው የተነገሩ ማስረጃዎች ናቸው።

የጻድቁ የአብርሃም ሕይወት በንጽሕናና በቅንነት መኖር ሳይታሰብ እግዚአብሔር ብቻ በሚያውቀው ጥበብ ከአምላክ ጋር የሚያነጋግር መሆኑን ያስተምረናል። እርሱ በየዋህነት በነበረው መመላለስ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለመስማት ከእግዚአብሔርም ጋር ደጋግሞ ቃል በቃል ለመነጋገር ብቅቷል። ይህን የእግዚአብሔርን የጥሪ ቃል ለመስማት በሃይማኖት መዘጋጀት፤ እግዚአብሔርም ሲጣራ አቤት በሚል ከሁሉ በላይ ለእግዚአብሔርና ለጥሪው በቃሉ በሚታዘዝ ቅንና ታዛዥ ልቡና ዝግጁ መሆንን ያስተምረናል።

እግዚአብሔር ሲጣራ አባቴ፥ እናቴ፥ ዘመዶቼ፥ ሀገሬ ሳይሉ ለተጠሩበት የሕይወት ጎዳና ቆርጦና አምኖ መሄድን፥ ሳያመነቱና ሳይጠራጠሩ ማመንን፥ በሁሉም ሥፍራ በሁሉም ጊዜ እግዚአብሔርን ብቻ ዘመድና ረዳት አድርጎ እግዚአብሔርም የሰጠው ሁሉ ሀገር መሆኑን አውቆ የትእዛዛቱ ፈጻሚ መሆንን ያስተምረናል።

የክርስቲያኖች ሕይወት እግዚአብሔር የሚጎበኘው፥ የሚያነጋግረው፥ የሚመራው፥ የሚባርከው ሊሆን ያስፈልጋል። እንደ አብርሃም ያለ ሃይማኖት ነው የእግዚአብሔርን ድምፅ ወደ ሰው ሊያመጣው የሚችለው። መጠራትም የሚቻለው ለመጠራት በሚያበቃ ሕይወት የተገኙ እንደሆነ ነው። ያለበለዚያ ባዶ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርና የእግዚአብሔር በረከት የሚገኝበትን ጥሪ መስማት አይቻልም። በሥጋ ከሥጋ ለሆነ ነገርና ከምድር የሚገኘውን ክብር፥ ተድላ ደስታ ብቻ ተስፋ አድርጎ የሚኖርና ሀሳቡ ሁሉ በምድር የሆነ ሰው ለእግዚአብሔር ሊሆን አይችልም። በምድር ያለው ማንነቱ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ላይ የሰለጠነበት ማንም ቢሆን የሥጋውን ምኞትና ምድራዊ ፍላጎቱን ማሸነፍ ካልቻለ የእግዚአብሔርን የጥሪ ቃል ለመስማት አይችልም። የእግዚአብሔርን የጥሪ ቃል ለመስማት እንደአብርሃም መለወጥና እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ሕይወት መመላለስ ያስፈልጋል። ኑሮውን በድንኳን ውስጥ በመንገድ ዳር አድርጎ የሚያልፍ የሚያገድመውን እያስተናገደ ይኖር የነበረው አብርሃም ውስጣዊ ማንነቱን ለውጦ የሃይማኖትና የምግባር ሰው ስለነበረ ሥላሴን ማስተናገዱን፤ ቃል በቃል ከፈጣሪው ጋር መነጋገሩን ስናስተውል ምንኛ የእግዚአብሔር ሰው እንደነበር እንገነዘባለን።

አብርሃም እግዚአብሔር ሲጠራው አምኖ ከሀገሩ ወጣ፤ ከወገኖቹም ተለየ–አምላኩን ፍለጋ፥ በረከት ፍለጋ። አዎን፥ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለጣዖት አምልኮ ተገዝቶ በኃጢአት ይኖርባት የነበረችውን ሀገር እግዚአብሔር በሰጠው ከፈጣሪው ጋር እየተነጋገረ በሚኖርባት ሀገረ–ሕይወት ለውጦ፥ በሥጋ የወለዱትን እናትና አባቱን ብቻ ሳይሆን በአምልኮ እናት አባት የሆኑትን ጣዖታት ሁሉ ጥሎ ወደኋላም ዞሮ ሳያያቸው ሀገሩን ከነዓን እናት አባቱን እግዚአብሔር አድርጎ ከምድረ ካራን ወጣ።

ይህ ነው እንግዲህ በእውነት የእግዚአብሔር ሰው የሚባለው፤ የበረከት ጥሪ ከሁሉ በላይ የሆንለት በሃይማኖት የማያልፈውን ተስፋ ገንዘብ አድርጎ በሕይወቱ የሰለጠኑትን የሥጋ ገመዶችና የፍላጎት ማነቆዎች በጥሶ ለእግዚአብሔር ለመሆን በእግዚአብሔር ለመኖር ራስን ለውጦ መሄድ። ለዚህ ነው ከዘሩ የተገኘው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «ብፁዕ ሕዝብ ዘእግዚአብሔር አምላኩ–



© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

እግዚአብሔር አምላኩ የሚሆን ሕዝብ ንዑድ ክቡር ነው» በማለት የተነበየልን። መዝ.32፥12

ዓለማችን አብርሃምን የመሰሉ ቀደምት አባቶችን ያላፈራችውን ያህል ሁሉን ትተው እግዚአብሔርን ብለው የሚመንኑ ቅዱሳን ያልተፈጠሩባትን ያህል ዛሬ ደግ ሰው አጥታ የሥጋ ፍላጎት እያቃጠላት ትገኛለች። ያኔ የነበረው እግዚአብሔር ዛሬም አለ ወደፊትም ደግሞ ይኖራል። ዛሬ የታጣው እንደ አብርሃም ያለ ሃይማኖት እንደ ይስሐቅ ያለ ትህትና እንደ ኢዮብ ያለ ትዕግሥት ነው። ከዚህም የተነሣ የሰዎች የመጀመሪያው ሀሳባቸው ሥጋ–ሥጋዊ፥ መሬት–መሬታዊ፥ በመሆኑ ራሳቸውን ወስነው ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ሕይወታቸውን ባለመለወጣቸው ዳግማውያን አብርሃሞች የሉም።

የዛሬው ሰው አካል ባልነሱና ባልገዘፉ በረቂቃን የፍላጎትና የምኞት ጣዖታት አምልኮ የተያዘ በመሆኑና ከእነዚህ ተላቅቆ እግዚአብሔር ወደሚኖርባት ወደመረጣት አማናዊቱ ከነዓን–ቤተ ክርስቲያን–እንዲሄድ የቀረበለትን የሐዲስ ዘመን ወንጌላዊ ጥሪ ለመቀበል የተዘጋጀ ባለመሆኑ፥ ያልለዘበ ጥሬ፥ ያልታደሰ አሮጌ ልቡና ስላለው ደግ ሰው፥ አብርሃምን የመሰለ ሰው ማግኘት ከባድ ነው። በዘመናችን ላለ ሰው ዓለምንና ምናምንቱ ንብረቷን ጥሎ እግዚአብሔርን ፍለጋ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር መሄድ እንደድንቁርና ስለሚመስለው ጥበብ በሚመስል የአላዋቂነትና የድንቁርና ባሕር ውስጥ ተዘፍቆ ከፈጣሪው እጅግ ርቆ ይገኛል።

በዚህች ለጊዜው ብቻ ተውባ በምታስደስት ነገር ግን ከመቅፅበት በምታልፍ ምናምንቴ ዓለም ለዘለዓለም መኖርና መደሰት የማይቻል መሆኑን ዐውቆ የዓለማት ሁሉ ጌታ በሆነው በእግዚአብሔር እግር ሥር ራሱን ማስገዛት እንደሚገባው፥ በዚህ ዓለም የሚኖረው ኑሮ ጊዜያዊ መሆኑንና በኋላ በፍርድ ቀን ከእግዚአብሔር ፊት እንደሚቆም ላላወቀው የዘመናችን ባለጥበብ ትውልድ መንገሩና ማስተማሩ ሐላፊነት ነው።

በነገራችን ላይ ክርስትና ለዓለም ከተገለጸ ሁለት ሺህ ዓመት ሊሞላው ነው። ታዲያ የሰው ልጆች እውነተኛ ክርስቲያኖች ሆነው የሚገኙት መቼ ይሆን? እናስብበት።

በዚህ ዘመንስ አብርሃም አባታችን እያልን የምንናገር ክርስቲያን ነን የምንል እኛ ለመሆኑ ከአብርሃም ጋር ምን መመሳሰል አለን? በስም ብቻ በመመካት የአብርሃም ልጆች ነን ያሉ አይሁድ የተነገራቸውን ወቀሳ አስተውለን የስም ብቻ ክርስቲያኖች መሆናችንን በመረዳት ማንነታችንን መለወጥ እንደሚገባን ልናውቅ ጊዜው ዛሬ ነው። የክርስቲያናዊ ሕይወት ሰዎች፥ የሃይማኖትና የምግባር ሰዎች ዳግማውያን አብረሃሞች እንድንሆን ሀገራችን ከሆነች በኃጢአት ከምን ኖርባት ዓለም እንውጣ። ከተዛመድናቸውና እናት አባት አድርገን ከተገዛንላቸው ፈቃዳተ ዓለምና ገቢረ ኃጢውዕ እንለይ። ያንጊዜ እግዚአብሔር ይጠራናል። በቃሉም ያነጋግረናል። ከዓለም ባሕር ያልወጣ፥ ከኃጢአት ያልተለየ፥ ረቂቃኑን የምኞት ጣዖታት ከነዝግንትሉ ከልቡናው አውጥቶ ያልጣለ፥ ውስጣዊ ማንነቱን ያልቀየረ እርሱ ለእግዚአብሔር ሊሆን እግዚአብሔርን ለማነጋገር አይችልም። ስለዚህ እኛነታችንን በእግዚአብሔር ቃል መስታወትነት መመልከትና አብርሃምን መሆን ያስፈልገናል።

አብርሃምን የሆንን እንደሆነ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር፥ እግዚአብሔር ለእኛ ይቆማል። የተስፋ ሀገራችን ወደ ሆነች ሰማያዊት ምድር እንገባ ዘንድ ይባርከናል። ለትውልዱ ምሳሌ ሆኖ ዘወትር የሚነገርለት የአብርሃም ሕይወት የተለወጠ በመሆኑ ነው የተባረከው። የተቀደሰው የተለወጠ በመሆኑ ነው። ያላየውን የእግዚአብሔርን ድምፅ ብቻ ሰምቶ ሀገርን፥ ወገንን ትቶ ወደማያውቁት ሀገር በተስፋ መሄድ የቱን ያህል የጸና እምነት እንደሆነ ስናስተውል ደንዳናውና አለት ልቡናችን ምን ያህል እንደሚያስቸግረን ስንመረምር የአብርሃምና የእኛ ሕይወት አብዝቶ መራራቁን እናውቃለን።

ስለዚህ ሕይወታችንን መመርመር፥ ድካማችን ከእኛ ማስወገድ፥ ኃጢአታችንን ከእኛ ማውለቅና መጣል፥ ዓለም ሀገራችንን መናቅና በታደሰ በተለወጠ ሕይወት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያስፈልጋል። እስከመቼ በኃጢአት ታመን፥ ከፈጣሪአችን በረከት ርቀን፥ ለፈቃደ ሥጋ ጣዖታችን ዕጣን ስናጥንና ስናጋፍት እንኖራለን? ያለፈውን የድካምና የኃጢአት ኑሮ ሁሉ ትተን ውስጣችንንም ውጫችንንም ለውጠን በንስሐ ታጥበን በሕገ እግዚአብሔር በመጓዝ ሕይወት ለሚገኝበት የክርስትና ማኅተም ለሥጋውና ለደሙ ታዳሚዎች በመሆን፥ የመምሰል የነበረውን በእውነት የክርስትና ሕይወት በመተካት በእግዚአብሔር ቤትና በፊቱ በበረከት የምንኖር መሆን ይገባናል። የተለወጥን እንደሆነ አምላካችን «የሚባርኩህን እባርካለሁ ...ለበረከትም ሁን!» ይለናል።

ለበረከት እንድንበቃ እግዚአብሔር በቸርነቱ የአብርሃምን ሃይማኖት ይግለጥልን። ወላዲተ አምላክ በአማላጅነት ቅዱሳን በረድኤት መላእክት በጥበቃ ከሁላችን ጋር ይሁኑ አሜን። ✣

ወይትባረክ እግዚአብሔር

## አራት ነገሮችን የሚጠብቅ ሰው ፍጹም ነው።

1. ተስፋን በመቁረጥ በሌላው እጅ ያለውን የማይመኝ፤
2. ሲሰድቡት እየሰማ እንዳልሰማ ሆኖ የሚታገሥ፤
3. ለራሱ የሚወደውን ለሌላውም የሚወድ፤
4. ፈጣሪው እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ የሚጸና።

ከፈላስፎች አንዱ




© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org



## አስደሳች ዜና ለሕዝበ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት ጠብቆ የተዘጋጀ «<u>ዓምደ ሃይማኖት</u>» የተሰኘ መጽሐፍ በገበያ ላይ ውሏል።

«ዓምደ ሃይማኖት»

- የሃይማኖት ክፍፍል እንዴት ተጀመረ?
- አምሥቱ አዕማደ ምሥጢራት
- ክብረ ድንግል
- ታቦት
- ሥዕል እና ሌሎችም አርእስቶች ይገኙበታል።

አዘጋጅ – ብርሃኑ ጎበና

መጽሐፉን ማከፋፈል የምትፈልጉ በግቢ ገብርኤል ቤ/ክ ወደሚገኘው ዓምደ–ሃይማኖት የሰ/ት/ቤት ጽ/ቤት ብቅ በሉ።

በሐመር ቁጥር 1 እትም ላይ ያለ እርማት።

1. ገጽ 3 «እግዚአብሔር በስም፥ በገጽ በአካል» በሚለው ላይ <u>በግብር</u> የሚል ይጨመርበት።

2. ገጽ 7 «<u>ሉቃ.25፥53</u>» በሚለው ምትክ <u>ሉቃ.24፥53</u> ይተካ።

3. ገጽ 11 «<u>አቶ ቲና ያሜ</u>» የሚለው <u>አቶ ቲና ያምኤ</u> ይባል።

4. ገጽ 11 «<u>ኅዳር 19</u>» የሚለው <u>ጥር 19</u> ይባል።

5. ገጽ 13 «<u>ለብፁው</u>» በሚለው «<u>ለብፁዕ</u>» የሚል ይጨመር።

6. ገጽ 15 «<u>በታህሳስ ወር ላይ</u>» የሚለው <u>በጥር ወር ላይ</u> ይባል።

7. ገጽ 16 «<u>መልአክቱ</u>» የሚለው <u>መላእክቱ</u> በሚል ይታረም።


8. ገጽ 19 ‹<u>ቀኝ እጇ</u>» የሚለው <u>ቀኝ እጅ</u> ይባል።

9. ገጽ 19 «<u>መኰነን</u>» የሚለው <u>መኰንን</u> ተብሎ ይነበብ።

10. ገጽ 22 «<u>ይትዎን</u>» የሚለው <u>ፌትዎን</u> ተብሎ ይታረም።

11. ገጽ 31 «<u>መዝ.101፥1</u> የሚለው <u>መዝ.121፥1</u> በሚል ይታረም።

© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org




© ማኅበረ ቅዱሳን 2003 ዓ.ም. www.eotcmk.org

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡